# ምዕራፍ ፩

## ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት።

ኢትዮጵያውያን፡ በአጠቃላይ፡ መሳውን *የሰውን ዘር*÷ በተለይም *የእግዚአብሔር ሕዝብ* የኾነውን ወገን በመወከልና ስለእነዚሁ ሰብአውያን ፍጡሮች ደህንነትና ጥቅም ሲሉ፡ ጠብቀው ያቆይዋቸው፡ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ምን እንደኾኑ፡ በዚህ መልእክት ውስጥ፡ በተቻለ መጠን አጠርና ጠቅለል ባለ አቀራረብ ለማስረዳት እሞክራለሁ።

ሰብአዊዉን ፍጡር፡ *የሰው ዘር* እና *የእግዚአብሔር ሕዝብ* በሚል መልክ፡ በግልጽ ለይቼ፡ ያመለከትሁት፡ ያለምክንያት አይደለም። ያም ምክንያት፡ በምድር ላይ ለቤተሰባዊ ኑሮ ወጣኞች የነበሩት ቀዳሚዎቹ ሰዎች፡ እርስ በርሳቸው ከነበራቸው ማኅበራዊ ግንኙነት፡ በገሃድ በተከሠተው እውነታ ላይ የተመሠረተ ነው። ያም እውነታ፡ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬዪቱ ዕለት ድረስ፡ የእነርሱ ዝርያዎች በኾኑት ትውልዶች መካከል፡ ህልውናው ሳይቋረጥ ቀጥሏል።

በፍጥረት መነሻ ዘመን፡ አቤልና ቃየል በተባሉት፡ የአዳምና ሔዋን፡ የመጀመሪያዎቹ ወንዶች ልጆች መካከል ደርሶ እንደታየው ኹሉ፡ ዛሬም፡ "ኢትዮጵያውያን፡ ወይም ዐምሐራ፡ ወይም ክርስቲያን ነን" በሚሉት መካከል እንኳ፡ እውነተኞቹ÷ ታማኞቹና ዓይነተኞዎቹ *የእግዚአብሔር ልጆች* ተብለው፡ በቀኙ ወገን ሲገኙ፡ ሓሰተኞቹ÷ አስመሳዮቹና ግብዞቹ ደግሞ፡ *የሰው ልጆች* የሚል መለያ ተሰጥቷቸው፡ በግራኛው ወገን ተመድበዋል። *የእግዚአብሔር ልጆች፡* ከአቤልና ከተተኪው ከእሴት አንሥቶ፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ዓላማ ልኡካን በመኾን ያገለግሉና የሚያገለግሉ ሲኾኑ፡ *የሰው ልጆች*[፴፪] ግን፡ ከቃየል ጀምሮ፡ የሰይጣን የክፋት ዕቅድ አገልጋዮች ኾነው ይኖራሉ።

እንግዴህ፡ የዚህን መጽሐፍ ሓተታ ለማሳጠር ስል፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሕዝብና አገር ኾነው ባሳለፏቸው፡ በሰባቱ ሺህ ዓመታት የህልውና ዘመናቸው ውስጥ፡ እነዚህን ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት በሙሉ፡ እንዴት ጠብቀዋቸው እንደኖሩ፡ የተጠቀሙባቸውን መንገዶች ኹሉ፡ "ኢትዮጵያዊው÷ በማንነቱ ፍለጋ!" በሚለው የመልእክት መጽሐፌ ውስጥ፡ በሚበቃ ያስረዳሁ ስለኾነ፡ በዚህኛው፡ ኹለተኛ፡ የመልእክት መጽሐፌ ውስጥ፡ ከዚያ የቀረውን ከማሟላት በቀር፡ እንደገና አንድ በአንድ በዝርዝር ከማስረዳት ተቆጥቤአለሁ። ከዚህ ይልቅ፡ በዚሁ መጽሐፍ መቅድም ውስጥ እንደተገለጸው፡ የዘር÷ የመልክ÷ የጾታ÷ የሃይማኖት÷ የሙያና የሥነ መንግሥት እምነት ልዩነት ሳይከለክሉት፡ ይህን መልእክት በሚያነብበው ኾነ በሚያዳምጠው፡ በማናቸውም ግለሰብ ዘንድ÷ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው ጭምር÷ እያንዳንዱ ኪዳን፡ ሊኖረው የሚገባውን በጎ ተቀባይነትና በሕይወቱ ላይ፡ ሊያስከትል የሚችለውን መልካም ለውጥ፡ ከኢትዮጵያዊው አመለካከት አኳያ ማብራራትን መርጫለሁ።

ይህ በሚኾንበት ጊዜ፡ እርግጥ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ በይበልጥም፡ ቃል ኪዳናቱን የተቀበሉት፡ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፡ እያንዳንዳቸው፡ እየራሳቸውን በነፍስ ወከፍ ጠይቀው መልስ ሊሰጡበት የሚገባ ዓቢይ ቁምነገር አለ! ይኸውም፡ በእያንዳንዱ የቃል ኪዳን ሓተታ ፍጻሜ ላይ፡ "ታዲያ፥ እኔ ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ ወይ?" ለሚለው ጥያቄ ተገቢውንና ትክክለኛውን ሙሉ መልስ መስጠት ግድ መኾኑን መገንዘብ ነው።

እንግዴህ፡ መልሱ፡ "አዎን፥ ፈጽሜአለሁ!" የሚል ኾኖ ከተገኘ፡ በብዙ የሚያስደስት፥ "እጅግ መልካም!" እና "የምሥራች!" የሚያሰኝ ነው፤ ራስን፡ ለዚህ ድል ለማብቃት መቻል፡ የራስን ማንነትና ጀግንነት፡ ለራስ ማረጋገጥ ነውና። ለቀራጥ መንፈሳዊ እርበኛ፡ ረድኤቱ ቅርብ የኾነውን፡ እግዚአብሔርንም፡ ማመስገን ይገባል። ይህም ቢኾን፡ በሥጋ ለባሽ ፍጡር ዘንድ፡ ፍጹምነት የለምና፥ ፈጣሪም፡ ከፍጡሩ፡ ይህን የመሰለውን ብቅዓት እንደማይጠብቅ ተናግሩዋልምና፡ ምንጊዜም የፍጹምነት ጉድለትን፡ በንስሓ ማስተካከልና ማረጋገጥ፡ በጣሙን አስፈላጊ ይኾናል።

መልሱ ግን፡ "የለም፥ አልፈጸምሁም!" የሚል ከኾነ፡ እንኳንስ ከፈጣሪ ጋር፡ በደም ማኅተምና መሐላ የተደረገ ቃል ኪዳን ይቅርና፡ ከፍጡር ጋር የተደረገ፡ ተራ ውል እንኳን ቢኾን፡ ግዳጁ ሳይከበርና ሳይፈጸም ቢቀር፡ ድርጊቱ፡ ጥፋትና በደል ኾኖ፡ ቅጣትን ማስከተሉ አይቀርም። ይኹን እንጂ፡ የቅዱሱ ኪዳን ግዳጅ፡ እንደፍጡር ሕግና ውል፡ "ያዘው! እሠረው! ቅጣው! ዕዳውን አስከፍለው! ካልቻለ፡ ንብረቱን ውረሰው! እምቢ ካለ፡ ግረፈው! ውገረው! ስቀለው! ግደለው!" የሚለውን ፍርድ የምታስከትል አይደለችም፤ በእርሷ ላይ የተፈጸመ ማናቸውም ዓይነት የጥፋትና የበደል ኃጢአት፡ በንስሐ ይወገዳል።

ንስሐ፡ ጥፋትንና በደልን አምኖ፡ ያለጥርጥር፡ መለኮታዊዉን ምሕረት የሚያስገኘውን ይቅርታ፡ በመንፈስና በእውነተኛ አምልኮ በመጠየቅ፡ ራስን፡ በሥጋም፥ በነፍስም፡ ከተዋዋዩ ፈጣሪ ጋር ማስታረቅና ማስማማት ነው፤ የቅዱሱ ኪዳን ግዳጅ፡ ከዚህ የሃይማኖት ምግባር አያልፍም። ይህ ጸጋ፡ የቃል ኪዳኑ ተዋዋይ የኾነው፡ አጥፌ ወንጀለኛ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከተበዳዩ ፈጣሪ በልግሥና የቀረበለት ፍጹም ስጦታ ነው፤ አጥፊው ወንጀለኛ፡ ተቀብሎ ይወስደውም ዘንድ፡ ለእርሱ፡ ምንጊዜም ተዘርግቶና ክፍት ኾኖ ይጠብቀዋል።

ጥፋቱና በደሉ፡ በዚህ መልክ፡ በንስሓ ከተወገደ በኋላ፡ ቃል ኪዳኑን አክብሮ እየፈጸሙና ሲያጠፉም፡ በንስሓ እያደሱ መኖር ይገባል። ጥፋቱና በደሉ፡ በንስሓ ሳይወገድ እንዲቀጥል ከተደረገ ግን፡ በግል ሕይወት፥ በቤተሰብና በአገር ደረጃ፡ ይኸው እስካሁን እየደረሰ ያለው የውርደትና የውድቀት መከራ፡ በበለጠ ጽናትና ስፋት እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው።

## የመጀመሪያው ቃል ኪዳን፤
## ኪዳነ አዳም ወሔዋን።

እግዚአብሔር፡ ከሰብአዊ ፍጡሩ ጋር ያደረገው የመጀመሪያው ቃል ኪዳን፡ ከቀዳማዊው አዳምና ከቀዳማዊቷ ሔዋን ጋር የፈጸመው ነው።

ኢትዮጵያ፡

ይህ ቃል ኪዳን፡ በጋብቻ ሥርዓት፡ ዘለዓለማዊነትን ተቀዳጅቷል። በእግዚአብሔር መልክ፡ መሰሉን ሰብአዊ ፍጡር፡ በሥጋ ልደት በማስገኘቱ፡ የዚህ የጋብቻ ዕፁብ ድንቅ ምሥጢር፡ ለፍጹም የልዕልና ፍሬ በቅቶና ገሃድ ኾኖ ተገልጿል። እግዚአብሔር፡ በዚህ ሕያው ፍሬ አማካይነት፡ *"በመልኩ፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ባረካቸውም፤ ...ኹለቱም አንድ ሥጋ ይኾናሉ!... ብዙ! ተባዙ!"* ያለው ቃሉ ተፈጽሞ፡ ጋብቻ ያስገኘውና በምድር ላይ ለተከሠተችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ተቀዳሚና መሠረታዊ የኾነው የቤተሰብ አቋም፡ ቅድስናው፥ አንድነቱና ፍሬያማነቱ ተረጋግጦበታል።[፵፫]

"ወንድ"፥ "ሴት" ተብለው የሚታወቁትና የዛሬዎቹ አዳምና ሔዋን የኾኑት፡ ኹለቱ የሰው ዘር ጾታዎች፡ በዳግማዊውና በፍጹሙ አዳም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ እንዲሁም፡ በዳግማዊቷና በፍጹሟ ሔዋን፡ በድንግል ማርያም የተገኘውን መለኮታዊ ጸጋ፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ ይህን የጋብቻ ቃል ኪዳን በሚፈጽሙበት ጊዜ፡ የዚያ፡ የተቀደሰው ቃል ኪዳን ዘለዓለማዊ በረከት፡ በቅድሚያ፡ በኹለቱ ተጋቢዎች፥ ቀጥሎ፡ በልጆቻቸው፥ በመጨረሻም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ቤተ ሕዝብ በሚያስገኘው፡ በመላው ቤተሰብ ላይ ያድርባቸዋል።

## ቀዳማውያኑና ዳግማውያኑ
## አዳምና ሔዋን።

የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፡ "ቀዳማውያን"፥ የእነርሱን ዕዳና ካሣ፡ በየራሳቸው ቤዛነት የከፈሉት፡ የመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እና እናቱ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ "ዳግማውያን" ተብለውና ተለይተው፡ ለምን መጠራት እንደተገባቸው፡ ከዚህ የሚከተሉት፡ የመለኮታዊው ዕቅድ ባሕርያት ማብራሪያዎች ያመለክታሉ።

፩) ቀዳማዊቷ ሔዋን፡ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ድንቅ ሥራ፡ ከቀዳማዊው አዳም ወጥታ፡ በሰውነት አካል ስለተገኘች፡ የጋብቻቸው ውህደት፡ ሥጋዊና ፍጹም መኾኑ፡ በጽኑ ታውቋል፤ ታምኖበታልም።

ዳግማዊዉን አዳም፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና ዳግማዊቷን ሔዋን፡ ድንግል ማርያምን በሚመለከት ግን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመገኘቱ (በመወለዱ)፡ በእነዚያ በቀዳማዊዎቹ አዳምና ሔዋን የደረሰው ኹኔታ ኹሉ፡ በዲያብሎስ ሰይጣናዊ ተንኮል ከተካኼደበት፡ ከክፉ ባሕርዩና ከጥፋት ገጽታው፡ ፈጽሞ ተለውጦ፡ መለኮታዊው ምሥጢር በተጠበበበት፡ በደገኛው ባሕርይና በትድግና (በማዳን) ገጽታው፡ ተከናውኖ ተፈጽሟል! ይህም ማለት፡ በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ግብር፡ የመለኮት አካልና ባሕርይ፡ ከሰውነት አካልና ባሕርይ ጋር፡ በ"ተዋህዶ" አንድ የመኾኑ ምሥጢር፡ በዳግማዊዎቹ አዳምና ሔዋን ተከሥቷል። "ተዋህዶ"፡ የሚለው ኢትዮጵያኛ ቃል፡ ከግእዝ የተገኘ ሲኾን፡ ዝክረ ነገሩ፡ ስለምሥጢረ ሥጋዌ፡ ማለትም፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የሚታወቅበት ትምህርት ነው።[፵፬]

፪) በቀዳማዊው አዳምና በቀዳማዊቷ ሔዋን መካከል የነበረው ዋናና ወሳኝ ግንኙነት፡ በባልና ሚስት፡ የጋብቻ አንድነት ተመሥርቶ፡ ፍትወት የጸናበት፡ ሥጋዊ መኾኑ ተረጋግጧል።

ይኸውም፡ ኹለቱም፡ በከፋት ኃይል ተሸንፈውና ተመርተው፡ በፈጣሪያቸው በእግዚአብሔር ላይ፡ ያሴሩት ዓመፅና ያለመታዘዝ ጠንቅ የፈጸሙት፡ የኃጢአት ሥራ፡ በሞት ዋጋ ስለመሰከረባቸው ነው። ይህም አድራጎታቸው፡ ራሳቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ልጆቻቸውን+ ተከታታዩንም ዘራቸውን ኹሉ ጭምር፡ ለሞት ጽዋ የዳረገ፡ መለኮታዊዉን ፍርድ አስከተለባቸው።

በዳግማዊው አዳምና በዳግማዊቷ ሔዋን መካከል ያለው ግንኙነት ግን፡ በእናትና ልጅ መካከል ባለ፡ ፍጹም ፍቅርና ቅድስና የተመላ መንፈሳዊው ኃይል የሰፈነበት ነው። በዚህ መንፈሳዊ ግንኙነት ምክንያት፡ ዳግማዊው አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዳግማዊቷ ሔዋን በድንግል ማርያም ማሕፀን ተጸንሶ ሰው በመኾኑ+ እንዲሁም፡ እናትና ልጁ፡ ኹለቱም፡ ለእግዚአብሔር አብ ፈቃድ፡ ፍጹም ታዛዦች ኾነው በመገኘታቸው፡ በምልዓት የወረደው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ የዳግም ልደትን ክብር ላቀዳጃቸው የእግዚአብሔር ልጆች፡ ጽድቅን+ ምሕረትንና ዘላለማዊ ሕይወትን አውርሷቸዋል።[፴፫]

፫) እግዚአብሔር፡ በምድራዊ ፍጥረቱ ላይ እንድትሰፍን የመሠረታትን መንግሥቱን፡ በንጉሥነትና በንግሥትነት እንዲያስተዳድሩ፡ ቀዳማዊውን አዳምና ቀዳማዊቷን ሔዋን ሾሟቸው ነበር። እነርሱ ግን፡ ይጠብቁት ዘንድ የሰጣቸውን ሥርዓት፡ ከነመመሪያው፡ እያወቁና ኾን ብለው ስላፈረሱት፡ ይህን የዘውድ ክብርና መብት+ መለኮታዊዉም ትእዛዝ፡ ያስገኘላቸውን ጸጋና በረከት ከማጣት ደረሱ።

ዳግማዊው አዳምና ዳግማዊቷ ሔዋን ግን፡ ለእግዚአብሔር አብ፡ ባላቸው ፍጹም ታዛዥነትና ታማኝነት፡ እስከመጨረሻው የጸኑ ኾነው ተገኝተዋል፤ በቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋን፡ የታጣውንም ኹሉ፡ በበለጠና በተሻለ መልክ፡ ወደነበረበት ቦታ፡ እንደገና መልሰውታል።

ከዚህ የተነሣ፡ ዳግማዊው አዳምና ዳግማዊቷ ሔዋን፡ ሥጋዊውን ብቻ ሳይኾን፡ መንፈሳዊዉን ፍጥረተ ዓለም ጭምር በምታጠቃልለው፡ በመላዋ የእግዚአብሔር ሕያውት መንግሥት ላይ፡ በዘለዓለማዊ ንጉሥነትና ንግሥትነት ነግሠው፡ እንዲመሩ፡ ሙሉና ፍጹም የኾነውን መለኮታዊ ሥልጣን ተቀዳጁ።[፴፬]

፬) ይህን ቃል ኪዳን ለፍጹምነት ለማብቃት፡ መለኮታዊውን ዕቅድ በመከተል፡ ከውጥኑ ጀምሮ እስከመጨረሻ ግቡ፡ የተደረገው አካኼድና የተፈጸመው ድርጊት ኹሉ፡ አስደናቂነቱ፡ አድማስ የሚወስነው+ ምሥጢሩም፡ በሥጋዊ አእምሮ ሊደረስበት የሚቻል አይደለም። ይህም እውነታ፡ ቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋን፡ የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ ባፈረሱበት ዕለት፡ በትንቢት ተነግሮአል።

በዚያች ዕለት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ የመለኮታዊው ትእዛዝ መፍረስ፡ በፍርድ ያስከተለውን የመርገም ውሳኔ፡ ለጥፋተኞቹ በሚያስታውቅበት ጊዜ፡ እባቡን (ማለትም፡ ዲያብሎስን)፡ እንዲህ አለው፦ "*ይህን ስላደረግህ፡ ...ባንተ* (በዲያብሎስ) *እና በሴቲቱ* (ማለትም፡ የመጨረሻዋ ሔዋን በኾነችው፡ በድንግል ማርያም) *መካከል+ በዘርህ* (ማለትም፡ የከፋት መናፍስት ወይም የክርስቶስ ተቃዋሚው) *እና በዘርዋ* (ማለትም፡ በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ+ በኢትዮጵያውያን ልጆቿና በእርሷ እመ አምላክነት አምነው በሚማጸኗት ክርስቲያኖች) *መካከል፡ ጠላትነትን አደርጋለሁ!*

*"እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም መንፈስ ቅዱስ)፡ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም (ዲያብሎስ)፡ ሰኰናውን ትነክሳለህ።"*[፴፮]

ኢትዮጵያውያን፡ ይህ፡ የጋብቻ ምሥጢርና ሥርዓቱ፡ በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት፡ ለእግዚአብሔር ሕዝብነት አቋማቸውና ለአምልኮተ እግዚአብሔር ሃይማኖታቸው፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር ላለው አስተዳደራቸውም፡ ቀዳሚው መሠረታቸው ስለኾነ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምረው እስከኖኅ፥ ከዚያም፡ ለኢትዮጵያዊነት ዘራቸው፡ ግንዳቸው እስከኾነው፡ እስከመልከ ጼዴቅ ድረስ፡ የተለየ ክብርና ጥንቃቄ ሰጥተውት እንደኖሩት ኹሉ፤ ዛሬም፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ ይህንኑ አጽንተውት ይገኛሉ። ለጋብቻቸው፡ አንድነትና አማናዊነት፥ ለባልና ሚስትነት ፍቅራቸውና ዘለዓለማዊነትም፡ አብነት የሚያደርጉት፡ ቀዳሚዎቹን አዳምና ሔዋን ሳይኾን፡ በዳግማውያኑ አዳምና ሔዋን የተገኘውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው። ይህም ማለት፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፥ እያንዳንዷም ኢትዮጵያዊት፡ ለሥጋዊው አኗኗራቸውና ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው፡ "አርአያ" አድርገው የሚከተሉት፡ ወንዱ፡ የፊተኛውን አዳም ሳይኾን፡ የኋለኛውን አዳም፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲኾን፡ ሴቷ ደግሞ፡ የፊተኛዪቱን ሔዋን ሳይኾን፡ የኋለኛዪቱን ሔዋን፡ ድንግል ማርያምን ነው።

ለዚህም፡ ሌላውን፡ የራሳቸውንና የቅርቦቹን በመተው፡ ዓለም በተቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሳይቀር፡ ዝክረ ነገራቸው የተገለጸውን፡ የአባቶቻቸውንና የእናቶቻቸውን፡ የነመልከ ጼዴቅን ተከታይ፡ የነዮቶርን፥ ቀጥሎም፡ ሴት ልጁን፡ ሲጳራን የዳረለትን፡ የነሙሴንና የዚችውን፡ ኢትዮጵያዊት ሚስቱን፥ እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ ለዳዊት የሰጠውን የቃል ኪዳን ዘር ለመቀበል፡ ወደኢየሩሳሌም፥ ወደእስራኤላዊው ንጉሥ፡ ወደሰሎሞን የተጓዘችውንና በኋለኛው የመጨረሻ ዘመን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ለወለደችው፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ አርአያ በመኾን፡ አንድ ልጇን፡ ምኒልክን እስከትፀንስ ድረስ፡ በድንግልናዋ ጸንታ የኖረችውን፡ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የነማክዳን፥ በማጠቃለያም፡ የራሷን፡ የድንግል ማርያምን ወላጆች፡ የነኢያቄምንና የነሐናን የጋብቻና የትዳር ሕይወት፡ በምሳሌነት መጠቃቀሱ ይበቃል።

## ኢትዮጵያ፡
## ስለጋብቻ ሥርዓቷ ስትፋረድ!

*ታዲያ፥* እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ ከመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን ሥነ ፍጥረቱ፡ አንድ ያደረገውን ጋብቻን፡ ኢትዮጵያውያን እንዲህ አድርገው፡ በቅዱሱ ኪዳን ጠብቀውና አጽንተው፥ አክብረውና አስከብረው መኖራቸው እየታወቀ፡ በአሁኑ ጊዜ፡ የእነርሱ ልጆች "ነን" የሚሉት፡ ወይም "ናቸው" የሚባሉት ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፡ በሚፈጽሙት የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቱ በሚመረቁበት ጊዜ፡ በረከታቸው ያድርባቸው ዘንድ፡ ስማቸውና ጋብቻው፡ በመልካም ምሳሌነትና አርአያነት፡ በንግግርና በዜማ እየተወሳ ሊሞገስ የሚገባው፡ የእኒህ የኢትዮጵያውያኑ፡ የሙሴና የሲጳራ፥ የኢያቄምና የሐና፥ የመጥምቁ ዮሐንስ ወላጆች የኾኑት፡ የዘካርያስና የኤልሣቤጥ፥ የቅዱስ ላሊበላና የባልተቤቱ የመስቀል ክብራ፥ እንዲሁም፡ የጻድቁ አባ ተክለ ሃይማኖት ወላጆች የኾኑት፡ የጸጋ ዘአብና የእግዚእ ኃረያ ስምና ጋብቻ ነበር።

ነገር ግን፡ ይህ መኾኑ ቀርቶ፡ በልማድ እንደሚደረገው፡ ተደጋግሞ የሚነሣው፡ የአብርሃምና የሣራ ስምና ጋብቻ ነው። ይህም፡ ከላይ በተገለጸው ምክንያት፡ ተገቢና ትክክል ባለመኾኑ፡ ሊታረምና ሊስተካከል ይገባዋል።

ኢትዮጵያውያን፡ የቃል ኪዳን ምልክቱን፡ እስከዛሬ ድረስ የሚፈጽሙለትንና "እውነተኞቹ ልጆቹ ነን" ብለው የሚመኩበትን አብርሃምን፡ በአርያነት የሚጠቅሱት፡ ከታች፡ በ፬ኛው ቃል ኪዳን ላይ፡ ተብራርቶ እንደሚገኘው፡ በሃይማኖቱና በምግባሩ እንጂ፡ ኢትዮጵያውያን፡ አክብረውና ጠብቀውት ከኖሩት፡ ከሕገ እግዚአብሔር ውጪ፡ ከአንዲት በላይ፡ ሌሎች ሚስቶችን አግብቶ፡ ከባለቃል ኪዳን ልጁ፡ ከይስሐቅ በቀር፡ ብዙ ልጆችን በወለደባቸው ጋብቻዎቹ አይደለም።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዘመነ አበው፡ በኪዳነ ልቦና፥ በዘመነ ኦሪት ደግሞ፡ በኪዳነ ሙሴ፡ ያን በመሰለ መልክ፡ አክብረውና ጠብቀው ያቆዩትን፡ ይህን፡ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉትን፡ የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት የጋብቻ ቃል ኪዳን፡ ማለትም፡ ኹለቱ፡ በጋብቻ ትዳር የሚኖሩትን ሕይወታቸውን፡ በዘመነ ምሕረት ደግሞ፡ ለፍጹም ቅድስና አብቅተውታል። ይኸውም፡ እነርሱም፥ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን ደርሰው፡ ለሥርዓተ ተክሊል የሚዘጋጁት፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውም፡ ጋብቻቸውን የሚፈጽሙት፡ ራሳቸውን በንስሓ አጥርተውና አጽድቀው፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም በመቀበል በመኾኑ ነው።

ይህን ሃይማኖታዊ ምግባር ሲፈጽሙ፡ ፈጣሪያቸው፡ ሰው እስከመኾን ተዋርዶ፡ ከማሕፀን ጀምሮ እስከሞቱ ድረስ፡ በማንም ፍጡሩ ላይ ያልደረሱ፥ ወደፊትም የማይደርሱ ፈተናዎችንና መከራዎችን፡ ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ጋር ተቀብሎ፡ በመስቀል ላይ የተሠዋው፡ ለማንና ለምን እንደኾነ አውቀው ነው። ያን ኹሉ ውርደት የተቀበለው፥ መከራውንና ሥቃዩን የታገሠው፥ በዚያም መሥዋዕትነቱ፡ ጠላቶቻቸውን ኹሉ ድል ያደረገው፡ ለእነርሱ ሲል መኾኑን ተረድተው ነው።

በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተመሠረተችውን ሃይማኖታቸውን፡ እንዲህ፡ በምግባር አጽንተው፡ የተቀበሉት ቅዱስ ቁርባን፡ በብቸኝነት ኑሮአቸውም ኾነ በጋብቻ ትዳራቸው ውስጥ፡ በሥጋቸውም፥ በነፍሳቸውም፡ የሚሠሩትን ኃጢአት የሚያስተሠርይ ኃይል፥ በዚህ ምክንያት የሚያድርባቸውን ደዌ የሚፈውስ መድኃኒት፥ ለተረከቡት ምድራዊና ዘለዓለማዊ መልካም ሕይወትም፡ አስተማማኝ የኾነውን ዋስትና የሚያረጋግጥላቸው ማኅተም ይኾናቸዋል። ከዚህ የተነሣ፡ የጋብቻ ትዳራቸው፡ ከሰይጣን ግዛት፥ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ፍዳ ነጻ ኾኖ፡ ሥጋትና ጭንቀት፥ ፍርሃትና ጥርጣሬ፥ ኃዘንና ትካዜ ተወግደው፡ እውነትና ሰላም፥ ፍቅርና ጤንነት፥ ብልጽግናና ደስታ የሰፈኑበት ይኾንላቸዋል።

ዳሩ ግን፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ ወደመልካሟ የገነት ሕይወት ተመልሰው ገብተው የሚኖሩባትን ይህችን፡ የቸሩ እግዚአብሔርን መለኮታዊ ጸጋ ለማሳጣት፡ ከላይ፡ "እባብ" ተብሎ፡ ስሙ የተጠቀሰው፡ ዲያብሎስ፡ ያለ የሌለ ኃይሉን ይዞ፡ በኢትዮጵያውያን ላይ መዝመቱን፡ እነሆ፡ እንመለከታለን። ይኸውም፡ በመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ላይ እንዳደረገው ኹሉ፡ ይህንኑ፡ እግዚአብሔር የመሠረተውን፡ የጋብቻን አቋም ለማፍረስ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ሲያካኼድ የኖረውን እኩይ ጥረቱን፡ ዛሬም፡ በበለጠ አጠናክሮ እየቀጠለበት የሚታየው የሠመረው ዝግጅቱና የተሟላው ድርጅቱ ነው።

## የጋብቻ አለመከበር ጠንቅ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፡ በየቦታው ተብራርቶ እንደሚገኘው፡ የዲያብሎስ የተንኰል ዓላማ፡ እንዲሣካ "አስችለዋል" በሚያሰኙ ልዩ ልዩ ግዙፋንና ረቂቃን ስልቶች ምክንያት፡ ጋብቻን በሚመለከት፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያውያን፡ በሴቶቹም፥ በወንዶቹም ላይ እየደረሰ ያለው ፈተና፡ እጅግ የተወሳሰበና የበረታ መኾኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ይኸውም፡ የጋብቻ ሥርዓት ተከብሮ፡ እየጸና በመኼድ ፋንታ፡ ተንቆ እየተዳከመ መቀጠሉ ነው። ይህ ኹኔታ፡ የዝሙትና የአመንዝራነት ኃጢአት እየነገሠ መኼዱን ያመለክታል። ዝሙት፡ ከጋብቻ ወጪ የሚፈጸም የወንድና የሴት ሩካቤ ሥጋ ሲኾን፡ አመንዝራነት ግን፡ ያለውን ጋብቻ ማፍረስ፥ በሌላ የፈረሰ ጋብቻም መተካት፥ እንዲሁም፡ ማናቸውንም፡ ሃይማኖትንና አምልኮን ጨምሮ፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ የኾነውን ቃል ኪዳን፡ በወረትም ኾነ በተመሳሳይ መልክ ማፍረስና መለዋወጥ ነው።

ይህን የመሰለው ኃጢአት፡ በዚህ መልክ መስፋቱ ደግሞ፡ በኖኅ ዘመን በነበሩት፥ ከዚያም በኋላ፡ በሰዶምና በገሞራ፥ በመጨረሻ፡ እስከቅርቦቹ ዘመናት ድረስ በኖሩት ዓለማውያን ሰዎች ላይ ደርሶ የታየው፡ አሳዛኝ ፍጻሜ፡ አሁንም፡ የዚህ ትውልድ ጽዋ መኾኑ እንደማይቀር፡ አንዳንድ ምልክቶች እየታዩ ነው። አሳዛኙ ፍጻሜ ከመድረሱ በፊት፡ የመፈራረሱና የአወዳደቁ ኹኔታ፡ ደረጃውን ጠብቆና ተከትሎ የሚካኼደው ግን፡ በመጀመሪያ፡ በቤተሰብ፥ ቀጥሎ፡ በኅብረተሰብ፥ ከዚያ በኋላ ደግሞ፡ በአገር፥ በመጨረሻ፡ በዓለም ላይ መኾኑ ተደጋግሞ ታይቷል። ይህን ለመሰለው ጥፋት፡ የተከፈለው ዋጋም፡ በቅድሚያ፡ በሚያጥለቀልቅ የውኃ ማዕበል መስጠም ሲኾን፥ ተያይዞም፡ በእሳት ገሞራ ተቃጥሎ መደምሰስንና የመሳሰሉትንም የቅጣት መቅሠፍቶችን በማስከተል መኾኑን፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ መዝግበው ይናገሩታል፤ የሃይማኖት ሕዝቦችም ኹሉ፡ ይህን ያውቁታል።

በአሁኑ ጊዜ፡ የጋብቻ ውድቀትና የዝሙት መስፋፋት፡ ጠንቁ፡ እያደገና እየተጠናከረ ማኼዱ፡ አሌ ሊባል አይቻልም። ከዚህ የተነሣ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ ምድር በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ ሳይቀር፡ እየደረሰ ያለውን፡ AIDS (ዔይድስ = Acquired Immuno-Deficiency Syndrome)፡ ማለትም፡ "*ተፈጥሮአዊ መከላከያ እጦት ጠንቅ*" (ተመእቅ) ወይም HIV (ኤችአይቪ = Human Immunodeficiency Virus)፡ ማለትም፡ "*ሰብአዊ ሓጻጼኃይል ተውሳክ*" (ሰሓተ) የሚል ስያሜ የሰጡትን፥ ጥንትም፡ የቅጣት መሣሪያ ኾኖ ያገለገለውንና ለሕዝብ ጤናማ ህልውና፡ አንዱ፡ ጠንቀኛ ምክንያት የኾነውን፡ የደዌ መቅሠፍት አስከትሎ ይገኛል።

የዚህ ኹሉ መሠረታዊ መንሥኤ፡ ሌላ ሳይኾን፡ ያው፡ በሥጋ ፍትወት ተሠውሮ ገብቶ፡ ለሞት የሚዳርገውን፡ የተለመደ የኃጢአት መርዙን ለማቅመስ፡ ዕቅዱም፥ ጥበቡም ያለው ዲያብሎስ ነው! ለዚህ የጥፋት ዓላማው አፈጻጸም፡ ዓለማውያን መሪዎችንና ባለሥልጣኖችን ብቻ ሳይኾን፡ ከዚያ አልፎ፡ "*የተመረጡትን እንኳ እስኪያስት ድረስ*" እንደተባለው፡ "የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች ነን" ብለው፡ ሥልጣነ ክህነትን፡ በቃል ኪዳን ከተቀበሉት መካከል ሳይቀር፡ መሣሪያዎች፤ አድርጎ፡ ተግባሩን የማከናወን ችሎታን እንዳገኘ፡ እነሆ፡ ኹሉም፡ በገሃድ ያየዋል።

እባቡ ዲያብሎስ: የልብ ልብ አግኝቶ: ይህን: አፍራሽ ዓላማውን: እንዲህ: ከግብ ሊያደርስ የበቃው: የመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን: የፈጣሪያቸውን የሕይወት ሕግ በማፍረስ: ለሞት ፍርድ የሚያበቃውን ኃጢአት እንዲሠሩ÷ የእርሱ: የዲያብሎስ ተገዦችና ባሮች እንዲኾኑም ለማድረግ የተጠቀመበትን ብልሃት: በዛሬዎቹ አዳምና ሔዋን ኢትዮጵያውያን ላይ: በተቃራኒ መልኩና ቃላቱ ለመፈጸም በመቻሉ ነው::

እግዚአብሔር አምላክ: ለመጀመሪያዎቹ: አዳምና ሔዋን ያቀረበላቸው: የሕይወት ትእዛዝ: *"ሌላውን ፍሬ ኹሉ ብሉ! ነገር ግን: እንዳትሞቱ: በገነት መካከል ከሚገኘው ዛፍ ብቻ አትብሉ!"* የሚል ሲኾን: ዲያብሎስ ደግሞ: የሐሰት መርዙን: በአስመሳይ ጣፋጭ ቃላት ሸፍኖ: "የለም÷ አትሞቱምና: በገነት መካከል ከሚገኘው: ከዚያ ዛፍ ብሉ!" ብሎ: የፈጣሪያቸውን ፈቃድ በድፍረት አስፈርሶ: ከገነት እንዳስወጣቸውና ለሞት ፍርድ እንዳበቃቸው በይፋ ይታወቃል::

ይኸው የእግዚአብሔር ተቃዋሚ÷ የሰው ልጆች ባላጋራና የከፋት አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ: በአሁኑ ጊዜ: በተለይ: እንደካህናተ ጣዖት: የእርሱ ሉሌዎቹ አድርጎ በመደባቸው ወገኖች አማካይነት: ለዛሬዎቹ አዳምና ሔዋን ኢትዮጵያውያን: የሚላቸውን ደግሞ: እስቲ በማስተዋል እንመልከት! ይኸውም: ለመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን: ያችን የሕይወት መመሪያ የሰጠው: ያው: እግዚአብሔር ቃል: በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ: "ለዘለዓለም ሕያዋን ኾናችሁ ትኖሩ ዘንድ: የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነው: ሥጋዬና ደሜ ይኸውላችሁ! እርሱን ብሉ! ጠጡ!" ሲል: በአዋጅ ላስተላለፈው የግብዣ ጥሪ: ዲያብሎስ: በተቃዋሚነት የሰጠው ምላሽ ነው::

ዲያብሎስ: በዚህ የተቃውሞ ምላሹ: ይህን: "ኑ! ቁረቡ!" የሚለውን: መለኮታዊ የግብዣ ጥሪ: በመቃረንና የቀድሞ ስልቱን በመቀየር: "የለም: አትምጡ! አትቁረቡ!" በሚለው: ሰይጣናዊ አዋጁ ሊቋቋመው እንደቻለ: ይኸው ይታያል:: "ሰይጣናዊው አዋጅ: መለኮታዊዉን ጥሪ: እንዴት ሊቋቋመው ቻለ?" ለሚለው ጥያቄ: መልሱ: አጭርና ቀላል ነው፤ እርሱም: "ዲያብሎስ: ሰይጣናዊ አዋጁን: በተግባር ላይ እንዲውል የሚያደርጉለት: ሥውር አገልጋዮች ስላሉት ብቻ ነው" በሚል ቃል ይጠቃለላል::

አዎን! የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውን በሃይማኖታዊ ሥርዓት ፈጽመውና ራሳቸውን: ለሥጋ ወደሙ አብቅተው: መልካሙን የእግዚአብሔርን ትዳርና ቤተሰብ ለመመሥረት ለተዘጋጁ ባልና ሚስት ሳይቀር: ዲያብሎስ: በእኒያ አገልጋዮቹ አማካይነት: ለቤተ ሕዝቡ: በሥውርም÷ በገሃድም የሚነግራቸው ቃል: የኢየሱስ ክርስቶስን: የሕይወት ጥሪ "አትቀበሉ!" በሚለው ቁርጥ ውሳኔው ነው:: ከዚያ ውሳኔው ጋር የሚያስተላልፍላቸውም መልእክት: ያን: መለኮታዊ ጥሪ መቀበል: ራሳቸውን: ለእሥረኛነትና ለጭንቀት ኑሮ መዳረግ መኾኑን በማስታወቅ÷ በማስጠንቀቅና በማስፈራራት ስለኾነ: በምንም መንገድ የሚያፈናፍን አይደለም:: አሳቹ ጠላት: በዚህ መልእክቱ: "'እንቁረብ!' ማለትን ትታችሁ: ዝም ብላችሁ: አርፋችሁ ተቀመጡ! በዚህ ዕድሜአችሁ: ሥጋ ወደሙ የምትቀበሉት ለምንድር ነው? ምን አስቸኮላችሁ? ኋላ: ስታረጁ ትደርሱበት የለ!? 'አሁን ካልተቀበልን!' ብላችሁ: ብትቆርቡ ግን: ዛሬ: በሥጋችሁ ትቀሠፋላችሁ! ኋላ ደግሞ: በነፍሳችሁ: ወደገሃነመ እሳት ትወርዳላችሁ!" እያለ: እነሆ÷ ክርስቶስ በደሙ የዋጃቸውን: የቃል ኪዳን ሕዝቡን: ዲያብሎስ: የራሱ ጭፍሮችና የገሃነም ልጆች ለማድረግ: በብርቱ እየጣረ መኾኑ በግልጽ ይታያል::

እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ግን፡ ይህን ኹሉ የጠላት ተቃውሞ በመቋቋም፡ የመሪያቸውን የግብዣ ጥሪ ተቀብለው፡ ኃጢአታቸውን ዘወትር በንስሓ እያጠሩና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበሉ፡ የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውን ሕያው በማድረግ፡ የቤተሰብ ሕይወታቸውን እያለመልሙ ይኖራሉ፡፡ የቅዱሱን ኪዳን የጋብቻ ቃል ኪዳን ባለማክበር የተነሣ፡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ተስፋፍቶ የሚገኘው (የAIDS ዔይድስ) መቅሠፍታዊ ደዌ ሊወገድ የሚችለው፡ በንስሓና የጋብቻን ቃል ኪዳን በማክበር ብቻ መኾኑንም ያምናሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው የተሰጣቸውን፡ ይህን፡ የጋብቻን ሥርዓት አክብረውና ቃል ኪዳኑንም ጠብቀው በመኖር፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ ነጻ ሕዝብ ኾነው፡ በግል፥ በቤተሰብና በአገር ደረጃ፡ እስከዛሬ ያሳለፉትን የህልውና ዘመናቸውን የሚያስሉት፡ የሰው ፍጥረት መነሻ ከኾነው፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምረው ነው፡፡ በዚህ መሠረት፡ የዘራቸውን ትውልድ የሚቆጥሩት፥ የማንነታቸውንም ዜና የሚያሰሙት፡ በቀጥታ የሰው ልጆች፡ የመጀመሪያ ወላጆች ከኾኑት፡ ከግንዶቹና ከምንጮቹ፡ ከአዳምና ሔዋን ተነሥተው ነው፡፡ እግዚአብሔር፡ ለአዳምና ሔዋን የሰጠው፡ የመጀመሪያው ቃል ኪዳን የተደረገውም፡ ከኤዶም ገነት ፈልቀው፡ ከጤግሮስና ከኤፍራጥስ አንጻር በሚፈስሱት፡ ዛሬ[1] "ጥቁር ዓባይ" እና "ነጭ ዓባይ" በሚባሉት፡ በፊሰንና በግዮን ወንዞች ለምልማና ተከብባ በምትገኘው፡ በምድረ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ መኾኑን እያበሠሩ ይናገራሉ፡፡

የሰዓት፥ የቀንና የሳምንት፥ የወርና የዓመት፡ በጠቅላላ የዘመን አቆጣጠራቸው ስልትና ስሌት፥ ስያሜዎቹ ጭምር፡ የመጀመሪያውን ቃል ኪዳን፡ መሠረታዊ ማዕከል ያደረገውን፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊዉን ሥርዓት፡ አሟልቶ የተከተለ ኾኖ ይገኛል፡፡ ይህ አርእስተ ነገር፡ የዘመን አቆጣጠርን በሚመለከተው፡ በዚህ መጽሐፋዊ ክፍል፡ ዝርዝር ሐተታ ተሰጥቶበታልና፡ እዚያ ላይ መመልከት ነው፡፡

"ታዲያ፥ እኔስ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"

## ኹለተኛው ቃል ኪዳን፤
## ኪዳነ ኖኅ፡፡

እግዚአብሔር፡ ፍጥረቱን፡ ዳግመኛ በውኃ ሙላት ፈጽሞ ላያጠፋ ዋስትና የሰጠበት፡ ኹለተኛው ቃል ኪዳኑ፡ ከኖኅ ጋር ያደረገው ነው፤ ዘለዓለማዊ ምልክቱም፡ በዚህ ዓለም፡ "ቀስተ ደመና" ኾኖ ይታያል፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ህልውናቸው ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፡ የቀስተ ደመናውን ምልክት በሚያዩበት ጊዜ ኹሉ፡ ፈጣሪያቸው፡ በመካከላቸው ለመገኘቱ፡ አንዱ ግዙፍ መተማመኛቸው ሲኾን፡ ይኸው የቃል ኪዳኑ መለኮታዊ ምልክት፡ ምንጊዜም፡ በሃይማኖት ተጠብቆና ተከብሮ በሚገኝበት፡ በልባቸው ጽላት ላይ የታተመ መኾኑ ደግሞ፡ ሌላው መንፈሳዊ ማረጋገጫቸው ኾኖ ኖርዋል፡፡

አዎን! እኒሁ ኢትዮጵያውያን፡ በአፍአዊዉ ዓይነ ሥጋቸውና በውሳጣዊው ዓይነ ሕሊናቸው፡ ዘወትር፡ ወደዚሁ፡ ወደቀስተ ደመናው ምልክት አተኵረው የሚመለከቱት፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም:: ይህም ምክንያት:- አንደኛ፡ ከእርሱ፡ ከአንድ አምላካቸው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ የቃል ኪዳን ስምምነት ያላቸው መኾኑን፥ ኹለተኛ፡ ያ ቃል ኪዳን፡ መለኮታዊ መከላከያ ኾኖ፡ ከጠላት አጥቂነት የሚጠብቃቸው መኾኑን፥ ሦስተኛ፡ የተፈጥሮ መቅሠፍትም ኾነ ሰብአዊ ክፋት በሚያመጣቸው የጥፋት ኃይላት ከሚደርሰው ጠቅላላ እልቂት የሚተርፉበት ረቂቅ መጠለያቸው፡ ያ ቃል ኪዳን መኾኑን በማረጋገጥ፡ "ቀስተ ደመናው፡ የደኅንነት መተማመኛችን፥ ዘለዓለማዊ ዋስትናችንና አማናዊ ምስክራችን ነው" ለማለት ይመለከቱታል::

የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሕፃን ወላጆች፡ በተለይ በአዲሱ ኪዳን፡ ዘመነ ምሕረት፡ ልጃቸው፡ ቀስተ ደመናውን፡ "የማርያም መቀነት" እያለ እንዲጠራ ያስተምሩታል:: ከዚህ ትውፊት የተነሣ፡ "ኢትዮጵያ"፡ ድንግል ማርያም መኾኗን በማረጋገጥ፥ የቀስተ ደመናውም ምልክት፡ በእርሷ የሰውነት አካልና ሕይወት፡ ዘለዓለማዊ ህልውናን እንደተቀዳጀ በማመን፡ "ኢትዮጵያ"፡ በኢትዮጵያውያን የአእምሮና የብራና ሰሌዳ ላይ፡ ሰብአዊ ባሕርይና ሕያው አካል ያላትን፡ "ድንግል ማርያምን" ኾና ተሥላ፡ የምትኖር ኾናለች:: በዚህም፡ የሰው ዘር ተደምስሶ ከመጥፋት፡ በእርግጥ ለመዳኑና የዘለዓለማዊ ምሕረትን ፍጹም ዋስትና ለመቀዳጀቱ፡ ቅድስቲቱ የአምላክ እናት፡ በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አማናዊት ምክንያትና ሕያውት ምልክት መኾኗ ተረጋግጧል::

በኋላ ዘመን፡ ለሕዝብ ማንነት መታወቂያና ለአገር ምንነት መለያ የሚኾን ብሔራዊ ምልክት አዘጋጅቶ ማውጣት፡ አስፈላጊ የኾነበት ጊዜ ሲደርስ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህንኑ፡ የቀስተ ደመና፡ መለኮታዊና ኪዳናዊ ምልክት የሚተካ ሌላ ሰው-ሠራሽ ሰንደቅ ዓላማ መፈልሰፍ አላስፈለጋቸውም:: ከዚህ ይልቅ፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፡ የቀስተ ደመናው፡ መደበኛና አጠቃላይ፥ ዓበይትና ደማቅ የኾኑትን፡ ማለትም፡ አረንጓዴን፥ ብጫንና ቀይን፡ እነዚህን ሦስት ኅብረ ቀለማት የያዘ ኾኖ እንዲዘጋጅ በመወሰን፡ ያው፡ የመለኮታዊው ቃል ኪዳን ምልክት የኾነው ቀስተ ደመና እንዲጸና አደረጉ! በዚህም ውሳኔያቸው፡ በፈጣሪያቸው በእግዚአብሔር ላይ የኖረው እምነታቸውና አምልኳቸው፡ በራሳቸው ዘንድ፡ በበለጠ ሊጠናከር፥ በዓለሙም ዘንድ፡ በይፋ ሊታወቅ ችሏል:: እኒያ የቀደሙት ኢትዮጵያውያን፡ በዚህ መልክ ተስማምተው ያዘጋጁትን፡ ይህን ሰንደቅ ዓላማ፡ ብሔራዊ አርማቸውና ሕዝባዊ ምልክታቸው አድርገውት፥ ተከታታዩም ትውልድ፡ በየዘመናቱ፡ ይህንኑ እያጸደቀው፡ ሳይለወጥ፡ እነሆ ከዛሬው ቀን ደርሷል::

## የሰንደቅ ዓላማው ምሥጢር::

በሰንደቅ ዓላማነቱ፡ አንድ፥ በኅብረ ቀለማቱ ግን፡ ሦስት የኾነው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊና ሕዝባዊ አርማ፡ በዚህ አንድነቱና ሦስትነቱ፡ የቀስተ ደመናው ብቻ ሳይኾን፡ የሌሎች በርካታ ዕፁብ ድንቅ ምሥጢራት፡ ምሳሌያዊ መገለጫ ምልክት ኾኖ ኖርዋል::

ከእነዚህ ምሥጢራት መካከል: ፩ኛ. የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት (አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ)፥ ፪ኛ. የሰው አንድነትና ሦስትነት (ነፍስ፥ሥጋ፥ መንፈስ)፥ ፫ኛ. የቤተሰብ አንድነትና ሦስትነት (አባት፥ እናት፥ ልጅ)፥ ፬ኛ. የሃይማኖት አንድነትና የምግባር ሦስትነት (ጾም፥ ጸሎት፥ ምጽዋት)፥ ፭ኛ. የኢትዮጵያዊው ዘር አንድነትና ሦስትነት (ካማዊ፥ ሴማዊ፥ ያፌታዊ)፥ ፮ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት አንድነትና ሦስትነት (ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነት፥ ቤተ ምልክና)፥ ፯ኛ. የቅዱሱ ኪዳን አንድነትና ሦስትነት (ኪዳነ ልቦና፥ ኪዳነ አሪት፥ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ) ይገኙባቸዋል::

ከዚህ በቀር: አረንጓዴ መስክ መስሎ የሚታየው: የሰንደቅ ዓላማው ላይኛው ክፍል: የኢትዮጵያን የተትረፈረፈ የተፈጥሮ ጸጋና ልምላሜ ያመለክታል፤ መካከለኛው ክፍል ደግሞ: እንደከበረውና በእሳት ቀልጦ እንደጠራው እንደወርቁ ድንጋይ: ብጫውን ቀለም ይዞ: በጽኑ የመከራ ነበልባል የተፈተነውን: የኢትዮጵያን: የሃይማኖቷን ጥራት ያስረዳል፤ ከታች ያለው: በጽጌ·ረዳ ቅላት የተሸፈነውም ክፍል: የደም መሥዋዕትነት የተከፈለበትን: የኢትዮጵያን ነጻነትና ብሔራዊ ህልውና: አጉልቶ ያሳያል::

እንደምሥጢረ ሥላሴ ኹሉ: ከኅብረ ቀለማቱ የተነሣ: ሦስትነት ያለው: ይህ ሰንደቅ ዓላማ: አንድ መኾኑ: የሦስቱ የኖኅ ልጆች ዘር ተዋህዶ: አንድ ከኾነበት: ከግንዱ ከመልከ ጼዴቅ የወረደው: ኢትዮጵያዊው ሰውነት: ሦስቱ ነገዶች ተዋህደው: አንድ የኾኑበት አካል ለመኾኑ ምልክት ነው::

የዚህ: የኹለተኛው ቃል ኪዳን ዓቢይ ቁም ነገር: ፍሬያማ በኾነ መንገድ: በበለጠ ሊጠናከርና ሊለመልም ችሏል:: ይኸውም: እግዚአብሔር: በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነትና ጉልላትነት ለሠራው ኢትዮጵያዊነት: ግንድ ከኾነው ከመልከ ጼዴቅ ጋር ባደረገው: በሦስተኛው ቃል ኪዳን ነው:: እርሱም: ቀጥሎ ባለው ክፍል: ሰፋ ባለ ሐተታ ተብራርቶ ቀርቧል::

"ታዲያ፥ እኔስ: በኢትዮጵያዊነቴ: ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"

## ሦስተኛው ቃል ኪዳን፤<br>ኪዳነ መልከ ጼዴቅ::

እግዚአብሔር: ከመልከ ጼዴቅ ጋር ያደረገው: የሦስተኛው ቃል ኪዳን ምልክት: የኅብስትና ጽዋ ቁርባን ነው::

ይህን ቃል ኪዳን: ኢትዮጵያውያን: የግል ወይም የቤተሰብ፥ የማኅበር ወይም የሃይማኖት በዓሎቻቸውን ምክንያት በማድረግ: "ጠበል ጠዲቅ": ማለትም: "ጸበለ መልከ ጼዴቅ": "የመልከ ጼዴቅ በረከት" እያሉ: በሚያቀርቡት መብል መጠጥ: እነሆ: ሕያው አድርገውት ይኖራሉ:: ይህንኑም ዝግጅት: በጥልቅ ሃይማኖታዊ ስሜት ኾነው: በጸሎት ሥርዓት: ይፈጽሙታል::

በዚያ ስብሰባ ላይ የተገኘው እያንዳንዱ ሰው: ከዚያ አንድ ኅብስትና አንድ ጽዋ: ድርሻውን ይሳተፋል:: ይህ አድራጎት: ልዩ ምክንያት ባለው: በእያንዳንዱ ማኅበራዊ ስብሰባ ላይ ተሳታፊዎች የኾኑት ኹሉ: በእውነት አንድ መኾናቸውንና ስብሰባው በሚመለከተው ግለሰብ፥ ቤተሰብ ወይም ኅብረተሰብ ላይ ሊደርስ በሚችለው: በማናቸውም ዓይነት ዕድል ውስጥ ተካፋይ ለመኾን ያላቸውን ቁርጠኛነት ለማሳየት የሚፈጸም ሥርዓት ነው::

እግዚአብሔር፡ ይህን፡ ሦስተኛውን ቃል ኪዳኑን፡ እውን አድርጎ ሊፈጽምበት የመረጠው ሰው፡ የግእዝ ስሙ፡ "የእውነት ንጉሥ" ወይም "እውነተኛው ንጉሥ" ተብሎ የሚተረጐመው፡ መልከ ጼዴቅ ነበር።

## ይህ ኪዳን፡ ለ"ኢትዮጵያዊነት" ግንድ ስለመኾኑ።

ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ምሳሌውና ጥላው ኾኖ በቅድሚያ የተገለጸው፥ እንዲሁም፡ የሴም፥ የካምና የያፌት ትውልዶች ከተዋሃዱበት፡ ከሦሉሱ ዘር በመብቀል፡ የኖኅን ግንድ መልሶ አስገኝቶ፡ አንድ ካደረገው ማሕፀን የተወለደው፡ ይኸው መልከ ጼዴቅ፡ በምድር ላይ ለተመሠረተችውና ሦስቱን አብያት፡ ማለትም፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን ይዛ ለምትገኘው፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሕያው ማደሪያ፥ አካላዊ መገለጫና አማናዊ ምልክት ኾኖ ሲታይ እንደኖረ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት መዝግበውት ይናገራሉ።

ይኸውም፡ ፩ኛ፦ የእግዚአብሔር፡ የቃል ኪዳን ወገን ለመኾን ለሚያበቃው፡ ለኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ የዘር ግንድ በመኾን፡ የቤተ ሕዝብን፥ ፪ኛ፦ "የልዑል እግዚአብሔር ካህን" በሚል ማዕርግ ተሠይሞ፡ የቤተ ክህነትን፥ ፫ኛም፦ "እውነተኛው የሳሌም (የሰላም/ የኢየሩሳሌም) ንጉሥ" ተብሎ በመቀባት፡ የቤተ ምልክናን ባለመብትነትና ባለቤትነት፡ ባጠቃላይ፡ ለሰው ልጆች ኹሉ፥ በተለይም፡ ቃል ኪዳኑን አምነው ለተቀበሉት ኢትዮጵያውያን ለማቀዳጀት የሚያበቃውን ጸጋ ያስገኘ፡ ይኸው መልከ ጼዴቅ መኾኑን እያረጋገጡ ያበሥራሉ። "ሳሌም"፡ የሚለው፡ የግእዙ፡ የቃል ለቃል ትርጉም፡ "ሰላም" ማለት ሲኾን[፴፱]፡ "ኢየሩሳሌም" ወይም፡ "ሀገረ ሰላም" የሚለው ስያሜ፡ ከዚያ ተገኝቷል።

ከመልከ ጼዴቅ ዘመን አንሥቶ፡ በኢየሩሳሌም ከተማ ታውቆና ጸንቶ የኖረው፡ የኢትዮጵያውያን ህልውና፥ እንዲሁም፡ የትውልድ ግንዶቻቸው የኾኑት፡ አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩባት፡ የኢትዮጵያ ምድር፡ በኖኅ መርከብ የተጀመረው፡ ወደኢየሩሳሌም የሚያደርጉት ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ እስከአሁን ድረስ ሳይቋረጥ እንደቀጠለ፡ እነሆ ይታያል። የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን፡ በግልና በማኅበር የሚፈጽሙት፡ ይህን የመሰለው የምእመናን ጉዞ፡ እየጨመረና እየተጠናከረ ማደጉን፡ ከሦስት ፲ታመታት በፊት ጥቂቶች ኢትዮጵያውያን፥ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ጭምር፡ በመተባበር ያቋቋሙትና እየሠራ የሚገኘው፡ "የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት"፡ ለዚህ ሕያው ትውፊት (ቋሚ ባህል)፡ አንዱ ማስረጃ ነው።

የዚህን እውነታ ጥንታዊነት በበለጠ ለማረጋገጥ፡ ገናና ስማቸው፡ እንደደማቅ ከዋክብት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሲያበራ የሚኖረውንና ለኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት፡ አንጸባራቂ አርአያነት ያላቸውን፡ ኹለት ባለዝናዎች፡ እዚህ ላይ ማንሣት ተገቢ ይኾናል። እነርሱም፡ የዘመነ ብሉይ ኪዳኗ፡ የሳባ ወይም የዓዜብ ንግሥት የተባለችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ማክዳ እና የዘመነ አዲስ ኪዳኑ፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ አቤሜሌክ ናቸው። እኒህ፡ ኹለት፡ ስመ ጥሩ ኢትዮጵያውያን፡ መለኮታዊው ዕቅድ በእነርሱ እንዲፈጸም፡ ራሳቸውን በፍጹም ፈቃደኛነት ያቀረቡ ከመኾናቸው ጋር፡ በኖሩባቸው የተለያዩ ዘመናት፡ የኦሪቱና የክርስትናው[፵] እምነቶች፡ በእነርሱ ጽኑ ድልድይነት፡ ወደኢትዮጵያ እንዲገቡ አድርገዋል።

ኢትዮጵያውያን፡ ዘመን ከማይወሳበት ጊዜ አንሥቶ፡ የልባቸው ሥር ስለኾነችው፡ ስለኢየሩሳሌም ከተማ ያላቸው፡ የጠበቀ መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍቅር፡ የጎላና የፈካ መኾኑን፡ የእነዚህ፡ የኹለት ሰዎች፡ የዜና መዋዕል ተጨባጭ ድርጊቶች አጉልተው ከማሳየታቸው ጋር፡ ለኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸው፡ ግንድ ከኾነው፡ ከመልከ ጼዴቅ የተነሣ፡ "ኢየሩሳሌም፡ ብሔረ ሙላዳችን (የልደት ቦታችን) ናት" የሚለውን እምነታቸውንም ያጸኑታል። የዚህ እምነታቸው አማናዊነት፡ *"የእግዚአብሔር ከተማ [ኢየሩሳሌም ] ሆይ! እርሱ ስላንቺ ያደረገው ነገር ዕፁብ ድንቅ ነው፤ ፍልስጥኤምና ጢሮስ፥ የኢትዮጵያም ሕዝብ፡ በዚያ ተወለዱ!"* ባለው፡ በመዝሙረ ዳዊት ቃል ተረጋግጧል።[፺፩]

## የኢትዮጵያዊነት ምሥጢር።

ከላይ እንደተጠቀሰው፡ እግዚአብሔር፡ በሦስተኛው ቃል ኪዳኑ አማካይነት፡ የመንግሥቱ ሦስት አብያት (አካላት)፡ ማለትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ በመልከ ጼዴቅ ሰውነት፡ ሠርፀውና ገዝፈው፡ በሕያውነት እንዲገለጹ አደረገ።

ይህ መልከ ጼዴቅ፡ በመለኮታዊው ጸጋና ሢመት፡ የተቀዳጀው የክብር ማዕርግ፡ የቱን ያህል ታላቅ መኾኑ፡ ገሃድ በኾነው አምላካዊ ድርጊት ተመስክሩዋል፤ ይኸውም፡ ለዕብራውያን የትውልድ አባትና ለይሁድና ሃይማኖት ግንድ የኾነውን፥ የሚቀጥለውንም መለኮታዊ ቃል ኪዳን፡ ከፈጣሪው ጋር ለመፈጸም የተጠራውን፡ አብርሃምን የሚያህል ሰው ለመባረክ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዙ ነው።

ምሳሌው ኾኖ ቀድሞት እንደተገለጸው፡ እንደመልከ ጼዴቅ ኹሉ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች፡ ከካም፥ ከሴምና ከያፌት ዘሮች ውህደት ስለተወለደ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝባዊነቱን፥ ካህንነቱንና ንጉሥነቱን በማሳየት፡ ራሱ፡ ዘለዓለማዊውና ፍጹሙ ኢትዮጵያዊ መኾኑን፡ አረጋግጧል።

ይህን መለኮታዊ እውነት፡ ወንጌላውያኑ፡ ማቴዎስና ሉቃስ፡ በየራሳቸው የምሥራች መልእክቶቻቸው ውስጥ በመዘገቡት በዮሴፍ የትውልድ ሐረግ አቀራረባቸው ላይ ጠቁመው እንዳመለከቱት ይታያል። ይኸውም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የሰውነትን ፍጹም ባሕርያት፡ በተዋህዶ የወረሰበት፡ እውነተኛው የትውልድ ሐረግ፡ በድንግል ማርያም በኩል ያለው ብቻ መኾኑን እያወቁ፡ ይህንኑ፡ በዝርዝር ተንትነው በመጻፍ ፋንታ፡ ይህን ትተው፡ በዮሴፍ ወገን ብቻ የተወሰኑበት፡ አንዳች ምክንያት መኖሩ፡ ግልጽ ነው። አዎን! በድንግል ማርያም በኩል ያለውን ገልጸው ቢኾን ኖሮ፡ ወንጌሉን በጻፉላቸው፥ በተለይም አይሁድ ወይም ዕብራውያን በተባሉት ወገኖች ዘንድ፡ መልእክቶቻቸው፡ ተቀባይነትን ማግኘት ሳይኾን፡ ወዲያው ብርቱ ተቃውሞን ሊያስነሡባቸው እንደሚችሉ በመፍራት፡ ከዚህ ችግር ለመዳን ሲሉ የደረጉት መኾኑ ይታመናል።[፺፪]

ወደዕብራውያን የተላከውን ደብዳቤ የጻፈው ሐዋርያ፡ በዚህ መልእክቱ ውስጥ፡ ስለመልከ ጼዴቅ ማንነት በማስረዳት፡ በሰጠው የትርጓሜው ሐተታ፡ ይህንኑ እምነት፡ በበለጠ አብራርቶታል።

ይኸውም: *"አባትና እናት+ የትውልድም ቁጥር የሉትም፤ ለዘመኑ: ጥንት+ ለሕይወቱም: ፍጻሜ የለውም:: ዳሩ ግን: በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሉ: ለዘለዓለም ካህን ኾኖ ይኖራል!"* በሚለው ቃሉ ነው::[፺፫]

መልከ ጼዴቅ የተባለው: ይህ ሰው: የቅዱሱ ኪዳን ሕዝባዊ ወገን ከመኾኑ ጋር: የልዑል እግዚአብሔር ካህንና የሰላም ንጉሥ ኾኖ: በእነዚህ አምላካውያት ማዕርጋት አማካይነት: በተጨባጭ የያዛቸውን የብፅዕና በትረ ሥልጣናት: በተግባር ላይ እያዋለ: በሰብአዊ አካልና በምድራዊው ዓለም: መልአካዊ ሕይወትን: በግዘፍ የኖረ መኾኑ እየታወቀ: በሐዋርያው መልእክት ውስጥ: ያን የመሰለ ምሥጢራዊና ምትሓታዊ የኾነ ገጽታ የተሰጠው: ያለበቂ መነሻ አይደለም:: ለዚህ አገላለጽና አቀራረብ መሠረታዊ ምክንያት የኾነው: በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ: ስለዚሁ መልከ ጼዴቅ የተጻፈው: ውሱንና አጭር+ በዚህም ነገር ረገድ "ያልተሟላ ነው" የተባለው: እንዲህ የሚለው መጽሓፋዊ ጥቅስ ኾኖ ይገኛል:-

*"የሳሌም ንጉሥ: መልከ ጼዴቅም: የምስጋና ኅብስትን: በመሶብ+ የበረከት ወይንንም: በጽዋ አወጣ፤ እርሱም: የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ:: አብራምንም: "አብራም: ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ: ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፤ ጠላቶችህን: በእጅህ የጣለልህ: ልዑል እግዚአብሔርም የተመሰገነ ነው"* ብሎ ባረከው::[፺፬]

ከኹሉ ይልቅ: በዘመኑ ፍጻሜ: የምሳሌው ባለቤት የኾነው: አማናዊውና ዘላለማዊው መልከ ጼዴቅ: ኢየሱስ ክርስቶስ: በቅድስት እናቱ በድንግል ማርያም የዘር ሓረግ: የተገለጸበት ሰብአዊ ማንነቱ: የዚያን የቀዳማዊውን መልከ ጼዴቅ ማንነት አረጋግጦ ሊያመለክትና ሊያሳውቅ ችሏል:: በመጨረሻ: የመልከ ጼዴቅም+ የኢየሱስ ክርስቶስም: የኹለቱም ተመሳሳይ ማንነት: በዚያ: በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሰውነት ተከሥቷል::

ያ: ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ: ስለክርስቶስ የዘር ሓረግና ማንነት: በነቢዩ በኢሳይያስ ለቀረበው: *"ትውልዱንስ ማን ይናገራል?"* ለሚለው: አጠያያቂና የእንቆቅልሽ ትንቢት: ራሱ: አካላዊው መገለጫና ተጨባጩ መልስ መኾኑን በማረጋገጥ: የነቢዩን ቃል: በሃይማኖታዊ ተመስጦ: ከአንደበቱ እንዲያሰማ: መንፈስ ቅዱስ በፈቀደ ጊዜ: ይህ መለኮታዊና ምሥጢራዊ እውነት: በሰብአዊ መልክ: እነሆ ገዝፎ ታየ::[፺፭]

እግዚአብሔር: በመልከ ጼዴቅ ማንነት: ማለትም: ሦስቱንም የኖኅን ልጆች ዘሮች በሙሉ ካዋሃደው ሕያው ሰውነት በመወለድ: ትስብእቱን ሊፈጽም የፈለገበት አንዱ ዓላማ: ለሰብአዊ ፍጡሩ: ፍጹም የኾነውን: የአካልና የባሕርይ ዕርቅና ኅብረት: በእርግጥ መልሶ ሊያጎናጽፈው መኾኑ: ግልጽ ነው:: ይህ ዕርቅና ኅብረት: በነፍስና በመንፈስ ብቻ ሳይኾን: በሥጋ ጭምር በመኾኑ: ከዚህ አምላካዊ ድርጊት የተነሣ: መላው የሰው ዘር: በግለሰብም ኾነ በዓለም-አቀፍ ደረጃ: ባለው የዓቅም አድማስ: ምኞቱንና ፍላጎቱን አሟልቶ ሊያረካ ከቻለበት ብቅዓት ለመድረሱ: አያጠራጥርም::

የእግዚአብሔር ልጅ: የአብርሃም ዘርና የይሁዳው አንበሳ+ የዳዊትም ልጅ መኾኑን በማስረዳት: ሰብአዊ ማንነቱን: በአስተማማኝ መልክ ለማሳየት: ይህን እውነታ: ከላይ እንደተመለከተው: ወንጌላዊው ማቴዎስ: የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሓረግ በዘረዘረበት መዝገብ ውስጥ ገልጸ አረጋግጦታል::

# ኢትዮጵያ፡

ቅዱስ ማቴዎስ፡ ይህን ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሲል በጻፈው፡ በዚሁ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ፡ ከሴማውያኑ አበው ጋር፡ የእነሣራን፥ ርብቃን፥ ራሔልንና ልያን የመሰሉትን፡ የሴማውያኑን እናቶች ስም ሳይኾን፡ ከካምና ከያፌት ዘሮች የተወለዱትን፡ የእነትዕማርን፥ ራኬብን፥ ሩትንና ቤትሳባን (ቤተ ሳባን) የመሰሉትን፡ በርኵሰትና በነውር፥ በኃጢአትና በአሕዛብነት ተንቀው የተጣሉትን፡ የእነዚህን እናቶች ስሞች ብቻ፡ ደፍሮ በመጥቀሱ፡ ስለእግዚአብሔር እውነት፡ ያለፍርሃት ለመግለጽ ያለውን ቆራጥነት አሳይቷል፡፡

እንግዴህ፡ እግዚአብሔር፡ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች የዘር ውህደት፡ በተገኘው ሥጋ፥ ይኸውም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ መልክ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው በኾነበት፡ በዚህ መለኮታዊ ሥራው አማካይነት፡ የዘረኝነት መርገምና የከፋቱ ጠንቅ የኾኑትን፡ ጥላቻንና ትምክህተኝነትን፥ ዕብሪትንም፡ ለአንደኛውና ለመቼውም ጊዜ፡ ጨርሶ አስወገደ! ፍቅርንና ስምምነትንም፡ በአጠቃላይ፡ በሦስቱ ነገዶች፥ በእያንዳንዳቸውም መካከል መልሶ በመመሥረት፡ ኹሉንም አስታረቀ!

የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ምክንያት በማድረግ፡ ሰብአ ሰገል የተባሉት፡ ሦስቱ ጠበብት፡ እያንዳንዳቸው፡ የሴምን፥ የካምንና የያፌትን ትውልዶች በመወከል፡ ከየአህጉራቸው ወጥተው፡ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ፡ በዚያ፡ ሦስቱም ወገኖች፡ በትንቢቱ መሠረት፡ ተገናኝተው፡ ተልእኳቸውን መፈጸማቸው፡ መለኮታዊው ዕቅድ፡ በደረጃው፡ ከብቅዓት ለመድረሱ፡ አንድ ምስክር ኾኗል፡፡ ከመካከላቸው፡ አንዳቸውም ኢትዮጵያዊ ያልኾኑት፡ እኒያ ሦስት የጥበብ ሰዎች፡ በየበኩላቸው፡ አያሌ ወራት የፈጀባቸውን፡ ረዥም መንገድ የተጓዙት፡ በቤተ ልሔም አውራጃ፡ በበረት ለተወለደው ለሕፃኑ ኢየሱስ፡ የተገባውን፡ የአምልኮ ስግደትን፥ የፈቃድ ተገዢነትንና የፍቅር ገጸ በረከትን ለማቅረብ እንደነበረ ይታወቃል፡፡

ይህም የኾነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነትና በእናቱ ድንግል ማርያም ንግሥትነት፡ በመላው የሴማውያን፥ የካማውያንና የያፌታውያን ነገዶች ላይ፡ በነፍስም፥ በሥጋም፥ በመንፈስም ለሰፈነችውና በአዲስ ኪዳን ጸንታ ለተገለጸችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ተገቢውን እውቅና ለመስጠት ነበር፡፡ በዚህ መልክ፡ እውቅናን ያገኘችው፡ የዚች መለኮታዊት መንግሥት ምስፍናም፡ ሥሩ፡ ከአቤል ምትክ፡ ከእሴት ወገን ሠርፆ፡ ወደእግዚአብሔር ልጆች ቅሬት፡ ወደኖኅ ከደረሰ በኋላ፡ በመልከ ጼዴቅ ሰውነት፡ አንድ ዘር ለመኾን እንደገና በተዋሃዱት፡ በሦስቱም የሰው ትውልድ ዘርፎች ላይ ኾነ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ሦስቱ የጥበብ ሰዎች ከተባሉት ሰብአ ሰገል መካከል እንዳልነበሩ፡ ከላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ ነገር፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሰብአ ሰገል እንዳደረጉት ሳይኾን፡ ለሕፃኑ ኢየሱስ፡ ገጸ በረከትን ከማቅረብ ነጻ መኾናቸውን ያመለክታል፡፡ ለዚህ እውነት፡ አንደኛውና የቅርቡ ማረጋገጫ፡ ከህልውናቸው ዘመን አንሥተው፡ እግዚአብሔርን፡ አምላካችን፥ ንጉሣችንም "ነው!" ብለው፡ ሲያመልኩት መኖራቸው ነው፡፡ ይህንኑም፡ እርሱን የሚጠሩበት፡ ይኸው ስያሜያቸው፡ ራሱ፡ በቂና ሕያው ማስረጃቸው ኾኖ ይመሰክርላቸዋል፡፡ በግእዝ ቋንቋቸው፡ "እግዚአብሔር"፡ የአንድነቱ፥ "እግዚእ፥ አብ፥ ሔር"፡ ጌታ ወልድ፡ ከሩኅሩኅ አብና ከቸር መንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው፡ የሦስትነቱ ስም ሲኾን፡ "እግዚአ - ብሔር" ሲል ደግሞ፡ "የአገሪቱና የሕዝቡ አምላክና ንጉሥ" ማለት መኾኑን ያስገነዝባል፡፡

አዎን! ሰብአ ሰገል፡ ለአራሱ መሢሕ ሕፃንና ለዘለዓለማዊው ንጉሥ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለንግሥት እናቱም፡ ያላቸውን የመገዛት ፈቃደኛነትና የመታመን ጽናት ለማሳየት፡ ለአዲሶቹ መሪዎቻቸው፡ በገሃድና በሥርዓት፡ እንዳቀረቡት ያለ፡ የግብር ወርቅንና የመታያ ስጦታን ይዘው መቅረብ፡ ለኢትዮጵያውያን አላስፈለጋቸውም። እነርሱ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎችና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ በመኾናቸው፡ ለዚህ ማዕርግ ከበቁበት፡ ከልዩው የባለመብትነት ክብራቸው የተነሣ፡ በቤተ ልሔም በረት መገኘት አላስፈለጋቸውም።

ይህ ኹሉ የኾነው፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገሩት፡ የነቢያት ትንቢት ደርሰው የተፈጸሙ በመኾናቸው ነው። ከእነዚህም፡- የመጀመሪያው እንዲህ ይላል፡- *“እግዚአብሔር፡ ከዓለም አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው። በምድር መካከል መድኃኒትን አደረገ። 'አንተ ባሕርን፡ በኃይልህ አጸናሃት! አንተ የእባቦችን ራስ፡ በውኃ ውስጥ ሰበርህ! አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ! ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው!'”* ኹለተኛውም፡- *“እግዚአብሔር ሆይ! ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ! ... በፊቱ፡ ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ። ጠላቶቹም፡ አፈር ይልሳሉ። የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት፡ ስጦታን ያመጣሉ። የዓረብና የሳባ ነገሥታት፡ እጅ መንሻን ያቀርባሉ። ነገሥታት ኹሉ ይሰግዱለታል! አሕዛብም ኹሉ ይገዙለታል።”* ይላል።

ከላይ እንደተብራራው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ትስብእቱን፡ በመልከ ጼዴቅ ሰውነትና ማንነት በመፈጸሙ፡ በምድር ላይ የተበተነው መላው የሰው ዘር፡ በየሃይማኖቱ የነበረውን መንፈሳዊ ርእዮት፥ በየነገዱም የነበረውን ሥጋዊ አስተሳሰብ፡ በተጨባጭ ኹኔታና በኹለንተና መልኩ፡ ጨርሶ ከመሠረቱ ለዋውጦታል። አዎን! መለኮትና ትስብእት፡ በአካልም፥ በባሕርይም፡ ተዋህደው፡ አንድ የኾኑበት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፍጹሙ የሰው ልጅና ፍጹሙ የእግዚአብሔር ልጅ በመኾኑ፡ ለኢትዮጵያውያንና ለመላው የክርስቲያኑ ዓለም ብቻ ሳይኾን፡ በጾታ፥ በዘር፥ በሃይማኖትና ወይም በሥነ መንግሥት ፈሊጥ፡ ለተለያየው የሰው ትውልድ ኹሉ፡ ለሕይወቱ፡ በግለሰብ ደረጃ ሳይቀር፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ በአርአያነትና ምሳሌነት፡ ፍጹሙ ገጸ-ባሕርይ ኾነ!

ከዚህ የተነሣ፡ ማናቸውም ግለሰብ፡ በነፍስ ወከፍ፡ ሴትም ኾነች ወንድ፡ በትውልዱ፡ ሙሉ በሙሉ፡ ሴማዊ፥ ካማዊ ወይም ያፌታዊ ቢኾን፥ ወይም በመልኩ ቀይ፥ ጥቁር ወይም ነጭ ቢኾን፥ ወይም በእምነቱና በምግባሩ፡ አረማዊ፥ እስላም፥ ቡዲስት፥ ሒንዱ፥ ይሁዲ፥ ክርስቲያን፥ ባዕለ ንዋይ፥ ኅብረተሰባዊ፥ የጋርዮሽ ኑሮ አማኝ፥ የልቅ ኑሮ አማኝ፥ ወይም ወግ አጥባቂ ቢኾን፡ የእርሱ ወይም የእርሷ የዘር ሓረግ፥ የትውልድ ብሔር፥ የሃይማኖት አቋምና የሥነ መንግሥት ዝንባሌ፡ የተለየ መኾኑ፡ ምንም ዓይነት ተጽዕኖን በማያስከትል ኹኔታ፡ ያ ግለሰብ፡ በአዲሱ ኪዳን ምክንያት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መልክ፡ አዲሱ ሰው ለመኾን፡ በፍጹም ይለወጣል።

ይህ፡ ዕፁብ ድንቅ የኾነ መለኮታዊ ምሥጢር፡ እውን የሚኾነው፡ ያ ግለሰብ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፡ ቃል ኪዳኑን እንደሕፃን ተቀብሎ፡ በሥርዓተ ጥምቀት አማካይነት፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ እንደገና ከእግዚአብሔር የመወለድን ጸጋ በሚቀዳጅበት ጊዜ ነው።

## ኢትዮጵያ:

ከዚች አፍታ ጀምሮ: ያ ግለሰብ: ማናቸውም የሚያደርገው ነገር ኹሉ: የሚታየውና የሚወሰነው: በሰውነቱ የሥጋ ሕዋሳት ብቻ ሳይኾን: በይበልጥ: ከእግዚአብሔር በመወለድ: በለበሰው: በአዲሱ መንፈሳዊ አካሉ ሕዋሳት ይኾናል:: ይህም ማለት: ለእርሱ ወይም ለእርሷ: እንግዲህ ወዲህ: ጥቁር፥ ነጭ ወይም ቀይ የሚባል ሰው የለም፤ ወይም: አረማዊ፥ እስላም፥ ቡዲስት፥ ሒንዱ፥ ይሁዲ፥ ክርስቲያን፥ ባዕለ ንዋይ፥ ኀብረተሰባዊ፥ የጋርዮሽ ኑሮ አማኝ፥ የልቅ ኑሮ አማኝ፥ ወይም ወግ አጥባቂ የሚባልም ነገር: ቦታ አይኖረውም፤ ነገር ግን: ኹሉም፥ እያንዳንዱም: በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ: ወንድም ወይም እህት ይኾንለታል፤ ይኾንላታል ማለት ነው:: አዎን! ያ ግለሰብ: ከዚያች አፍታ ጀምሮ: ከሌላው ከማናቸውም ፍጡር ጋር የሚኖረው ግንኙነት: በየትኛውም ገጽታው ቢኾን: እግዚአብሔር: በኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመውን ፍቅሩን በማሰብ: በመልክ ቀለም፥ በብሔር ማንነት ወይም በሃይማኖት ወገንነት ላይ የተመሠረተ ሳይኾን: ይህን የመሰለውን ልዩነት ተከትሎ በማያይ: አንድ ዓይን ብቻ የሚካሄድ ይኾናል::

በዚህ ጊዜ: በዚሁ: በአንዱ ግለሰብ: ሰብአዊ አካል ላይ: በእውንና በገሃድ የሚከናወነው: ይህ: የዘር ውህደት: በመንፈስ ቅዱስ ግብር: ወደቀደመው አንድነትና ማንነት ተመልሶ: ፍጹም ይኾናል:: ማንኛውም ሰው: "እኔ: በእውነት: ኢትዮጵያዊ ወይም ክርስቲያን ነኝን? ወይስ አይደለሁም?" ብሎ ራሱን የሚመዝንበት፥ የሚያውቅበትና የሚመድብበት: አንደኛው ወሳኝ መሥፈሪያ ይህ ነው::

እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን: የመልከ ጼዴቅ ዘሮች በመኾናቸውና በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ: የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር በመቀዳጀታቸው: ይህ: ዕፁብ ድንቅ የኾነ የመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር: በየግል ሕይወታቸው ላይ እየተፈጸመ ሲያንጸባርቅ፥ ረዥም ዕድሜ ባለው: በብሔራዊ ህልውናቸውም ዜና መዋዕል ሲነገር ኖርዋል:: በነገድ፥ በብሔር፥ በሃይማኖት ወይም እኒህን በመሰሉ የመለያያ ምክንያቶች ከተከፋፈሉት: አያሌና ልዩ ልዩ ከኾኑ ሕዝቦች ጋር የመሠረቱት ግንኙነት የሠመረ ኾኖ የኖረው: አድልዎ የሌለበትን: የተስተካከለ መስተንግዶን: ለኹሉም በማበርከታቸው፥ የራሳቸውን ብቻ ሳይኾን: የሌሎችንም መብት አክብረው በማስከበራቸውና ከማንኛቸውም ሰብአዊ ፍጡር ጋር በመስማማት: አብሮ ለመኖር በመቻላቸው መኾኑን: ይኸው ዜና መዋዕላቸው ያረጋግጣል፤ ይህን: ልምድና ባህል ያገኙት: ከዚሁ: ከመለኮታዊው ጸጋ በመኾኑ: በትክክለኛነቱ ይተማመኑበታል:: በመላው ዓለም በየአህጉሩ በሚኖሩት የሰው ልጆች ኀብረተሰቦች መካከል: በዘር ጥላቻና በሃይማኖት ልዩነት ሰበብ: አሁንም በርክቶና ተስፋፍቶ የሚካኼደውን ጦርነት: እነርሱ: እንኳንስ በገቢር ሊፈጽሙት ቀርቶ: በአእምሮአቸው እንኳ: ሊያስቡት የሚቸግራቸው: በዚህ ረገድ ከወረሱት: ጥልቅ ከኾነው ሃይማኖታዊ አቋማቸው የተነሣ መኾኑን ማወቅ ይገባል::

## የዲያብሎስ ሐሰት መፈራረስ አለበት::

በእያንዳንዱ አገር፥ በተለይም: ራሳቸውን: "ክርስቲያኖች ነን" ብለው በሚጠሩት ዘንድ: ይህን የመሰለው የዘር ጥላቻና የጎሣ ግጭት: በክልል፥ በብሔርና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ሲካኼድ ማየት: የማይጣጣም አሳዛኝ ድርጊት ብቻ ሳይኾን: ግብዝነትንም የሚያመለክት ኾኖ ይገኛል::

እንዲሁም: ራሳቸውን "ክርስቲያን" ብለው በሚጠሩና ክርስቲያኖች ባልኾኑ አንዳንድ ወገኖች ዘንድ እጅግ ሰፍኖ የሚገኘው: በአንድ በኩል: ኢየሱስ ክርስቶስ: ከሴም ወይም ከያፌት ነገድ ብቻ እንደተወለደ በማስመሰል: "የመልኩ ቀለም: ነጭ ነው" የሚለው ይትበሃል፥ በሌላው በኩል ደግሞ: "ክርስትና: የነጩ ሕዝብ፥ እስልምናም: የጥቁሩ ሕዝብ ሃይማኖት ነው" የሚለው አስተሳሰብ: በሃይማኖት ስም: በማናለብኝነትና በድፍረት የሚካኼድ: ገሃድ የኾነ የሐሰትና የማታለል ድርጊት በመኾኑ: ሊጋለጥና ሊታረም ይገባዋል:: የግልና የተንኰል ዓላማን ከግብ ለማድረስ ሲባል: ይህን የመሰለውን የተሳሳተ: የሐሳውያን ይትበሃልንና አስተሳሰብን ፈጥሮ: እንዲህ በሰፊው መንዛት: የዚህ በደል ፈጻሚዎቹን: ለዘለዓለም ኵነኔ የሚዳርገውን: መለኮታዊ ፍርዱን በሚሰጠው: በኃያሉ እግዚአብሔር ላይ: ታላቅ ክህደትን እንደመፈጸም ይቈጠራል::

ድንግል ማርያምንና ኢየሱስ ክርስቶስን: ነጮች እንደኾኑ አድርገው: ባዕዳን የሚሥሉትን ሥዕል: በተለይ ኢትዮጵያውያን: "ምስለ ፍቁር ወልዳ" ብለው: በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገለገሉበት መኾኑ: እጅግ ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም፤ ስለዚህ: ይህ ከባድ ስሕተት: ሊታረም ይገባዋል::

እዚህ ላይ: ይህን በሚመለከት: ሊወሳ የሚገባው: አንድ ቁም ነገር አለ:: ይኸውም: በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት: ለሰው ዘር ስለተገኘው: የዘለዓለም ትድግና: የተነገረው: የተስፋው መፈጸምና የምሥራቹ (የወንጌል) መልእክት: ከነጩም ኾነ ከጥቁሩ ሕዝብ ጆሮ ከመድረሱ: ከአያሌ ሺህ ዓመታት በፊት፥ ወይም: ኹለቱም ወገኖች ወይም ከኹለት አንዳቸው: የክርስትናውም ኾነ: የእስልምናው ሃይማኖት መኖሩን እንኳ ከመስማታቸው: ከብዙ ምዕት ዓመታት አስቀድሞ: ኹሉን በፈጠረ: አንድ አምላክ አምኖ: እርሱን ብቻ የማምለክ ሥርዓት: ማለትም: አምልኮተ እግዚአብሔር: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ከመጀመሪያው የአዳምና ሔዋን ቃል ኪዳን አንሥቶ: ጸንቶ መኖሩ: በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ መታወቁ ነው::

አዎን! "የደቡቧ ወይም የሳባዋ" የሚል መታወቂያ ቅጽል የተሰጣት: ኢትዮጵያዊቷ ንግሥታቸው ማከዳ: የኢትዮጵያዊነትን ቅዱስ ዓላማ: ለፍሬ ለማብቃት: ባላት ቀናዒነት: ማለትም ለፈጣሪዋ: ለእግዚአብሔር ባላት ፍቅር ተነሣሥታ: ወደኢየሩሳሌም ያደረገችውን: ገናና የኾነውን: የተቀደሰ ጉዞዋን እስከፈጸመችበትና በእርሷ ምክንያት: የአሪቱ እምነት: ወደኢትዮጵያ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ: በዚህ: "አንድ እግዚአብሔር" በሚለው አምልኮ ላይ የተመሠረቱት: የቀደሙት: የብሉዩ ኪዳን: ቃል ኪዳናት: የኢትዮጵያውያን ሃይማኖት መሠረት ኾነው ኖረዋል::

ንግሥት ማከዳ: ወደኢየሩሳሌም ያደረገችው ይህ ምክንያታዊ ጉዞ: በኋለኛው ዘመን: በአዲሱ ኪዳን በጸደቀው: በክርስትና ሃይማኖት መሰላልነት: ለመጨረሻው የዘውድ አክሊል የበቁትን: የሕገ ኦሪትን ቃል ኪዳናት ወደኢትዮጵያ ለማምጣት: በር ከፋች ኾኗል::

ከዚህ በላይ የተወሱትን እውነታዎች መሠረት በማድረግ፥ ለተነሣውም አጠያያቂ ነጥብ፡ መፍትሔ የኾነውን ምላሽ ለማግኘት ያህል፡ ኢትዮጵያውያን፡ የኹለቱም ወገኖች፡ ማለትም፡ የጥቁሩም፥ የነጩም ሕዝቦች ወኪሎች በመኾን፡ ከእስልምና ሃይማኖት መምጣት አስቀድሞ፡ ክርስትናን ተቀብለው በምግባር ላይ አውለውታል ብሎ፡ በማያሻማ ኹኔታ መደምደም፡ አጥጋቢና ተገቢ ይኾናል፡፡

እንግዲህ፡ እስካሁን እንደተብራራውና ወደፊት ባሉትም ገጾች፡ በበለጠ ተስፋፍቶ እንደሚታተተው፡ ለማናቸውም ሰው፡ ራሱን እንዲህ አድርጎ፡ በአዲስ ሰውነት፡ ሊለውጥ የሚያስችለውን፡ ይህን የመሰለውን መንፈሳዊ ኃይል አጎናጽፎ፡ ያ ሰው፡ ከሌላው፡ ከማናቸውም ባዕድ ሰው ጋር፡ የመጨረሻውና ፍጹም የኾነውን ሰላማዊ ግንኙነት ለመመሥረት ከሚበቃበት፡ የአስተሳሰብ ልዕልና የሚያደርሰው ብቸኛ መንገድ፡ የኢትዮጵያዊነት እምነት መኾኑ በይፋ ይታወቅ!

"ታዲያ፥ እኔስ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"

## አራተኛው ቃል ኪዳን፤
## ኪዳነ አብርሃም፡፡

እግዚአብሔር፡ አራተኛውን ቃል ኪዳኑን ያደረገው፡ ከአብርሃም ጋር ሲኾን፡ ይኸው ቃል ኪዳን፡ በዘለዓለማዊነት የቀጠለበት ምልክት፡ ግርዛት ነው፡፡

ግለሰቦችና ወይም ሕዝቦች፡ ከዚህ ቃል ኪዳን የተነሣ የሚያገኙት በረከት የሚታወቅበት መገለጫው፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የመታሰቢያነቱ ቅርስ፡ በአኵስም ሐውልት ሳይቀር ተጠብቆ ከኖረው፡ ከሥጋዊው ግርዛት ይልቅ፡ መንፈሳዊው ገጽታው የበለጠ ከፍተኛ ግምት ያለው መኾኑ በሃይማኖት ተረጋግጧል፡፡

አንድ ግለሰብ፡ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት፡ እውነተኛ መኾኑ ተረጋግጦ የሚታወቀው፡ እጅግ በርካታ በኾኑ መራራ መንገዶች፡ እስከሞት ድረስ ተፈትኖና በትእግሥቱ እስከመጨረሻው ጸንቶ፥ ይህንኑም፡ በበጎ ምግባር እውን አድርጎት ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ይህን የመሰለው ሃይማኖትና ምግባር፡ ያን ግለሰብ ወይም ያን ሕዝብ፡ ለፍጹሙ መንፈሳዊ ማዕርግ ያበቃዋል፡፡ ለዚህም፡ አብርሃም፡ ብቸኛ ምሳሌ ኾኖ፡ ሲወሳና ሲጠቀስ ይኖራል፡፡

በማናቸውም ዓይነት የስምምነት ውል ውስጥ ተካፋይ የኾነው፡ የእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን አባል፡ በስምምነቱ ውል ውስጥ ለተመለከቱት አንቀጾች፡ ተገዢ እንደመኾኑ መጠን፡ አንቀጾቹ የሚጠይቁትን ግዴታዎች ኹሉ እንዲፈጽም ይጠበቅበታል፡፡ ይህን የመሰለውን ዓለም-አቀፍ ሥነ ምግባር በመከተል፥ በተለይም፡ ለዚህ የተቀደሰ ቃል ኪዳን፡ ጥልቅ የኾነ፡ ሃይማኖታዊ አክብሮትን በመስጠት፡ ኢትዮጵያውያንና በዚህ ረገድ፡ እነርሱን የሚመስሏቸው እውነተኞች ክርስቲያኖች ጭምር፡ በአብርሃምና በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ደርሰው የታዩትን፡ እነዚያን የመሰሉትን ፈተናዎች፡ እስከመጨረሻው በመጽናት መቋቋምና መከራዎቹን በፍጹም ትእግሥት መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡

በቀደሙት ዘመናት፡ አልፎ አልፎ ሲደርስ እንደኖረው ኹሉ፡ በአሁኑ ጊዜም፡ ይኸው ኹኔታ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፡ በግለሰብ ሕይወት ኾነ በአገር ህልውና ደረጃ፡ እነሆ፡ ሰፍኖ ሲካኼድ ይታያል። ይኸው ሕዝብ፡ ለአብርሃም ለተሰጠው፡ ለዚህ ቃል ኪዳንና ለቀሩትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ቃል ኪዳናት፡ ያለው ታማኝነት እስከምን ድረስ እንደኾነ፡ ወይም በእነርሱ ላይ የሚፈጽመው ክህደት ይኖር እንደኾነ፥ ደግሞም፡ ፈተናውንና መከራውን፡ በትእግሥት በመቋቋም፡ እስከመጨረሻው ይጸኑ ወይም ይወድቁ እንደኾነ፡ እነሆ ገና እየተመዘኑ ናቸው። "ክርስቲያኑ ዓለም" ተብሎ የሚጠራውንና "የአብርሃም ልጆች ነን፤ በቅዱሳት መጻሕፍት የታወቀውን፡ እግዚአብሔርንም እናመልካለን" ብለው የሚታመኑትን ኹሉ፡ ይኸው ጽዋ እየጠበቃቸው ነው።

## ኢትዮጵያውያን፡
## እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች ስለመኾናቸው።

በ"አንድ እግዚአብሔር" የሚያምን፡ ማናቸውም ግለሰብ፥ በተለይም፡ ኢትዮጵያዊ፡ ለራሱም ኾነ ለሌላው ሰው፥ እንዲሁም፡ ለፈጣሪው፡ "እኔ የአብርሃም ልጅ ነኝ!" ብሎ በሚያስብበት፥ በሚናገርበትና በሚመሰክርበት ጊዜ፡ በብርቱ መጠንቀቅ አለበት። ምክንያቱም፡ "ነኝ!" ላለው፡ ለዚያ ማንነቱ፡ ራሱን፡ በሃይማኖት ብቻ ሳይኾን፡ በምግባር ጭምር ካላበቃ በቀር፡ "ነኝ!" ማለቱ ብቻ፡ ያንን ሰው፡ ለዚያ፡ "ነኝ!" ላለው ማንነቱ፡ ሊያበቃው ስለማይችል ነው።

ይህ እውነታ የማይታበል ትክክል መኾኑን፡ በምሳሌነት የሚጠቀሱት፡ ቀደም ብሎ፡ በመጥምቁ ዮሓንስ፥ በመጨረሻ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ተከታትሎም፡ በሐዋርያው ያዕቆብ፡ የተነገሩት ቃላት ያረጋግጣሉ። መጥምቁ ዮሓንስ፡ *"ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን፡ ብዙዎች፡ ወደጥምቀቱ ሲመጡ ባየ ጊዜ፡ እንዲህ አላቸው፡- "እናንተ የእፉኝት ልጆች! ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዴህ፡ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ! በልባችሁም፡ 'አብርሃም፡ አባት አለን!' እንደምትሉ አይምሰላችሁ! እላችኋለሁና፥ 'እግዚአብሔር፡ ከእነዚህ ድንጋዮች፡ ለአብርሃም፡ ልጆችን ሊያስነሣለት ይችላል!' አሁንስ፡ ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጧል! እንግዴህ፡ መልካም ፍሬ የማያደደርግ ዛፍ ኹሉ ይቆረጣል! ወደእሳትም ይጣላል!""*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ያመኑትን አይሁድ፡ 'እናንተ፡ በቃሌ ብትኖሩ፡ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ! እውነትንም ታውቃላችሁ! እውነትም፡ አርነት (ነጻ) ታወጣችኋለች!' አላቸው። እነርሱም መለሰው፡ 'የአብርሃም ዘር ነን! ለአንድም ሰንኳ፡ ከቶ፡ ባሮች አልኾንም! አንተ፡ "አርነት ትወጣላችሁ!" እንዴት ትላለህ?' አሉት። ጌታችን ኢየሱስም፡- 'እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ! ኃጢአት የሚያደርግ ኹሉ፡ የኃጢአት ባርያ ነው! ባርያም፡ ለዘለዓለም በቤት አይኖርም! ልጁ፡ ለዘለዓለም ይኖራል! እንግዴህ፡ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ፡ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ! የአብርሃም ዘር መኾናችሁንስ አውቃለሁ! ነገር ግን፡ ቃሌ፡ በእናንተ አይኖርምና፡ ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ! እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ! እናንተም ደግሞ፡ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ!' ሲል መለሰላቸው።*

ኢትዮጵያ:

"እነርሱም መልሰው:- 'አባታችንስ: አብርሃም ነው!' አሉት:: ጌታችን ኢየሱስም: 'የአብርሃም ልጆች ብትኾኑ: የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር:: ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት: የነገርኋችሁን ሰው: ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ! አብርሃም: እንዲህ ኣላደረገም! እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ!' ኣላቸው:: እነርሱም: 'እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም፤ አንድ አባት አለን፤ እርሱም: እግዚአብሔር ነው!' አሉት::

"ጌታችን ኢየሱስም:- 'እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከኾነ: በወደዳችሁኝ ነበር! እኔ: ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና! እርሱ ላከኝ እንጂ: ከራሴ አልመጣሁምና! ንግግሬን የማታስተውሉ: ስለምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው:: እናንተ: ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ! የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወድዳላችሁ! እርሱ: ከመጀመሪያ: ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም: በእርሱ ስለሌለች: በእውነት አልቆመም፤ ሐሰትን ሲናገር: ከራሱ ይናገራል:: "ሐሰተኛ፥ የሐሰትም አባት ነውና! እኔ ግን: እውነትን የምናገር ስለኾንሁ: አታምኑኝም:: ...ከእግዚአብሔር የኾነ: የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል! እናንተ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና: ስለዚህ: አትሰሙም! ...እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ! ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር: ለዘለዓለም ሞትን አያይም!' ኣላቸው::

"አይሁድም: 'አብርሃም ስንኳ ሞተ! ነቢያትም ሞቱ! አንተም: :ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር: ለዘለዓለም ሞትን አይቀምስም!: ትላለህ፤ በውኑ: አንተ: ከሞተው: ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያትም: ሞቱ! ራስህን: ማንን ታደርጋለህ?' አሉት:: ጌታችን ኢየሱስም: '...አባታችሁ አብርሃም: ቀኔን ያይ ዘንድ: ሐሤት አደረገ! አየም! ደስም አለው!' ኣላቸው:: አይሁድም: 'ገና: ሃምሣ ዓመት ያልኾነህ: አብርሃምን አይተሃልን?' አሉት:: ጌታችን ኢየሱስም: 'እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ! አብርሃም ሳይወለድ: እኔ አለሁ!' ኣላቸው::"

ሐዋርያው ያዕቆብም: "አንተ: ከንቱ ሰው! ሃይማኖት (እምነት): ከምግባር (ከሥራ) ተለይቶ: የሞተ መኾኑን ልታውቅ ትወድዳለህን? አባታችን አብርሃም: ልጁን ይስሐቅን: በመሠዊያው ላይ ባቀረበው ጊዜ: ሃይማኖቱ: በምግባር የጸደቀ አልነበረምን? ሃይማኖቱን ከምግባሩ ጋር አብሮ ያደርግ እንደነበረ፥ ሃይማኖቱም በምግባር እንደተፈጸመ ትመለከታለህን? ...ከነፍስ የተለየ ሥጋ: የሞተ እንደኾነ: እንዲሁ ደግሞ: ከምግባር የተለየ ሃይማኖት: የሞተ ነው!" ብሎ ጽፏል::[፳፮]

የአብርሃም ሃይማኖትና ምግባር: በእግዚአብሔር ቃል: እንዲህ: አንድ ኾነውና ሠምረው: በግልጽ መታየት አለባቸው:: ስለኪዳነ አብርሃም የታተተው: ይህ አቀራረብና አገላለጽ: ለሌሎቹ ቃል ኪዳናት ኹሉ ሊጸና የሚገባው ነው::

ኢትዮጵያውያን: የቃል ኪዳኑን: ሥጋዊ የግርዛት ምልክት: ወንዶቹም፥ ሴቶቹም: በሰውነታቸው አካል ላይ በማሳየት ብቻ ሳይኾን: መንፈሳዊ ገጽታውንም: በሃይማኖታዊ ኹለንተናው ጠብቀው በመፈጸም የሚኖሩ በመኾናቸው: እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች: እነርሱ መኾናቸውን አረጋግጠዋል::

በቃል ኪዳኑ ላይ ያላቸው እምነት: የቱን ያህል የጠነከረ መኾኑን ለማመልከት፥ የሴቶቹም የእኩልነት መብት: ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ: የተከበረ ኾኖ የኖረ መኾኑን ለማሳየት: የቃል ኪዳኑን በረከት: ወንዶች ብቻ ሳይኾኑ: ሴቶቹም ጭምር መካፈል አለባቸው በሚል የፍትሕ አስተሳሰብ: ግርዛቱ: በወንዶቹ ብቻ ሳይኾን: በሴቶቹም አካል ላይ እንዲፈጸም ሲያደርጉ ኖረዋል::

እዚህ ላይ: ይህንኑ: ግርዛቱን በሚመለከት: ሊጠቀስና ሊታወቅ የሚገባው: አንድ ቁም ነገር አለ! ይኸውም: የግርዛቱ ምልክት: በሴቶቹም አካል ላይ ይፈጸማል ሲባል: አገራረዙ: አረማውያንና አሕዛብ፥ ወይም አንዳንድ: ከክርስትና ውጭ የኾኑ ሃይማኖቶች: "በሴቶቻቸው ላይ በሚያደርጉት አሠቃቂ መልክ: ይፈጸማል" ማለት አለመኾኑን ነው:: የግርዛቱ ሥርዓት የሚፈጸመው: ልክ: በወንዱ በኩል እንደሚደረገው: ማለትም: "ሸለፈት" የሚባለው: የአባለ ዘሩን ጫፍ የሚሸፍነው ትርፍ ሥጋ: በግርዛት እንደሚወገድ ኹሉ: በሴትም በኩል: በግርዛት የሚወገደው: እንደወንዱ ሸለፈት: አፈ ማኅፀኗን ለመሸፈን: ተጨማሪ ኾኖ የተፈጠረውን፥ ምንም ጉዳት የማያስከትለውንና የማያስፈልገውን ትርፍ ሥጋ መኾኑ: በግልጽ ሊታወቅ ይገባል:: ግርዛት: በመንፈሳዊ ገጽታው በኩል: በቃል ኪዳን ምልክትነቱ: ለነፍስ ህልውና: ጤናማ ሕይወትን የሚያጐናፅፍ ሲኾን: በሥጋዊ ገጽታው በኩል ደግሞ: ለአካል ንጽሕና: ጤናማ አስተዋጽዖን እንደሚያበረክት ተረጋግጧል::

ከዚህ በቀር: ኢትዮጵያውያን: የአብርሃም ሚስት በነበረችው: በኬጡራ ምክንያት: በቀጥታ በሥጋና ደም ጭምር: ከአብርሃም ጋር የተዛመዱ መኾናቸው ይታወቃል:: ይኸውም: ኬጡራ: የሳባና የሌሎቹ፥ ይልቁንም: የምድያማውያን እናት ስትኾን: የምድያሙ ካህን የተባለውና የልጅ ልጇ ተወላጅ የኾነው ዮቶር የወለዳት ሲጳራ የተባለችው ልጁ: "የሙሴ ኢትዮጵያዊት ሚስት" ተብላ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ፶፰ በመጠቀሷ: ኢትዮጵያዊነቷ እሙን ኾኖ በመረጋገጡ ነው::

"ታዲያ፥ እኔስ: በኢትዮጵያዊነቴ: ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"

## አምስተኛው ቃል ኪዳን፤
## ኪዳነ ሙሴ::

እግዚአብሔር: በሙሴ አማካይነት: ከእስራኤል ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን: አምስተኛው ሲኾን: የዚህ ቃል ኪዳን ምልክት: አሥሩ ትእዛዛት የተቀረጸባቸውን: "ጽላት" የተባሉትን ኹለቱን ገበታዎች የያዘው: "ታቦት" የተባለው ነው:: ("ጽሌ" የግእዝ ቃል ሲኾን: ትርጉሙ: በኢትዮጵያኛ: "ገበታ" ወይም "ሰሌዳ" ማለት ነው፤ ለኹለት ሲኾን: "ጽላት" ይባላል፤ "ታቦት": ጽላቱ የሚቀመጥበት "ሣጥን" ማለት ነው::)

የእግዚአብሔር ቃል: በግዙፍ አካል ላይ ተቀርጾ: በምድርና በሕዝቡ መካከል: ያለማቋረጥ የሚገኝ መኾኑ: ለመጀመሪያ ጊዜ የተረጋገጠው: በዚህ ቃል ኪዳን አማካይነት ነበር:: ሕዝቡ: እግዚአብሔር አምላካቸውን: እርሱን ብቻ እንዲያመልኩት የገቡትን: የቃል ኪዳን ግዴታቸውን: በበኩላቸው አክብረውና ፈጽመው ከተገኙ: ለእነርሱ የሚኾነውን ኹሉ ለማድረግ: በታቦቱ ላይ ያደረው መለኮታዊው ኃይልና በረከት: ወሰን አልነበረውም::

እስራኤል ግን፡ ይህን ቃል ኪዳን፡ በተከታታይ ለማፍረስ ታጥቀው በመነሣት፡ በራሳቸው ላይ ጽኑ ጥፋትን ሊያመጣ የሚችል፡ እጅግ አሳዛኝ ድርጊትን መፈጸም፡ ተግባራቸው አድርገው ተያያዙት፡፡ ከዚህ በደላቸውና ደንዳናነታቸው፡ በንስሓ መመለስን እምቢ ብለው፡ ዓመፃቸውን በቀጠሉ ጊዜም፡ ሊደርስባቸው ስለተዘጋጀው፡ ስለመጨረሻው፡ አሪታዊ የቅጣት መቅሠፍት፡ ተገቢው ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው፡፡ ያም መቅሠፍት፡ ቤተ መቅደሳቸውን ጨምሮ፥ በውስጧና በክልሏ ካለው ሀብትና ንብረት መካከል አንዳችም ነገር ሳያተርፍ፡ የኢየሩሳሌምን ከተማ፡ በሙሉ በመደምሰስ ተፈጸመ፡፡ ከባቢሎኑ ንጉሥ፡ ከናቡከደነጾር ሠራዊት ሠይፍና ጦር የተረፈውም ሕዝብ፡ ለስደትና ለምርኮ ተዳረገ፡፡[፺፱]

ይኹን እንጂ፡ ኢየሩሳሌም የምትጠፋበት፥ ቤተ መቅደሷም የሚፈርስበት፡ የማይቀረው የቅጣት ቀን ከመድረሱ በፊት፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ትንቢታዊ ምልክትነት፡ በእርሱ አካላዊ ቃል፡ ከድንግል ማርያም ሰው መኾን፡ ለፍጻሜ እስከሚበቃባት፡ እስከዚያች የተወሰነች ቅጽበት ድረስ፡ ያችን፡ በምድር ላይ የከበረችና የተቀደሰች ንዋዩ የኾነችውን ታቦት፡ በባለአደራነት ጠብቆ ሊያቆይለት የሚበቃ፥ ስለታማኝነቱ፡ በፊቱ ሞገስን ሊያገኝ የሚችል፡ ሌላ ሕዝብ ይኖር እንደኾነ፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ በዓለም ውስጥ ከሚኖሩ ሕዝቦች መካከል፡ ይሻ ጀመር፡፡ እነሆም፡ ለዚህ፡ ታላቅና ዘለዓለማዊ ባለአደራነት፡ ኢትዮጵያውያንን፡ ፍጹም ተስማሚዎችና ብቁዎች ኾነው አገኛቸው፡፡

በዚህ ጊዜ፡ *"'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?" ይላል እግዚአብሔር"* ሲል፡ ጌታ፡ በነቢዩ በአሞጽ አንደበት የተናገረው ቃሉ፡ በግብር ተተርጉሞ የታወቀ ኾነ![፻]

ስለዚህ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ የሳባ ወይም የደቡብ ንግሥት በሚል ቅጽል የምትታወቀውን፡ ኢትዮጵያዊቷን ንግሥት ማክዳን፡ እግዚአብሔር፡ መንፈሷን አነሣስቶ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝና ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን ጋር እንድትገናኝ አደረገ፡፡

ይህን ሃይማኖታዊ ጉዞ ያደረገችው፡ ንግሥት ማክዳ፡ በዚያን ጊዜ፡ ከሕዝቧ ጋር ታመልከው የነበረው አምላክ፡ ያው የአባቶቿና የእናቶቿ፡ የአዳምና ሔዋን፥ የኖህና የቤተሰቡ፥ የመልከ ጼዴቅና የወገኖቹ፥ የአብርሃምና የሣራ፥ የዮቶርና የልጆቹ፥ የሙሴና የኢትዮጵያዊት ሚስቱ፥ የዳዊትና የቤትሳባ አምላክ የኾነው፡ እርሱ እግዚአብሔር ስለነበረ፡ ይኸው አምላኳ፡ ጉዞዋ የሠመረ እንዲኾን በማድረግ፡ የኢትዮጵያዊነትን የተቀደሰ ዓላማ፡ ከታቀደለት መለኮታዊ ግቡ ታደርስ ዘንድ፡ የተመረጠችበትን መሣሪያነቷን፡ ለመልካሙ ፍሬ እንድታበቃ አስቻላት፡፡

ይህን፡ የንግሥት ማክዳንና የንጉሥ ሰሎሞንን ግንኙነት፡ ከአገራዊው፥ ከሀልውና ዜና መዋዕላቸውና ከሃይማኖታዊው አቋማቸው አግጣጫ ሲመለከቱት፡ በኢትዮጵያና በእስራኤል፡ በኹለቱም ላይ ያስከተለው ለውጥ፡ መሠረታዊ እንደነበረ፡ በውጤቱ ተረጋግጧል፡፡ መለኮታዊውን ዕቅድ ተከትሎ ከተፈጸመው፡ ከዚህ ድርጊት የተነሣ፡ ለእስራኤል የነበረው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን በረከት ኹሉ፡ ወደኢትዮጵያ ተላለፈ! ለእስራኤላውያን ተሰጥቶ የነበረውም የአምላክ ጸጋ፡ ለኢትዮጵያውያን ኾነ!

ይህ እውነታ፡ ገሃድ የኾነው፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ፡ የዳዊትን ዘር፡ ከዘውድ ዙፋኑ ጋር፥ ታቦተ ጽዮንን፡ ከመላው ንዋያተ ቅድሳቷና በረከቷ ጋር፥ የሕገ አሪትን እምነት፡ ከትምህርቱና ከአምልኮቱ ሥርዓታት ጋር፥ ቅዱሳት መጻሕፍቱን፡ ከመምህራኑና ሊቃውንቱ ጋር፥ እንዲሁም፡ እንደእስራኤላውያን ልማድ፡ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ከተባሉት ኹለት ዘርፎች መካከል፡ በብኵርናቸው የተመለመሉትንና በብቍዕነታቸው የተመረጡትን እስራኤላውያንን ጨምረው ያጠቃለሉት፡ የኋለኞቹ ቅዱሳት ቃል ኪዳናት፡ በሙሉ፡ ከኢየሩሳሌም ወደኢትዮጵያ ፈልሰው፡ የመጨረሻ ማረፊያቸውና መጠለያቸው፡ ይህችው ኢትዮጵያ እንድትኾን፥ ባለአደራዎቻቸውም፡ ኢትዮጵያውያን እንዲኾኑ፥ በፍጻሜውም፡ ኹሉም፡ ወደኢትዮጵያዊነት ተለውጠው፡ ለከፍተኛው ማዕርግ እንዲበቁ በማድረጉ ነው።

የማይታመን ቢመስልም፡ እነዚህ እውን ኹኔታዎች፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ መሠረታዊ ለውጥ ሳይታይባቸው፡ እንደጥንቱ የቆዩና በሙሉ ተጠብቀው የኖሩ፥ ዛሬም እንኳ ቢኾን፡ እንደዚያው እንዳሉ፡ ሕያዋን ኾነው የሚገኙ ናቸው። የቃል ኪዳኑን ታቦት፡ ለአምልኮቱ ማዕከላዊ ምልክት ያደረገው፡ የሕገ አሪቱ እምነት፡ በዚህ መልክ፡ ወደኢትዮጵያ በመግባቱ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በአዳምና ሔዋን በተመሠረተው፡ በኪዳነ ልቦና አስፍነው ያኖሩትን፡ የ"አንድ አምላክ" ሃይማኖታቸውንና በተከታታዮቹ ቃል ኪዳናት፡ እየጸና የቀጠለውን፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር ምግባራዊ ሥርዓታቸውን፡ እንዲያድግ፥ ከዚህ የተነሣም፡ መንፈሳዊ ልዕልናቸው በጋለ የቅንዓት ኃይል፡ የበለጠ ተጠናክሮ፡ ወደሚቀጥለው ደረጃ ከፍ እንዲል አድርጎታል።

ይህ እንደመኾኑ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት ተገልጾ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ለኢትዮጵያውያን ሕይወት፡ በሃይማኖት፥ በባህልና በማኅበራዊ ኑሮአቸው ብቻ ሳይኾን፡ በህብት ልማት ተግባራቸው፥ በመንግሥታዊ አቋማቸው፥ አመራራቸውና አስተዳደራቸው፥ በብሔራዊ ማንነት መታወቂያቸውም ረገድ፡ እንደድርና ማግ ለተሣሰረው ህልውናቸው፡ የማይነጥፍ፡ ጽኑ የተስፋ ምንጭና የማያረጅ፡ ጠንካራ የአንድነት ማሠሪያ ኾኖ ኖርዋል።

## የጽላትና የታቦት ምሥጢር።

ቀድሞውንም ቢኾን፡ አሥሩን ቃላት የያዘችውን ጽላት ያስገኘው፡ የእስራኤላውያን ክህደትና ዓመፅ ሲኾን፡ ኋላ፡ ወደኢትዮጵያ እንድትመጣ ያደረገው ደግሞ፡ የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጽናትና የማይጠረጠር ታማኝነታቸው መኾኑን፡ ኹለቱም ሕዝቦች፡ በየህልውናቸው በኩል፡ በገሃድ ያሳዩት ምግባር፡ በግልጽ ያረጋግጣል። ይህም፡ ከዚህ በሚከተለው አጭር ሐተታ ሊጠቃለል ይችላል።

አሥሩን ቃላት የያዘችው ዘለዓለማዊት ሕግ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች፡ በእውነትና በመንፈስ፡ የተጻፈችው እኮ፡ ገና አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ ነው! የተጻፈችውም፡ በአሪቱ ጊዜ እንደኾነው፡ በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይኾን፡ "ሕሊና" በተባለው፡ በረቂቁ ሰብአዊ የልብ ጽላት ላይ ነው!

አመሠራረቷ እንዲህ እንደመኾኑ፡ የሃይማኖት አምልኮቷና የምግባር ሥርዓቷ እንዲሁ፡ በእውነትና በመንፈስ ይፈጸም ዘንድ፡ መለኮታዊ ባሕርይዋ ይጠይቃል። ኪዳነ ልቦና ያሰኛት ቅሉ፡ ይህ ነው!

ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በሰዎች ልቦና ላይ በእውነትና በመንፈስ ተጽፋ የምትኖረውን ይህችን፡ አሥሩን ቃላት የያዘችውን ሕግ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ጽላተ ሙሴ ወደኢትዮጵያ ከመምጣቷ፡ ገና ከረዥም ዘመን በፊት፡ አስቀድመው፡ በኪዳነ ልቦና ጠብቀውና አጽንተው፡ በእውነትና በመንፈስ እየፈጸሟት ኖረዋል። ይህም ይታወቅ ዘንድ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ እየኖሩ በሚገኙበት፡ በአሁኑ የክርስትና ሕይወታቸው እንኳ፡ ከአሥሩ ቃላት መካከል፡ አንዷ የኾነችውንና ጥንት፡ በሥነ ፍጥረት የተሠራችውን፡ ሰባተኛዋን፡ የእግዚአብሔርን የሰንበት ቀን፡ "ቀዳሚት ሰንበት" ወይም ወይም "ቅዳሜ" ብለው በመሠየም፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" ከኾነችው፡ ከዕለተ እሑድ፡ ዝቅ ባለ፡ መለስተኛ ደረጃ፡ ዛሬም እነሆ፡ እያከበሩዋት ይገኛሉ።

"የመጀመሪያዋ ሰንበት"፡ ከኹለተኛዋና ከዘላለማዊቷ "ሰንበተ ክርስቲያን" በፊት፡ አስቀድማ የነበረች መኾኗን ለመግለጽ፡ "ቀዳሚት ሰንበት" ወይም "ቅዳሜ" የሚለው ስያሜ ያረጋግጣል። እንዲህ አድርጋ፡ ኹለቱን ሰንበታት፡ በየመልካቸውና በየማዕርጋቸው የምታከብረው፡ ኢትዮጵያ ብቻ በመኾኗ፡ በዓለም ላይ ካሉ ሃይማኖቶችና አብያተ ክርስቲያናት መካከል፡ እርሷ ለያዘችው ቀዳሚነት፡ አንዱ ማስረጃ፡ ይህ መኾኑን ማስተዋል ይገባል።

ኋላ፡ እግዚአብሔር፡ ታቦተ ጽዮንን፡ ከእስራኤላውያን እጅ አውጥቶ፡ በባለአደራነት፡ ለእነርሱ፡ ለኢትዮጵያውያን እንድትሰጥ ያደረገው፡ አንዱም፡ በዚሁ፡ በኪዳነ ልቦና ይፈጽሙት በነበረው፡ ንጹሕ አምልኮታቸው ምክንያት መኾኑ፡ ሊታበል ከቶ አይቻልም። ይህም እውነታ፡ ዓለም በተቀበላቸው፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስማቸው በተመዘገበው፡ በመልከ ጼዴቅ፥ በዮቶርና በንግሥተ ሳባ ሃይማኖት፥ አምልኮና ምግባር ተረጋግጦ ይታወቃል።

ቀድሞ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በሰብአዊ ልባቸው ውስጥ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች ተጽፋ ያገኟት፥ ኋላ፡ በኪዳነ አሪት፡ በድንጋዩ ጽላት ላይ ተቀርፃ ያዩዋት፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ ምሕረት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፡ መንፈሳዊ አካላቸውን ተዋህዳ የተመሰጡባት፥ እነርሱም፡ በእውነተኛውና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው ጠብቀው ያኖሩዋት፡ አሥሩን የእግዚአብሔር ቃላት የያዘችው የሕይወት ሕግ ይህች ናት።

*"፩ኛ. እግዚአብሔር አምላክህ፡ እኔ ነኝ!*

*"፪ኛ. ከእኔ በቀር፡ ሌሎች አማልክት አይኹኑልህ! በላይ፡ በሰማይ ካለው፥ በታችም፡ በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች፡ በውኃ ካለው ነገር፡ የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ! አትስገድላቸው! አታምልካቸውምም! በሚጠሉኝ ዘንድ፡ እስከሦስተኛና እስከአራተኛ ትውልድ ድረስ፡ የአባቶችን ኃጢአት፡ በልጆች ላይ የማመጣ፥ ለሚወድዱኝና ትእዛዜን ለሚጠብቁ ግን፡ እስከሺህ ትውልድ ድረስ፡ ምሕረትን የማደርግ፡ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ፡ ቀናተኛ አምላክ ነኝ።*

*"፫ኛ. እግዚአብሔር፡ ስሙን በከንቱ የሚጠራውን፡ ከበደል አያነጻውምና፡ የእግዚአብሔርን፡ የአምላክህን ስም፡ በከንቱ አትጥራ!*

*"፬ኛ. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ! ስድስት ቀን ሥራ! ተግባርህንም ኹሉ አድርግ! ሰባተኛው ቀን ግን፡ ለእግዚአብሔር ለአምላክህ፡ ሰንበት ነው! አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ፡ በእርሱ፡ ምንም ሥራ አትሥሩ! እግዚአብሔር፡ በስድስት ቀን፡ ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ኹሉ ፈጥሮ፡ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና! ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ የሰንበትን ቀን፡ ባርኮታል፤ ቀድሶታልም።*

*"፭ኛ. እግዚአብሔር አምላክህ፡ በሚሰጥህ ምድር፡ ዕድሜህ እንዲረዝም፡ አባትህንና እናትህን አክብር!*

*"፮ኛ. አትግደል!*

*"፯ኛ. አታመንዝር!*

*"፰ኛ. አትስረቅ!*

*"፱ኛ. በሐሰት አትመስክር!*

*"፲ኛ. የሌላ ሰው የኾነውን ሀብት አትመኝ!"*[፺፮]

ከታች ተከታትሎ እንደሚብራራው፡ ሙሴ፡ በኢትዮጵያ ይኖር በነበረበት ጊዜ፡ እነዚህን አሥሩን የእግዚአብሔር ቃላት፡ በኢትዮጵያውያን ሕይወት፡ ሕያዋን ኾነው ሲሠራባቸው ማየቱ ብቻ ሳይኾን፡ ከእነርሱ ተምሮአቸውም ነበርና፡ እግዚአብሔር፡ ኋላ፡ በደብረ ሲና፡ ለእስራኤል፡ በጽላት ጽፎ የሰጣቸውን ሕግ፡ በእርሱ እጅ ማስረከቡ፥ ይህን በመሰለ ሃይማኖትና ምግባር፡ አስቀድሞ በሕገ ልቡና አሟልቶ፡ ያዘጋጀውንም ሙሴን፡ ለዚህ ተልእኮ መምረጡ ሊያስደንቅ ከቶ አይችልም።

በዚህ መሠረት፡ እግዚአብሔር፡ ገና ከመጀመሪያው፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ እንዲያወጣቸው፡ ሙሴን፡ ከኢትዮጵያ ወደፈርዖን በላከው ጊዜ፡ እንደጣዖታትና ባዕዳን አማልክት፡ በሚታይና በሚዳሰስ ነገር መመለክን የማይፈልግ፥ ይህን መሰሉንም አምልኮ የሚጠላው እንጂ የማይወድደው መኾኑን ለማመልከት፡ ማንነቱን፥ የማዳንና የማጥፋት ኃይሉንም ያሳያቸው፡ በእውነትና በመንፈስ ድርጊቶቹ ብቻ ነበር። እነዚህም፡ የሙሴን በትር፡ እባብ አድርጎ፡ እንደገና ወደበትርነቷ ከመመለስ አንሥቶ፡ የእስራኤልን በኵራት አድኖ፡ የፈርዖንን የበኵር ልጅ እስከመግደል የደረሱትን፡ አሥሩን፥ ከዚያም፡ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ በመክፈትና መልሶ በመዝጋት፥ እያከታተለም፡ በምድረ በዳ ያሳያቸውን፡ ሌሎቹን የምሕረትና የመቅሠፍት ተአምራቱን ያጠቃልላል፤ እነዚህን ኹሉ፡ በዓይናቸው ፊትና በየእራሳቸውም ላይ እያካሄደና እየፈጸመ ያሳያቸው፡ ያው፡ በእውነትና በመንፈስ ባሕርዩ ተሠውሮ እንጂ፡ እንደጣዖታትና ባዕዳን አማልክት ገዝፎ በሚታይና በሚዳሰስ የፍጡራን ተግባረ እድ አለመኾኑን በሚበቃ አስተምሩዋቸው ነበር። ይኸውም፡ እርሱ፡ የአባቶቻቸውና የእናቶቻቸው አምላክ፡ በእነርሱ በልጆቻቸው መመለክ የሚፈልገውና የሚወድደው፡ በግብፃውያን ዘንድ ሲያዩ በኖሩት መልክ ሳይኾን፡ ከዚያ፡ ፍጹም በተለየው፡ "በእውነትና በመንፈስ" ብቻ መኾኑን ነው። ይህን፡ እንዲህ ተከናውኖ፡ በቀጥታና በገሃድ፡ ከፈጣሪያቸው ያገኙትን፥ ኋላም፡ በሙሴ አማት፡ በኢትዮጵያዊው ካህን፡ በዮቶር አማካይነት፡ በተግባር ተተርጉሞ የተመለከቱትን ትምህርት፡ በእርግጥ ተቀብለውት እንደኾነ፡ ወዲያውም ሊፈትናቸው፡ ሙሴ፡ ለሱባዔ ጸሎቱ፡ ለጥቂት ቀኖች ቢለያቸው፡ በግብፅ የለመዱትን ጣዖት ሠርተው አመለኩ!

ከህደትና ዓመፅ ብቻ ሳይኾን፡ ርኵሰትም በኾነው፡ በዚህ ድርጊታቸው፡ እርሱን፡ ሙሴንና ወንድሙን አሮንን ቀርቶ፡ ያን ኹሉ የትድግናና የምሕረት ሥራ ያደረገላቸውን፡ እግዚአብሔርን እንኳን አላፈሩም፤ አልፈሩምም።

እስራኤል፡ በተራራው ሥር ኾነው ይፈጽሙ የነበረውን ያን የርኵሰታቸውን ድርጊት ያወቀ እግዚአብሔር፡ በዚያ ሥራቸው አዝኖና ተቆጥቶ፥ "ሕዝቤ" ያሰኘው የነበረውም፡ ያ ኹሉ ፍቅሩ ቀርቶ፡ ለሙሴ ያለውን እንስማ! *"'ከግብፅ ምድር ያወጣኸው ሕዝብህ፡ ኃጢአት ሠርተዋልና፡ ኺድ! ውረድ! ካዘዝኋቸው መንገድ፡ ፈጥነው፡ ፈቀቅ አሉ! ቀልጦ የተሠራ የጥጃ ምስል፡ ለራሳቸው አደረጉ! ሰገዱለትም፤ ሠዉለትም! "እስራኤል ሆይ! እነዚህ፡ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው!" አሉ!' እግዚአብሔርም ሙሴን፡ 'እኔ፡ ይህን ሕዝብ አየሁት፤ እነሆም፡ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አሁንም፡ ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸው፥ እንዳጠፋቸውም፡ ተወኝ! አንተንም፡ ለታላቅ ሕዝብ (መሪ፥ ተጠሪዬ) አደርግሃለሁ!' አለው።*

*"ሙሴም፡ በአምላኩ ፊት ጸለየ፤ አለም፡- 'አቤቱ! በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ፡ ከግብፅ ምድር ባወጣኸው፡ በሕዝብህ ላይ፡ ቍጣህ፡ ስለምን ተቃጠለ? ግብፃውያንስ፡ 'በተራራ መካከል ሊገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው፡ ለክፋት አወጣቸው!' ብለው፡ ስለምን ይናገራሉ? ከመዓትህ ተመለስ! ለሕዝብህም፡ በክፋታቸው ላይ ራራ! 'ዘራችሁን፡ እንደሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ! ይህችንም፡ የተናገርኋትን ምድር ኹሉ፡ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ! ለዘለዓለምም ይወርሷታል!' ብለህ፡ በራስህ የማልህላቸውን፡ ባሪያዎችህን፡ አብርሃምንና ይስሐቅን፥ እስራኤልንም አስብ!' እግዚአብሔርም፡ በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት፡ ራራ!"*[፶፱]

ከዚህ መለኮታዊ ቃል የምናገኘው መልእክት፡ አንደኛ፡ እግዚአብሔር፡ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ምን ያህል አዝኖና ተቆጥቶ፡ ከቃል ኪዳን ሕዝብነት ሊያወጣቸው እስከመቍረጥ እንደደረሰ፥ ኹለተኛ፡ ሙሴን፡ "ለሌላ ሕዝብ መሪና ተጠሪዬ አደርግሃለሁ!" ያለው፡ ያው እንደሚታወቀው፡ ሙሴ ወደኢትዮጵያ መጥቶና ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶ በመኖሩ፥ የኋላ ኋላም፡ ታቦተ ጽዮን፡ ወደኢትዮጵያ ገብታ በመኖርዋ፡ ኹለቱም፡ ለኢትዮጵያውያን እንደሚኾኑ፥ ሦስተኛ፡ ሙሴ ብቻ ሳይኾን፡ እርሱን የሚመስሉት፡ እውነተኞች የእግዚአብሔር ወዳጆችና አገልጋዮች፡ ከእግዚአብሔር እንደሚያማልዱ ነው።

እስራኤል፡ እንደሰው ሳይኾን፡ እንደአምላክነቱ፡ የደከመላቸውን ድካምና የጣረላቸውን ጥረት፡ በሙሉ ከንቱ ያደረጉበት፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ ለአባቶቻቸውና ለእናቶቻቸው፡ ለአብርሃምና ለሣራ፥ ለይስሐቅና ለርብቃ፥ ለያዕቆብና ለራሔል የሰጠውን፡ ያን ቃል ኪዳኑን በማሰብና በባለሟሉ በሙሴ አንደበት የቀረበለትን ምልጃ በመቀበል፡ ቁጣውን በትዕግሥት፥ መቅሠፍቱንም በምሕረት ለወጠላቸው! እንደኢትዮጵያ ልጆቹ ኹሉ፡ በእነርሱም፡ በእስራኤል ልጆች ሰብአዊ ልቦና ላይ፡ "በእውነትና በመንፈስ" እንዲጻፍ ፈልጎትና ደክሞበት የነበረውንም፡ ያን፡ የዐሠርቱ ቃላትን ሕግ፡ በደንጊያ ጽላት ላይ ጽፎ፡ የሚኾንላቸው ከኾነ፡ እንደእነርሱው ፍላጎት፡ በዚያ፡ ጽላቱን በያዘው ታቦት፡ እርሱን ያመልኩት ዘንድ "ስጣቸው!" ብሎ፡ አገልጋዩን፡ ሙሴን አሰናበተው።

ያም፡ እንደሚታወቀው፡ ሳይኾንላቸው ቀርቶ፡ በመጨረሻ፡ ይህችው፡ ታቦተ ሕጉ የኾነችው፡ ጽላተ ሙሴ፡ በመጨረሻ፡ በባለአደራነት ስም፡ ከኢትዮጵያውያን እጅ ገብታ፡ አማናዊው ጽላት፡ ኢየሱስ ክርስቶስና አማናዊቷ ታቦት፡ ድንግል ማርያም፡ በሰውነት እስኪገለጹ ድረስ፡ በኢትዮጵያ፡ "በእውነትና በመንፈስ" ስትመለክ ኖረች።

## የብሉዩ እና የአዲሱ ኪዳናት

## ፡ "ጽላትና ታቦታት"፡ የተለያዩ ስለመኾናቸው።

የብሉዩ ኪዳን ጽላትና የእርሷ ማኅደር የኾነው ታቦቷ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጡበት ምክንያትና ኹኔታ፡ ከላይ በተገለጸው መልክ መኾኑን፡ ኢትዮጵያውያን ኹሉ በትክክል ሊያውቁትና ሊረዱት ይገባል። በአዲስ ኪዳኑ የምሕረት ዘመን ደግሞ፡ ማለትም፡ በክርስትና እምነታቸው፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን፡ የጽላትና የታቦት ሥርዓት፡ በምን ዓይነት መልክ እንደሚፈጽሙት፡ ከዚህ በታች የተብራራ ስለኾነ፡ ይህንኑ፡ በማስተዋል ሊመለከቱት ያስፈልጋቸዋል።

ኢትዮጵያውያን፡ በዘመነ ብሉይም ኾነ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በእነዚህ፡ ጽላቱን በያዙት ታቦታት፡ የሚፈጽሙት አምልኮተ እግዚአብሔር፡ ጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፥ በመካከሉ ደግሞ፡ በኪዳነ ኦሪት፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ ምሕረት፡ ጸንቶ እንደኖረው፡ "በቅዱሱ መንፈስና እውነት" ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ መለኮታዊ ሥርዓት ለየት ብሎ፡ የጣዖት ወይም የባዕድ አምልኮ የሚያስመስለውን፡ ሌላውን አግጣጫ እንዲይዝ በሚደረግበት ጊዜ ግን፡ በራሳቸውና በአገራቸው ላይ የሚያስከትልባቸው የቁጣ መቅሠፍት፡ የቱን ያህል ከባድ እንደኾነ፡ በቀደሙት ዘመናት እየደረሱ ባለፉትና ዛሬም እየወረደ ባለው የጥፋት ማዕበል በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

በኢትዮጵያ፡ የክርስትና እምነት፡ የኪዳነ ኦሪቱን ተክቶ፡ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራትና ሥርዓታት በሥራ ላይ መዋል ሲጀምሩ፡ የእግዚአብሔር አሥሩ ቃላት የተጻፈባቸውን ኹለቱን ጽላት የያዘው፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ የአምልኮ ማዕከላዊ ምልክትነቱ አበቃ። ይህም ማለት፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ለእግዚአብሔር ቃል፡ የቀደመ ምሳሌው፥ ጥላውና አርአያው በመኾን፡ መለኮታዊው ዓላማ፡ ለታቀደለት ግብ እስኪበቃ ድረስ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ፡ አሁን፡ ያ፡ *"በመጀመሪያ፡ ቃል ነበረ፤ ቃልም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም፡ እግዚአብሔር ነበረ።"* የተባለው፡ እርሱ ራሱ፡ አማናዊው እግዚአብሔር ወልድ፡ *"ቃልም፡ ሥጋ ኾነ!"* ባለው መሠረት፡ በድንግል ማርያም ማኅጸን፡ ፍጹም ሰው በኾነ ጊዜ፡ ለቃል[፺] ኪዳኑ ታቦት የተሰጠው ልዩና ውሱን ተልእኮ፡ ከፍጻሜ ደረሰ ማለት ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት መወለድ፡ የቃል ኪዳኑን ታቦት ነገር፡ መለኮታዊ ምሥጢር ከማድረጉ ጋር፡ ስለዚሁ ምሥጢር የተነገሩት፡ የነቢያት ትንቢት ከፍጻሜ መድረሳቸውንም ያረጋግጣል። ከእነዚህም ውስጥ፡ ከጌታ ልደት በኋላ፡ የኪዳኑ ታቦት መገኛየት እንደኾነ፥ ራስዋም፡ የኪዳኑ ታቦት ማን ኾና እንደምትኖር፡ የሚያመለክቱት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች፡ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

እነርሱም፡ “ኪዳነ ምሕረት”፥ “ቤተ ክርስቲያን”፥ “ኢትዮጵያ” የተባለችው፥ የቅዱሱ ኪዳን ምልክቶችም ኹሉ፡ ምሳሌዋ የኾኑላት፡ ድንግል ማርያም መኾኗን፥ ዛሬ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ፡ እየደረሰ እንደሚታየው፡ እርሷን፡ ኢትዮጵያንና የእርሷ የኾኑትን፡ ልጆቿን፡ ኢትዮጵያውያንን፡ “የቀደመው እባብ”፥ “ታላቁ ቀይ ዘንዶ”፥ “ዓለሙን የሚያስተው ሰይጣን” የተባለው ዲያብሎስ፡ እስከመጨረሻው፡ የሚያሳድዳቸው መኾኑን አረጋግጠው ያሳያሉ።

*፩) “‘በበዛችሁም ጊዜ፥ በምድር ላይ በረባችሁም ጊዜ’ ይላል እግዚአብሔር፥ ‘በዚያ ዘመን፡ ፡የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ብለው፡ ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም፤ ልብ አያደርጉትም፤ አያስቡትምም፤ አይሹትምም፤ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም።’”*

*፪) “ከዚህ በኋላ፡ በሰማይ ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፤ የኪዳኑም ታቦት፡ (ድንግል ማርያም) በመቅደሱ ታየ! መብረቅና ድምፅም፥ ነጐድጓድም፥ የምድር መናወጥም፥ ታላቅ በረዶም ኾነ!*

*“ታላቅ ምልክትም፡ በሰማይ ታየ! ፀሓይን ተጐናጽፋ፥ ጨረቃ፡ ከእግሮቿ በታች ያላት፥ በራስዋም ላይ፡ የአሥራ ኹለት ከዋክብት አክሊል የኾነላት፡ አንዲት ሴት (ድንግል ማርያም) ነበረች። እርሷም፡ ፀንሳ ነበር፤ ምጥም ተይዛ፡ ልትወልድ ተጨንቃ፡ ጮኸች። ሌላም ምልክት፡ በሰማይ ታየ! እነሆም እርሱ፡ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት፡ ታላቅ ቀይ ዘንዶ (ዲያብሎስ) ነበረ፤ በራሶቹም ላይ፡ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፤ ጅራቱም፡ የሰማይን ከዋክብት፡ ሲሶ እየሳበ፡ ወደምድር ጣላቸው።*

*“ዘንዶውም፡ ሴቲቱ በወለደች ጊዜ፡ ሕፃንዋን (ኢየሱስ ክርስቶስን) እንዲበላ፡ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ! ሴቲቱም፡ አሕዛብን ኹሉ፡ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ፡ ያለውን ልጅ፥ ወንድ ልጅ ወለደች! ልጇም፡ ወደእግዚአብሔር፥ ወደዙፋኑ ተነጠቀ! ሴቲቱም፡ ሺህ ከኹለት መቶ ስድሳ ቀን፡ በዚያ እንዲመግቧት፡ በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ሥፍራ፥ ወደበረሃ (ወደኢትዮጵያ) ሸሸች።*

*“በሰማይም ሰልፍ ኾነ! ሚካኤልና መላእክቱ፡ ዘንዶውን ተዋጉ! ዘንዶውም፡ ከመላእክቱ ጋር ኾኖ ተዋጋቸው፤ አልቻላቸውምም። ከዚያም ወዲያ፡ ዘንዶው፡ በሰማይ፡ ማረፊያ ሥፍራ አላገኘም፤ ይኸው፡ ታላቅ ዘንዶ፡ ወደምድር ተጣለ! ዓለሙንም ኹሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው፡ ታላቁ ዘንዶ፡ እርሱም፡ የቀደመው እባብ ወደምድር ተጣለ! መላእክቱም፡ ከእርሱ ጋር ተጣሉ!*

*“ታላቅም ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ፤ እንዲህ ሲል፦ ‘አሁን፡ የአምላካችን፡ ማዳንና ኃይል፥ መንግሥትም፥ የክርስቶስም ሥልጣን ኾነ! ቀንና ሌሊትም፡ በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው፡ የአባቶቻችን ከሳሽ ተጥሏልና። እነርሱም፡ ከበጉ ደም የተነሣ፡ ከእውነተኛ የምስክርነት ቃላቸውም የተነሣ፡ ድል ነሡት! ነፍሳቸውንም፡ እስከሞት ድረስ አልወደዱም። ስለእነርሱም፡ ሰማያትና በውስጣቸው የምትኖሩ ሆይ! ደስ ይበላችሁ! ለምድርና ለባሕር ግን፡ ወዮላቸው! ዲያብሎስ፡ የቀረው ዘመን ጥቂት መኾኑን አውቆ፡ በታላቅ የቁጣው መርዝ፡ ወደእናንተ ወርዷልና።’*

*“ዘንዶውም፡ ወደምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ፡ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት! እርሷም፡ ከእባቡ ፊት ርቃ፡ አንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኩሌታ ወደምትመገብበት፡ ወደሥፍራዋ፡ ወደበረሃ እንድትበር፡ ለሴቲቱ፡ ኹለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት።*

*"እባቡም፡ ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ፡ ወንዝ የሚያህልን ውኃ፡ ከአፉ፡ በስተኋላዋ አፈሰሰ። ምድሪቱም፡ ሴቲቱን ረዳቻት፤ ምድሪቱም፡ አፏን ከፍታ፡ ዘንዶው፡ ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው። ዘንዶውም፡ በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት (ቃል ኪዳናት) የሚጠብቁትን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ እውነት የሚኖሩትንም፡ የቀሩ ልጆቿን (ኢትዮጵያውያንን) ሊዋጋ ኼደ፤ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ።"*[፺፮]

እንግዴህ፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ በምድር ላይ ሣለ፡ ማረፊያው ኾኖ የቆየው፡ በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ መኾኑን ለማዘከርና ይህን ትውፊት ለመጠበቅ ሲባል፡ ይኸው፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ የተቀደሰ ቅርስ፡ ማለትም፡ በምሥጢረ ሥጋዌ ከተሠወሩት፡ ከጽላቱና ከታቦቱ በቀር፡ ሌሎቹ፡ ንዋያተ ቅድሳት፡ በርእሰ አድባራት አኵስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ዓፀድ ውስጥ በምትገኝ፡ በአንዲት የተለየች፡ የተቀደሰች ዕቃ ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ።

ይህም ይታወቅ ዘንድ፡ የቀደሙት አባቶቻችን፡ የተቀደሰው የታቦተ ጽዮን ቅርስ፡ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ፡ በመዘክርነት እንዲቀመጥባት ወደተዘጋጀችው፡ "ዕቃ ቤት" ወደተባለች፡ ልዩ ቤተ ጸሎት እንዲዛወር፥ በዚያም ላይ አምልኮና የምሥጢረ ቊርባን ሥርዓተ ቅዳሴ ሳይፈጸምበት፡ በጸሎተ እጣን ብቻ እንዲከበር በማድረጋቸው፡ እውነታው ይታወቃል።

እውነተኛዋና አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምና ልጇ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በዚያች ቤተ ጸሎት ኾነ፡ በሌሎቹ ቅዱሳት መካናት የሚገኙት በመንፈስ ብቻ ነው! ስለዚህም ነው፡ እስከዛሬና ዛሬ፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም፡ ማንም ሰብአዊ ፍጡር፡ እርሷን፡ ታቦተ ጽዮንን፡ በኢትዮጵያ፡ "አለች!" ብሎ፡ በዘመነ ብሉይ፡ ሙሴ እንዳያት፡ ሊያያት፥ ዳዊት እንዳገኛት፡ ሊያገኛት፥ ፍልስጥኤማውያን እንደወሰዷት፡ ሊወስዳትና እነአዛርያስ እንደሠረቋት፡ ሊሠርቃት፥ ሌላውንም ድርጊት፡ በእርሷ ላይ ሊፈጽም የማይቻለው።

ይህን የታቦተ ጽዮንን የተቀደሰ ቅርስ፡ "ዕቃ ቤት" ተብሎ፡ አንድ መነኵስ፡ በቀዋሚው የአኵስም ጽዮን ማኅበር፡ መራጭ ምርፋቅ እየተሠየመ፥ ለዚህ የዕድሜ ልክ ጥበቃና የጸሎተ ዕጣን አገልግሎትም እየተመደበ፡ በዚህ መልክ ሲሠራ ይኖራል።

## ኢትዮጵያ፡<br>ስለታቦተ ጽዮን ፍለጋ<br>ስትፋረድ!

ታቦተ ጽዮን፡ በጥንታዊው ግዛፍነቷ፡ በምድር ላይ፡ በአካል መኖርዋን ለማረጋገጥ፡ በመካከለኛው ዘመን ተነሥተው ከነበሩት፡ "ቴምፕላርስ" (Templars) ከተባሉት፡ ከቅርቦቹ እንግሊዛውያን የሃይማኖት ጀብደኞች ጀምሮ፡ ጀምስ ብሩስ (James Bruce) እና ግራም ሓንኮክ (Graham Hancock) እስከተባሉት፡ እስከኋለኞቹና እስከዛሬዎቹ ሌሎች እንግሊዛውያን ድረስ፡ ሲፈጸም የኖረውን ብርቱ ፍለጋ በሚመለከት፡ ከተፈጸሙ እንግዳ ድርጊቶች መካከል፡ አንዱን ብቻ፡ እስቲ፡ እዚህ ላይ ላውሳው!

# ኢትዮጵያ!

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ፡ ኢትዮጵያን፡ ከእስልምና ወረራ ለማዳን ብቻ ሳይኾን፡ ኢየሩሳሌምንም ነጻ ለማውጣት፡ "እኛ ክርስቲያኖች በበለጠ ብንወዳጅና ብንተባበር! ይህንንም የተቀራረበ ግንኙነታችንን፡ በጋብቻ ሳይቀር ወደዝምድና ከፍ ብናደርገው! ለዚህ የሚያገለግለንን፡ የጦር መሣሪያ ማምረቻ፡ እዚህም፡ በኢትዮጵያ ምድር ብናቋቁም!" የሚል አሳባቸውንና ምኞታቸውን የያዘ ደብዳቤ፡ ለእንግሊዟ ንግሥት ቪክቶርያ ልከው፡ የጠበቁትንና ተገቢ የነበረውን ምላሽ ሳያገኙ በመቅረታቸው፡ የራሳቸውና የኢትዮጵያ፥ የሕዝባም ክብር እንደተነካ ቆጥረውት፡ ይህን ጥቃት ለመወጣት ሲሉ፡ በአጠገባቸው ይኖሩ የነበሩትን፡ የእንግሊዝን መንግሥት ተጠሪ፥ ሌሎቹንም አውሮጳውያን ጭምር ይዘው ማሠራቸው ይታወቃል።

ከዚህ የተነሣ፡ የእንግሊዝ መንግሥት፡ ሰር ሮበርት ናፒየር የተባለውን የጦር አዛዡን፡ ከነሠራዊቱ፡ ከሕንድ ወደኢትዮጵያ ከመላኩ በፊት፡ ችግሩን፡ በዕርቅ ለመፍታት ሲል፡ በኢየሩሳሌም፡ ለኢትዮጵያ የቅርብ ወዳጅነት አላቸው የተባሉትን፡ የአርመን ሊቀ ጳጳስ ይስሓቅ ዘኻርጰርን፡ ዲሞጥዮስ ከተባለ፡ አንድ ሌላ ፡መነኰሴ ጋር ወደአጼ ቴዎድሮስ፡ በሽምግልና ላከ።

ዳሩ ግን፡ ባዕዳኑ ሽማግሌዎች፡ ኢትዮጵያ ገብተው፡ ከአጼ ቴዎድሮስ ለመድረስ፡ በሰሜንና በመኻል ኢትዮጵያ ወዲያ ወዲህ እያሉ ሲባዝኑ፡ ረዥም ጊዜ አልፎባቸው፡ በመጨረሻ፡ አጼ ቴዎድሮስ ሞተውና አጼ ዮሓንስ በዙፋኑ ተቀምጠው አገኟቸው። ጳጳሱም፡ የመጡበትን ምክንያት፡ ለአጼ ዮሓንስ ካስረዷቸው በኋላ፡ ምንም እንኳ፡ ተልእኳቸው፡ አስፈላጊነቱ ያበቃ ቢኾንም፡ "መቼም፡ አንድ ጊዜ፡ ኢትዮጵያ ድረስ መጥቻለሁና፡ ስመኘው የኖርሁትን ፈቃዴን ለመፈጸም ያብቁኝ!" ሲሉ፡ እንግዳው ጳጳስ፡ አጼ ዮሓንስን ለመኗቸው። ልመናቸውም፡ "በአኵስም 'አለች!' የምትባለውን፡ ታቦተ ጽዮንን ለማየት" ነበር።

አጼ ዮሓንስም፡ የውጭ ግንኙነታቸው እየዳበረ እንዲኼድ ለማድረግ በሚረዳቸው፡ በዚህ አጋጣሚ ዕድል ለመጠቀም በማሰብ ይመስላል፡ ነገሩ ሊኾን እንደማይችል እያወቁ፡ የጳጳሱ ፍላጎት ይፈጸምላቸው ዘንድ በማሳሰብ፡ ደብዳቤ ጽፈውና መልእክተኞች ጨምረው፡ እንግዶቹን፡ ወደአኵስም ማኅበር ላኳቸው። እንደተፈራውም፡ የጳጳሱ ጥያቄ ሳይፈጸም ቀረና፡ ለዚሁ አቤቱታ፥ ካልኾነም፡ በዚያው ተሰነባብተው፡ ወደአገራቸው ለመኼድ፡ እንግዶቹ፡ ወደአጼ ዮሓንስ ተመልሰው መጥተው ተገናኟቸው። ጳጳሱ፡ የንጉሡ ትእዛዝ ተከብሮ ሳይፈጸም በመቅረቱ የተሰማቸውን ቅሬታና ኀዘን ስለገለጹ፡ "እንግዶቹን በኾነው መልክ አስደስተው ይሸኟቸው ዘንድ፡ አደራ!" በማለት፡ አጼ ዮሓንስ፡ እንደገና፡ ጠበቅ ያለ መልእክትን ያዘለ ደብዳቤ አስይዘው፡ ጳጳሱንና መነኰሴውን፡ ወደአኵስም ማኅበር መለሷቸው።

በአኵሱሞች ዘንድ፡ የእሪቱ ሥርዓት እንደተጠበቀ ስለኾነ፡ ማንም ካህን፡ ጳጳስም ቢኾን፡ ጽላተ ኪዳኗን ማየት ቀርቶ፡ አለችበት መንበር ድረስ እንኳን እንዲገባ አይፈቅዱለትም። አሁን፡ የአጼ ዮሓንስ ድጋሚ መልእክት ሲደርሳቸው፡ የሚያደርጉት ቸግሩዋቸው፡ ሌላ ምንም ዘዴ ስላጡ፡ ከአዲስ ኪዳኑ ጽላቶች መካከል፡ አንዱን አውጥተው፡ "ጽላቷ ይህች ናት!" ብለው ለጳጳሱ አሳዩዋቸው።

ከጳጳሱ ጋር የነበረው መነኩስ፡ የሥዕል ባለሙያ ስለነበረ፡ "ጽላት" ተብሎ የቀረበላቸውንና ያዩትን የእብነ በረዱን ባለአራት ማዕዘን ስሌዳ፡ ልኩንና ቅርጹን፡ በቢጋር ሠርቶ፡ በላዩም፡ እንደጠበቁት፡ በእብራይስጡ ፊደላት የተጻፉትን፡ አሥሩን ቃላት ሳይኾን፡ የመስመር ቅርጽና ሥዕል መሳይ ንድፍ ብቻ ያገኙበት መኾኑን በመግለጽ የጻፈውን ማስታወሻ ጠቅሶ፡ ጂ. ቢ. ኩልቦ የተባለ ፈረንሳዊና ካቶሊካዊ ካህን፡ በኢትዮጵያ የታሪክ መጽሐፉ፡ ስለታቦተ ጽዮን ነገር፡ ያወቀውንና የተረዳውን፡ ለዓለም ገልጿል::[፵ሀ]

የአኵስም ጽዮን ማኅበር፡ መቼም፡ ዘዴኞች ናቸውና፡ "ታቦተ ጽዮን ናት" ብለው ያን፡ በሥዕል ንድፍ የተቀዳ ገበታ፡ ገልጠው ያሳዩት፡ በአንድ በኩል፡ የባዕዳኑን ጳጳስና መነኩስ ፍላጎት በማሟላት፡ አጼ ዮሐንስን ለማስደሰት፥ በሌላው በኩል ደግሞ፡ የኖረ ሥርዓታቸው እንዳይፈርስባቸው ሲሉ፡ ዛሬ በየቤተ ክርስቲያኑ ያለውን ከሚመስለው፡ ከአዲስ ኪዳኑ ጽላት መካከል፡ አንዱን መርጠው፡ ለእንግዶቹ አቅርበውላቸው እንደኾነ አይታወቅም::

እኔ ራሴ፡ የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ ኾኜ፡ በዚያ አገለግል በነበረበት ጊዜ፡ ገና በመጀመሪያ፡ አኵስም በገባሁባት ዕለት፥ ከዚያም በኋላ፡ የታቦተ ጽዮንን የተቀደሰ ቅርስና የቤተ ክርስቲያኒቱን ንዋያት ቅድሳት የሚጠብቁ በመኾናቸው፡ ራሳቸው "ዕቃ ቤት" የሚባሉት መነኩስ፡ ከበዓታቸው ስለማይወጡ፡ እርሳቸውን ለመጠየቅ፡ በየጊዜው ወደእርሳቸው እየኼድሁ፡ የታቦተ ጽዮን የተቀደሰ ቅርስ ወደሚገኝባት ክፍል ድረስ እገባ ነበረ:: በዚያን ጊዜና በዓት፡ ተገቢውን ጸሎት አድርጌና ከዕቃ ቤቱ ጋር ተነጋግሬ ከመመለስ በስተቀር፡ "ታቦተ ጽዮን፡ በእርግጥ እዚህ እንዳለች እንዲነግሩኝ፥ ወይም፡ እርሷን ገልጠው እንዲያሳዩኝ፡ እስቲ፡ ዕቃ ቤቱን ልጠይቃቸው!" ብዬ፡ ይህን ድርጊት፡ እንኳንስ በአንደበቴ በማሰማት ልፈጽመው ቀርቶ፡ በአእምሮዬም ላስበው አልቃጣም ነበር፤ በሕሊናዬም ጨርሶ አልነበረም፤ አይኖርምም፤ ሊኖርም አይችልም:: ምክንያቱም፡ ይህን ድርጊት፡ እንኳንስ መፈጸሙ፡ ማሰቡም እንኳ፡ ታላቅ ኃጢአት ኾኖ፡ በሥጋዬ ላይ፡ የሞት መቅሠፍትን፥ በነፍሴም ላይ፡ የዘለዓለም ደይንን የሚያስከትል መኾኑን፡ በሃይማኖት አረጋግጬ ስለማውቅ ነው::

ይህም ማለት፡ "ራሴን፡ ገና በዘመነ ኦሪቱና በኪዳነ ኦሪቱ ቀምበር ሥር እንዳለሁ አድርጌ በመቁጠር፡ 'ታቦተ ጽዮን፡ በዚያች፡ ቅድስት ዕቃ ቤት አለች' ብዬ የማምንም ቢኾን ኖሮ እንኳ፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ እርሷን ማየት፥ ወይም ያለችበትን መንበር መንካት ቀርቶ፡ 'የዘመኑ ሊቀ ካህናት ነኝ' ብዬ፡ እርሷ ከምትገኝበት፡ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ፡ አለጊዜው መግባት እንኳ፡ በሞተ ሥጋ እንደሚያስቀሥፈኝ በማወቄ ነው፤ አለዚያ ደግሞ፡ ዛሬ በዘመነ አዲስ፡ በኪዳነ ምሕረት ጸጋ ተመልቼ የምኖር በመኾኔ፡ *'በሰማይም ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ! የኪዳኑም ታቦት፡ በመቅደሱ ታየ!'* በሚለው፡ የራእየ ዮሐንስ ቃል መሠረት፡ በአሁኑ ጊዜ፡ ታቦተ ጽዮን፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሕያው ኾና፡ በሰማያት፡ በአካለ ትንሣኤ፥ በምድር ደግሞ፡ በአካለ መንፈስ ቅዱስ እንደምትገኝ ስለማምን፡ ይህን ሃይማኖቴን ከንቱ ማድረጌ፡ የነፍስ ደይንን እንደሚያስከትልብኝ በማወቄ ነው" ማለት ይኾናል::

ይህ ነገር፡ "በእውነትና በመንፈስ" ልንፈጽመው የሚገባንን አምልኳችንን፡ በጥልቅ የሚመለከት አምላካዊ ጉዳይ ስለኾነ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በብርቱ ሊያስቡበትና ሊጨነቁበት፥ሊጨክኑበትም የሚያስፈልግ ስለኾነ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ኾነው፥ በጾም በጸሎትም ተወስነው፡ መርምረውትና አጥንተውት፡ በቅዱሱ ኪዳን የተዋህዶ ሃይማኖታቸው ላይ፡ በጽኑ የተመሠረተውን ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ በጊዜው አጥርተው በማስተካከል፡ በያግጣጫው ከዘመተባቸው፡ ከዲያብሎስ፡ የባዕድ አምልኮ፥ የኑፋቄና የክህደት አስፈጻሚ ሠራዊት፡ ራሳቸውን ጠብቀውና ተከላክለው መኖር ይገባቸዋል።

## የአዲስ ኪዳኑ ታቦት
## አገልግሎት።

ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ኹለቱን ጽላት የያዘው፡ ዋናው የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ በመላው የብሉይ ኪዳን ዘመን፡ ምንጊዜም፡ አንድ ብቻ የተቀደሰ ማዕከላዊ አካል ኾኖ ኖርዋል። ይኹን እንጂ፡ በእርሱ ቦታ፡ እርሱን የሚተካ፡ ነገር ግን፡ በአዲስ ኪዳኑ እምነት መሠረት፡ አራት ማዕዘን ኾኖ የተቀረጸ፡ አንድ ጽሌን ብቻ የያዘ፡ ሌላ ተመሳሳይ ታቦት ተዘጋጀ።

ይህም አዲሱ ታቦት፡ የቀደመውን የብሉዩን ታቦት፡ ምሳሌዋ፥ ጥላዋና አርአያዋ አድርጋ ቆይታ፡ አሁን፡ ራሷ፡ አማናዊቷ፥ ሕያውቷና ዘለዓለማዊቷ የቃል ኪዳን ታቦት በኾነችው፡ በቅድስት ማርያም ጽዮን ስም ተሠይሞ፡ ወደቤተ ክርስቲያንነት በተቀየረው ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ።

ኹለቱን፡ የብሉዩን ኪዳን ጽላት ተክቶ፡ በአዲሱ ታቦት ውስጥ የተቀመጠው፡ አዲሱ፡ አራት ማዕዘን ነጠላ ጽሌ፡ በላዩ ተቀርጾ የሚታየው ጽሑፍ፡ እንደቀደሙት ጽላት፡ አሥሩን ትእዛዛት የያዘው፡ የእግዚአብሔር ቃል ሳይኾን፡ ያ ቃል፡ በድንግል ማርያም ማኅጸን፡ ሰው መኾኑን ለማሳየት፡ በመኻል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ስቅለት ኾኖ፡ በቀኝ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፥ በግራ፡ የወንጌላዊው ዮሐንስ ሥዕሎች፥ ዙርያውንም፡ የእግዚአብሔር፡ የአምላክነቱ ስሞች ተጽፈውና ተሥለው ነው። ያ፡ ታቦት የሚገኝበት ቤተ መቅደስ፡ በጌታ ወይም በእመቤታችን ስም እንደኾነ፡ ስማቸው፥ አለዚያ፡ መታሰቢያነቱ፡ ለነቢይ፥ ለሐዋርያ፥ ለጻድቅ፥ ለሰማዕት ወይም ለመልአክ ከኾነ፡ የዚያ ቅዱስ ስም፡ "ዝ ጽላት፡ ዘቅዱስ እከሌ" ተብሎ፡ ከጀርባው ይቀረጽበታል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ በዚያ፡ በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳኑ ጽሌ ዓይነት፡ ነገር ግን አራት ማዕዘን ኾኖ፡ በዕብነ በረድ፡ ወይም በማይነቅዝ የእንጨት ወገን፡ በተለያየ ቅጽና ቅርጽ እየተዘጋጀ፥ እየተራባና በተገቢው ሥርዓተ ጸሎት እየተባረከ፥ ታቦት በተባለውም፡ የእንጨት ሣጥን ውስጥ በክብር እንዲቀመጥ እየተደረገ፡ ሲሠራበት ኖርዋል። ከዚህ በኋላ፡ ይህን የመሰለውን ጽላትና ታቦት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ለሰው ልጆች ባስገኘው ዘለዓለማዊ ትድግናው አማካይነት፡ የሚወርዱትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች፡ ወደምእመናን ለማስተላለፍ የሚያስችሉት ምሥጢራትና ሥርዓታት በሚፈጸሙበት፡ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ባለው መንበር ውስጥ ያኖሩታል።

በብሉዩ ኪዳን እንደነበረው ኹሉ፡ የአዲስ ኪዳኑም ጽሌ፡ ወይም በልማድ እንደሚባለው፡ ጽላቱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፥ ታቦቱ ደግሞ፡ የቅድስት እናቱ፡ የድንግል ማርያም ምሳሌ የመኾኑ ምሥጢር፡ ሳይቃወስ ቀጥሏል። እንዲህ ኾኖ፡ የአዲስ ኪዳኑን እምነት በመከተል፡ እስከዛሬ ያልቋረጠው፡ ይህ፡ የጽላትና የታቦት ዝግጅትና ሥርዓት፡ እስከዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር በተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ሲካኼድ የኖረው፡ ለምን እንደኾነ፡ ከዚህ የሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች በሚበቃ ያስረዳሉ፡-

፩ኛ፡ ማናቸውም የቤተ ሕዝቡ ሰበካ ጉባዔ፡ ማለትም፡ ገጠር፥ ደብር ወይም ገዳም፡ በማኅበር ተቋቁሞና በቤተ ክርስቲያንነት ተደራጅቶ መገልገል ሲፈልግ፡ ጽላቱ፡ ከሌላ ከማንም ምእመን፥ ካህን ወይም ጳጳስ ሳይኾን፡ ሕጋዊው ሥልጣን ካላት ቤተ ክህነት ብቻ፡ ለዚያ ሃይማኖታዊ አቋምና መንፈሳዊ ድርጅት፡ የመሠረቱ ድንጋይ፥ ሕጋዊው ፈቃድና መለኪታዊው ማኅተም ኾኖ ይሰጣል።

፪ኛ፡ ካህናቱ፡ በእውነተኛው ሃይማኖታዊ አምልኮ ኾነው፡ በቅዳሴ ጊዜ በሚያከናውኑት ሥርዓተ ጸሎት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል በዚያ ተገኝቶ፡ ወደኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለውጠው ዘንድ፡ ኅብስተ አኰቴቱን፡ በጻሕል፥ ወይኑ በረከቱን፡ በጽዋ አድርገው፡ ለሚያቀርቡት ቅዱስ ቁርባን፡ በመንበሩ መካከል ጽላቱን ይዞ የሚገኘው ታቦት፡ መሠዊያ ኾኖ፡ ተልእኳቸው ይፈጸምበታል።

፫ኛ፡ በኪዳነ ልቦና፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፥ ከዚያም በኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር በኩል፡ እስከንግሥተ ሳባ ዘመን፡ ተያይዞ የደረሰው፡ የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዓ በረከት አምልኮተ እግዚአብሔር፡ በኪዳነ ኦሪቱ ተጠናክሮ ከኖረ በኋላ፡ በአዲሱ ኪዳን፡ የክርስትና እምነት ጸድቆ እንዲቀጥል በተደረገ ጊዜ፡ የጽላቱና የታቦቱ ሥርዓት፡ ሽግግሩን እንዴት እንዳሠመረው በማዘከር፡ ይህን ቅርስ ጠብቃ የኖረች ኢትዮጵያ ብቻ መኾኗን ለማረጋገጥ፡ የአዲስ ኪዳኑን ጽላት የያዘው፡ ይኸው ታቦት፡ የዚህ ትውፊት፡ አማናዊ ድልድይና ቋሚ ማስረጃ ኾኖ፡ ለትውልደ ትውልድ ይተላለፍበታል።

ይህን፡ የብሉይ ኪዳኑን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓት፡ እንዲህ፡ በአዲስ ኪዳኑ ምሥጢራት አድሶና አስተካክሎ በመተካት፡ የቀድሞው ቅርስ ተጠብቆና ሕያው ኾኖ እንዲቀጥል የማድረጉ ችሎታና ብቅዓት የተገኘው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ መኾኑ ይታወቃል። ይኹን እንጂ፡ ኢትዮጵያውያን፡ አምላካቸውን፡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት፡ ይኸው አዲሱ የክርስትና ሥርዓት፡ ጥንትም ኾነ ኋላ፥ ምንጊዜም፡- *"እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል።"* በሚለው በጌታችን በኢየሱስ[፶፰] ክርስቶስ ቃል ላይ የተመሠረተና ያንን የተከተለ መኾኑ ሊዘነጋ አይገባም።

ይህን የመሰለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተመሠረተው፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር ባህል፡ ባንድ ወገን፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ እስከመጨረሻው፡ በዚችው ምድር ለመቆየቱ፡ ተጨባጭ ማስረጃና ሕያው ምስክር ሲኾን፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በመላዋ ምድር ላይ በሚገኙት፡ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ መካከል፡ ከኹሉ የተለየች ብርቅና ከኹሉ የቀደመች አረጋዊት ለመኾኗ፡ ዓቢዩ መለያ ምልክት ኾኖ ይኖራል።

በሐዋርያት ሥራ ላይ ተጽፎ እንደሚነበበውና በመላው ዓለም ሕዝቦች ዘንድ በይፋ እንደሚታወቀው፡ ሐዋርያው ፊልጶስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ባጠመቀው፡ በዚያ፡ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አማካይነት፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል፡ እጅግ አብዛኛው ክፍል፡ ክርስቲያን ኾነ!

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ያንኑ የኦሪቱን እምነት እንደያዙ ለመቀጠል እንጂ፡ ክርስትናን ለመቀበል ፈቃደኞች ያልኾኑ ጥቂት ወገኖችም ነበሩ፤ እነዚህ አናሳ ወገኖች፡ ክርስቲያን ከኾነው ከቀረው ኅብረተሰባቸው፡ ራሳቸውን አግልለው ስለተለዩ፡ "ፈላሻ" የሚል ስም ወጥቶላቸው፡ በዚሁ ይጠሩ ጀመር:: "ፈለሰ" የሚለው የግእዙ ቃል፡ "ተለየ፥ ተሰደደ" ማለት ነው:: ባዕዳን ግን፡ እነዚህን ፈላሾች፡ "የኢትዮጵያ አይሁድ" ይሏቸዋል::

## በታቦት የሚፈጸመው አምልኮ፡ "በመንፈስና በእውነት" ስለመኾኑ::

እስከዚህ ድረስ የታተተው አሠራር፡ ኢትዮጵያውያን፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመን ይፈጽሙት የነበረውን፡ ያን፡ የጽላትና የታቦት ሥርዓታቸውን፡ በማኅበር ደረጃ፡ በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው፡ በግዙፉ አካላዊ መልኩ፡ ለአዲስ ኪዳኑ ዘመን እምነታቸውና አምልኳቸው፡ እንዴት፡ እንዲስማማ በማድረግ፡ አዘጋጅተው፥ አደራጅተውና አከናውነው መቀጠል እንደቻሉ ለማስረዳት ያህል ነው::

በረቀቀው አማናዊ መልኩ ግን፡ "በእውነትና በመንፈስ" መመለክን የሚፈልገውና የሚወድደው ፈጣሪያቸው፡ በአዲሱ ኪዳን የታተመውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሕጉን የጻፈበት ሕያው ጽላት፥ ያ ጽላት የተቈለፈባት ታቦት፥ ታቦቱ የተቀመጠበት መንበር፥ መንበሩ የቆመበት፡ ቤተ መቅደስ፥ በጠቅላላ ማደሪያው፡ ቤተ ክርስቲያኑ፡ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና የእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት ልብ፥ ልቦናና ሰውነት መኾኑን፡ ራሳቸው ኢትዮጵያውያን አምነው፥ ይህንኑ ሃይማኖታቸውን በምግባር በመግለጽ፡ ሌሎችንም ያሳምናሉ::

ይህንንም፡ ከላይ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውና እንዲህ ተብሎ በትንቢት የተነገረው፥ ደግሞም በሐዋርያው መልእክታት ውስጥ የሠፈሩት፡ የእግዚአብሔር ቃላት ያረጋግጡላቸዋል:- *"'እነሆ፥ ከእስራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል!' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ፡ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን፡ ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም! እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኳቸው!' ይላል እግዚአብሔር:: 'ከእነዚያ ወራት በኋላ፡ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና!' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ! በልባቸውም እጽፈዋለሁ! እኔም አምላክ እኾናቸዋለሁ! እነርሱም ሕዝብ ይኾኑኛል::'"*

*"የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደኾናችሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲያድርባችሁ፡ አታውቁምን? ማንም፡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ ቅዱስ ነውና፤ ያውም፡ እናንተ ናችሁ! ...የእግዚአብሔርን ታቦት፡ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው? እኛ፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና!"* [፶፰]

በዘመነ አሪትና በዘመነ ሐዲስ ያለው፡ የጽላትና የታቦት ነገር፡ ጥልቅ የኾነውን፡ መለኮታዊ ምሥጢር የያዘ ስለኾነ፡ ስለእርሱ ለመረዳት፡ በዚያው በእግዚአብሔር መንፈስ ኾኖ ማንበብን፡ ወይም ማዳመጥን የሚጠይቅ መኾኑን በመግለጽ፡ ስለዚሁ ምሥጢር፡ የሚከተለው ማብራሪያ ቀርቧል።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዘመነ ብሉይ፡ በኪዳነ አሪት፡ ማለትም፡ ገዝፎ በሚዳሰሰውና ዓሠርቱ ቃላት የተጻፉበትን፡ ጽላተ ኪዳኑን በያዘው ታቦት ላይ፡ በአኵስም ጽዮን ቤተ መቅደስ፡ እናካኺደው የነበረው የእግዚአብሔር አምልኳችን ሥርዓት፡ በሃይማኖት ያበቃው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በእናቱ ድንግል ማርያም ምክንያት፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነውን፡ የጥምቀትን መንፈሳዊ ልደት በተቀበልንባት አፍታ ነበረ።

ያችም አፍታ፡ እንደቀን አቆጣጠራችን፡ ያ፡ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" የምንለው፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ በሐዋርያው ፊልጶስ እጅ የተጠመቀባት አፍታ ናት። ይህም ምሥጢራዊ ሥርዓት፡ ብዙም ሳይቆይ፡ ተከታትሎ፡ በአኵስም እንደተፈጸመ፡ ከዚህ የሚቀጥለው፡ የሐዋርያት ሥራ ጥቅስ ያስረዳል። *"ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ ኹለቱም ወደውኃ ወረዱ፤ አጠመቀውም። ከውኃው ከወጡም በኋላ፡ የጌታ መንፈስ፡ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም፡ ኹለተኛ አላየውም፤ ደስ ብሎት መንገዱን ይኼድ ነበርና።"* የሚለው ቃል፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ የምሥራቹን[፶] ዜና፡ ወደአገሩ ለማድረስ፡ ምን ያህል እንደቸኰለ ያመለክታል።

በይፋ የኾነውን ለማስረዳት፡ እንዲህ እንበል እንጂ፡ ጽላተ ኪዳኑን በያዘው ታቦት ላይ፡ በአኵስም ጽዮን ቤተ መቅደስ እናካኺደው የነበረው የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓት አብቅቶ፡ በአዲስ ኪዳኑ፡ የክርስትና ሥርዓት የመተካቱ ምሥጢር፡ በእውነት የተፈጸመው፡ ድንግል ማርያም፡ *"ትፀንሲ!"*፡ ማለትም፡ *"ትፀንሻለሽ!"* ያላትን፡ የመልአኩን የቅዱስ ገብርኤልን የምሥራች ቃል ተቀብላ፡ *"ይኵነኒ በከመ ትቤለኒ!"* ማለትም፡ *"እንዳልኸኝ (እንደቃልህ) ይኹንልኝ!"* ባለችበት ቅጽበት ነበር።

በዚያች ቅጽበት፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢርና ጥበብ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ላይ ዐርፎ የተፀነሰው፡ ያው፡ በጽላቷ ላይ ተቀርጾ የነበረው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የኾነችው፡ ጽላተ ኪዳንና የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው፡ የጽላቷ ማደሪያ ታቦት (ሣጥን)፡ ኹለቱም፡ በምድር ላይ ከነበሩበት ግዙፍ ህልውናቸው ተሠውረው፡ በሰውነት የተገለጹት፡ በዚያች ቅጽበት ነበር። ያም ሕያው ሰውነታቸው፡ ከትንሣኤ በኋላ፡ በመንፈሳዊው አካል ተለውጦ፡ ዛሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በሰማያዊትና ምድራዊት መንግሥታቸው ላይ በዘለዓለማዊነት ነግሠውና በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው ይገኛሉ። ወንጌላዊው ዮሐንስ፡ በራእዩ፡ *"በሰማይም ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ!* (ጽላቱን የያዘው) *የኪዳኑም ታቦት* (ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም)፡ *በመቅደሱ ታየ!"* በሚል ቃል አረጋግጦ የገለጸው፡ ይህንኑ እውነታ ነውና።

## ኢትዮጵያ፡

እኛም ዛሬ፡ በያዓመቱ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን በምናከብረው፡ የፍልሰታ ለማርያም በዓላችን ላይ፡ የምንፈጽመው ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ዮሐንስ፡ በራእዩ ያየውን፡ ያንን ሥርዓተ ሰማይ፡ በምድርም ላይ እውን አድርገን፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰማያዊት መቅደሱ፡ ቅድስት ንግሥት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን ታቦት፥ መንበር አድርጎ፡ ቀድሶ፡ ሐዋርያትን እንዳቆረበ፥ እንዲሁ፡ እኛም፡ ዕለቲቱን በማዘከር፡ መንፈሳዊት በኾነችው፡ ምድራዊት መቅደሱ፡ ያንኑ ሰማያዊ ሥርዓት፡ መልሰን መፈጸማችን እኮ ነው!

በየዕለቱ በሚካኼደውና በሚፈጸመው ሥርዓተ ቅዳሴያችን ላይ፡ የሚከናወነው፡ መለኮታዊና ሰማያዊ ምሥጢር እኮ፡ እጅግ ታላቅ ነው! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡- እኛ፡ እያንዳንዳችን፡ ካህኑም፥ ምእመኑም፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ከየኃጢአታችን ነጽተን፡ በእውነተኛው አምላክ፡ ከፈጣሪያችን፡ ከእግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ፡ መንፈሳዊው ጽላታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስና እርሱን የያዘችው፡ መንፈሳዊቷ ታቦታችን፡ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ በመንፈስ ቅዱስ አንድነት፡ ራሳቸውን ገልጸውልን ይቀበሉናል፡፡ ራሳቸውን፡ በመንፈስ ቅዱስ ገልጸው የሚቀበሉንም፡ የሥጋ ወደሙ መሠዊያ ኾኖ፡ በመንበሩ ውስጥ በተቀመጠው፡ ግዙፏን ጽላት በያዘው፡ በግዙፉ ታቦት ላይ ነው፡፡ በዚያን ጊዜም፡ አምልኳችን፡ እንደጌታ ቃል፡ "በእውነትና በመንፈስ" መካኼዱንና መከናወኑን እናረጋግጣለን፡፡

ይህን፡ ረቂቅ የኾነ መንፈሳዊ ምሥጢር፡ በሃይማኖቷዊው ዓይናችን አግዝፈን የምናየው፡ ታቦተ ጽዮን፡ በዘመነ አሪት፡ "ደብተራ ኦሪት" ከተባለችው፡ ከማደሪያዋ ድንኳን ጀምሮ፡ በጠቅላላ፡ በድንኳኗ ውስጥ የሚገኙት ንዋያት ቅድሳት፡ በሙሉ፡ ጽላቷና ታቦቷ ጭምር፡ እያንዳንዳቸው፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የእናቱ የድንግል ማርያም ምሳሌዎች መኾናቸውን በማረጋገጥ፡ በመዓልትና በሌሊት፥ በዘወትርና በሰንበታት፥ በሰዓታትና በማኅሌት የምናቀርባቸው ጸሎቶቻችን ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም፡ በሳምንቱ የዕለታት ውዳሴ ማርያምና በዘወትሩ ቅዳሴያት ምስጋናችን ውስጥ፡ እርሱን ልጇን፡ የአዲሱ ኪዳን ጽላታችን፥ እርሷን እናቱን፡ የአዲሱ ኪዳን ታቦታችን አድርገን፡ ያለማሠለስ የምንሰጠው ምስክርነት፡ ለምንነጋገርበት፡ የጽላትና የታቦት አርእስተ ነገር፡ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ይህንንም፡ እንደዓባይ ወንዝ ያለማቋረጥ ከሚፈስሰውና እንደውቅያኖስ መልቶ ከሚኖረው ቅዳሴና ውዳሴ ላይ፡ ለዓይነት ያህል፡ የተጨለፈውን ጥቂት ቃል፡ ከዚህ በሚከተለው ጥቅስ መመልከት ይቻላል፡፡

*"የዐቢ ክብራ ለማርያም፡ እምኵሎሙ ቅዱሳን፤ እስመ ድልወ ኮነት ለተወክፎ ቃለ አብ፤ ዘይፈርህዎ መላእክት፥ ወየአኵትዎ ትጉሃን፡፡ ጸረቶ ማርያም ድንግል በከርሣ፡፡ ይእቲ ተዓቢ እምኪሩቤል፤ ወትፈደፍድ እምሱራፌል፤ እስመ ኮነት ታቦተ፡ ለአሐዱ እምቅድስት ሥላሴ፡፡ ...አንቲ ውእቱ ደብተራ፥ እንተ ተሰመይኪ ቅድስተ ቅዱሳን፤ ወውስቴታ ታቦት፡ በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ፤ ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን፡፡ ... አንቲ ውእቱ ዳግሚት ቀመር፡ እንተ ትሰመይ ቅድስተ ቅዱሳን፡ ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን፥ ዐሠርቱ ቃላት እለ ተጽሕፋ በአጻብዒሁ ለእግዚአብሔር፤ ቀዲሙ ዜነወነ በየውጣ፥ እንተ ይእቲ፡ ቀዳሚ ስሙ ለመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ፤ ወኮነ ዐራቄ ለሓዲስ ኪዳን፡፡*

"...ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ፥ ዘግቡር እምዕፅ ዘኢይነቅዝ፤ ይትሜሰል ለነ፡ ዘእግዚአብሔር ቃል፥ ዘኮነ ሰብአ፡ ዘእንበለ ፍልጠት፥ ወኢውላጤ። ...አንቲ ውእቱ፡ ሀየንተ አርያም ዘበሰማያት፡ ዘኮንኪ አርያመ፡ በዲበ ምድር፤ ብኪ አስተማሰሉ፡ ቅዱሳን ነቢያት፥ ካህናት ወነገሥት፤ ገብሩ ሎሙ ቅድስተ ቅዱሳን፤ ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን። ...ዐሠርቱ ቃላት እለ ተጽሕፉ በአጻብዒሁ፡ ለእግዚአ ኵሉ ፍጥረት፤ ኀደረ ወልደ አምላክ ላዕሌኪ። ...ቀዲሙ ዜነወነ አብ በየውጣ፥ እንተ ይእቲ፡ ዐሠርቱ ቃላት፡ እለ ተጽሕፉ በአጻብዒሁ ለእግዚአብሔር፤ ወመሀረነ ወልድከ፡ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ...ጽላት ዘሙሴ፤ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና። ...አ መፍቀሬ ሰብእ! አርኢ ገጸከ፡ ላዕለ ዝንቱ ኀብስት፥ ወዲበ ዝንቱ ጽዋዕ፥ ዘአንበርነ ላዕለ ዝንቱ ታቦት መንፈሳዊ ዘለከ!"

የዚህ፡ የግእዙ ቃል ነጠላ ትርጉም፡ እንዲህ ነው፡- "ማርያም ክብሩዋ፡ ከቅዱሳን ክብር ኹሉ ይልቅ ይበልጣል። በሰማያት፡ መላእክት የሚፈሩትንና ትጉሃን የሚያመሰግኑትን፡ የአብን ቃል ለመቀበል፡ የበቃች ኾና ተገኝታለችና፤ እርሱን፡ ድንግል ማርያም፡ በማኅጸኗ ተሸክመችው። ስለዚህ፡ እርሷ፡ ከኪሩቤል፥ ከሱራፌልም አብዝታ ትበልጣለች፥ ትልቃለችም፤ ከሦስቱ፡ የቅድስት ሥላሴ አካላት፡ ለአንዱ፡ ታቦት (ማደሪያ) ኾናለችና።

"...ከተለዩ የተለየች የተባልሽ፡ የኪዳኑን ጽላት፡ በውስጧ የያዘችውና ኹለንተናዋ በወርቅ የተለበጠው ታቦት፥ እርሷም የምትገኝባት ድንኳን አንቺ ነሽ። ...ለአዲሱ ኪዳን፡ አስታራቂ የኾነውና ከአምላክነቱ ሳይለወጥ፡ ካንቺ ሰው የኾነውን፡ የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ የመጀመሪያ ስሙን፡ ቀድሞ፡ በእርሷ የነገረን፡ እግዚአብሔር፡ በጣቶቹ የጻፋቸው፡ ዓሥሩ ቃላት የተቀረጹባትን የኪዳን ጽላት፡ በውስጧ የያዘችው ታቦትና ከተለዩ የተለየሽ የተባልሽ፡ የውስጠኛዪቱ መጋረጃ፡ አንቺ ነሽ።

"...ከማይነቅዝ እንጨት የተቀረፀውና ኹለንተናው፥ በወርቅ የተለበጠው ታቦት፡ ከመለኮቱ ያለመለየትና ያለመለወጥ፡ ካንቺ ሰው ለኾነው፡ ለእግዚአብሔር ቃል ተመሰለልን። ...በምድር ላይ ከፍተኛ አርያምን የኾንሽ፥ ከሰማያት በላይ ያለ፡ የአርያም የልዑል ሥፍራ ምትክ አንቺ ነሽ። በውስጧ፡ የኪዳኑን ጽላት የያዘችውን ታቦት፡ ያንቺ ምሳሌ አድርገው፡ ቅዱሳን ነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት፡ ቅድስተ ቅዱሳኑን ሠሩ። ...ዓሥሩን ቃላት በጣቶቹ የጻፈውና የፍጥረቱ ኹሉ ጌታ የኾነው የአምላክ ልጅ፡ ባንቺ ማኅጸን ተፀነሰ። ...አብ አስቀድሞ፡ በየውጣ ነገረን፤ የውጣም የተባሉ፡ በእግዚአብሔር የተጻፉ፡ ዓሥሩ ቃላት ናቸው፤ ይህንንም፡ ልጅህ፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረን። ...የሙሴ ጽላት፥ ተራራ ላይ እየተንበለበለች ሳትቃጠል ያያት፡ የሲና ቍጥቋጦ አንቺ ነሽ። ...ሰውን የምትወድድ ሆይ? በዚህ፡ ያንተ በኾነው፡ በመንፈሳዊው ታቦት ላይ ባኖርነው፡ በዚህ ኅብስት ላይና በዚህ ጽዋ ላይ ፊትህን ግለጽ!"

በሃይማኖታዊ አእምሮ የሚቀበሉትን፡ ይህን ምሥጢር፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል ማጠቃለል ይቻላል፡- በአሪቱ ጊዜ፡ ራሷ፡ ጽላቷ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀረጸባት ስለነበረች፡ ማኅደሩዋ ከኾነችው ታቦት ጋር ይሰገድላት፡ ማለትም፡ ትመለክ ነበር። ያች ጽላት፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" በሚለው፡ በወንጌላዊው የምሥራች ዜና መሠረት፡ ሰው ኾነች! እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጽላቷን የያዘችውና የአካላዊው ቃለ መለኮት ማደሪያ የኾነችውም ታቦት፡ ሰው ኾነች! እርሷም፡ ድንግል ማርያም ናት።

በመጨረሻ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም፥ ድንግል ማርያምም፡ ከትንሣኤያቸው በኋላ፡ ወደሰማይ ዓርገው፥ በሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋናቸውም ላይ ተቀምጠው፡ መላ ፍጥረታቸውን፡ በአባትነትና እናትነት፥ በንጉሥነትና ንግሥትነት፡ ያጠብቃሉ፤ ያስተዳድራሉ። በዳግም ትንሣኤ፡ በግዘፍ ተገልጠው፡ የቸርነት ሥራቸውን፡ ገሃድ እስኪያደርጉት ድረስ፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም ተገኝተው፡ ሥጋዊዉን ፍጥረት፡[፶፱] የሚጠብቁትና የሚያስተዳድሩት፡ በመንፈስ ቅዱስ ህልውናቸው ነው።

በኪዳነ አሪቱ ሥርዓት፡ ጽላቱና ታቦቱ፡ ሊለያዩ እንደማይችሉ፥ ቢለያዩ ግን፡ ያ፡ አማናዊው ማንነታቸውና ኃይላቸው ሊቀር እንደሚችል ኹሉ፡ እንዲሁ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ በሃይማኖታቸውም፥ በአምልኳቸውም፥ በስግደታቸውም፥ በምግባራቸውም፥ በሥርዓታቸውም፥ በባህላቸውም፥ በምስጋናቸውም፡ ማለትም፡ በድርሰታቸው አቀራረብ ኾነ በሥዕላቸው ዝግጅት እንኳ ሳይቀር፥ በመሳሰለው በማናቸውም ድርጊታቸው፡ በምንም መልክ ከቶ አይለያዩአቸውም። ሌሎች፡ ለያይተዋቸው ቢያገኟቸው፡ እነዚያ የተለያዩት እናትና ልጅ፡ በእነርሱ ዘንድ፡ እነርሱ የሚያውቋቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም አይኾኑም። ስለዚህ፡ ያልተለያዩትና የማይለያዩት፡ እናትና ልጇ፡ ከቃል ኪዳን ልጆቻቸው ኢትዮጵያውያንም፡ ሳይለዩ አብረዋቸው የሚኖሩት፡ እንዲህ፡ "በመንፈስና በእውነት" ስለኾነ፡ እኛም፡ በዚህ እምነት ኾነን፡ የምንሰግድላቸው፡ ማለትም፡ የምናመልካቸው፡ "በእውነትና በመንፈስ" ነው። በዚህ ጊዜ፡ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!"* ያለው፡ ያ፡ የጌታ ቃል መፈጸሙን እናረጋግጣለን።

ይህም ማለት፡ በጽላትና በታቦት ፊት፡ ወይም፡ በመንበር፥ በመቅደስ፥ በቤተ ክርስቲያን ሕንፃ፥ በመስቀል፥ ወይም በሥዕል አንጻር ኾነን በምንሰግድበት ጊዜ ኹሉ፡ ከድንግል ማርያም በመወለድ፡ ሰው ኾኖ ተገልጾ ያወቅነውን፥ በሕማማተ መስቀሉ፡ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ፥ ሞቶና ተቀብሮ፡ በትንሣኤው ያዳነንን፥ በመጨረሻም፡ "ብሉኝ! ጠጡኝ!" ብሎ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሰጠንን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን፡ በንስሓ ነጽተን በመቀበል፡ ከእርሱ ጋር እንድንዋሃድ ያደረገንን እግዚአብሔርን፡ "አምነንሃል! ወድደንሃል! ለዚህ ኹሉ ምሕረትህና ቸርነትህም እናመሰግንሃለን!" በማለት፡ መንፈሳዊዉንና እውነተኛውን አምልኳችንን እየፈጸምን መስገዳችን እንጂ፡ ለዚያ፡ በግዙፍነት ለሚታየውና ለሚዳሰሰው፥ እንደዛሬው ጊዜና እንደቀደሙት ዘመናት፡ በጠላት ዲያብሎስ አማካይነት፡ በከሃዲዎች እጅ፡ ወድቆ ሊረከስ፥ ሊበላሽና ሊፈራርስ ለሚችለው፥ ለመሬታዊው ግዑዝ አካል፥ ቅርፅ ወይም ምስል አይደለም። አለዚያማ፡ እንኳን ዛሬ፡ የኪዳነ መንፈስ ቅዱስን ሕይወት በወረስንበት፡ በዘመነ ምሕረት ይቅርና፡ ቀድሞ፡ በኪዳነ አሪቱ፡ የኵነኔ ዘመን ጊዜ እንኳ፡ በሰው እጅ የተሠራውን፡ *"የተቀረፀውን ምስል ላንተ አታድርግ! አትስገድላቸው! አታምልካቸውም! ...እኔ እግዚአብሔር አምላክህ፡ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።"* ያለውን ሕያው ቃሉን ማስተሓቀር፥ ከዚያም አልፎ መቃረን፥ ከኹሉም ይባስ፡ መተላለፍ ስለሚኾን፡ ራሳችን ጠፍተን፡ በክፉ አርአያነታችን፡ ሌሎችንም፡ ወደታላቁ ጥፋት መምራት ሊኾንብን አይደለምን? ስለዚህ፡ *አምልኮታችን፡ "መንፈሳዊነቱንና እውነተኛነቱን" እንዳይለቅ ለማድረግ፡* በብርቱ መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

## በታቦት የሚፈጸመው አምልኮ፡ "ባዕድ" እንዳይኾን ስለመጠንቀቅ!

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በተለይ፡ በመጨረሻው ኪዳነ ምሕረት አማካይነት፡ ከፈጣሪያችን፡ ከእግዚአብሔር ጋር የተጋባነው ቃል ኪዳን፡ እርሱን፡ ንጹሕና ትክክለኛ በኾነው፡ "በእውነትና በመንፈስ"፡ ይህም ማለት፡ እኛ፡ ወደእርሱ፡ "በእውነት" በምንቀርብበት ጊዜ፡ እርሱ ደግሞ፡ "በመንፈስ" ከእኛ ጋር በመዋሃድ ልናመልከው፥ እርሱም፡ በአምላክነቱ፡ ለእኛ የሚያስፈልገንን የአባትነት ቸርነቱን፥ ጥበቃውንና ትድግናውን ሊደርግልን መኾኑን ለአንዲት ቅጽበት እንኳ መዘንጋት የለብንም። ይህም ሲኾን፡ እርሱ፡ በቃል ኪዳኑ የታመነ፥ እኛ ግን፡ ለእርሱ ለገባነው ቃል ኪዳን የማንታመን ስሑታን በመኾናችን፡ ራሳችንን ዘወትር፡ በንስሓ እያስተካከልንና እያጸደቅን፡ ራሳችንን ለቃል ኪዳኑ ማብቃት እንዳለብን አውቀነው ሊኾን ይገባል። ያ፡ የቁጣው ቅጣት የሚመጣውም፡ ከዚህ ውጪ በምንኾንበት ጊዜ መኾኑን እንዳንረሳው ያስፈልጋል።

እንግዴህ፡ በሰላሙ ጊዜ ኾነ በዘመነ ዐጸባ (የጭንቅና የመከራ ዘመን)፡ ጽላትን የያዘው ታቦት በሚገኝበት ቤተ መቅደስ ኹሉ የምናካኼደው አምልኳችን፡ እንዲህ፡ "በመንፈስና በእውነት" ሊኾን አግባብ ነው፤ ሌላ ማማረጫ የለም። ወይም፡ ዘመኑ፡ እንደዛሬው ጊዜ፡ የመከራ መቅሠፍት የታዘዘበት፥ ዓመፀኞችና ከሃዲዎች፥ አመንዝሮችና አረመኔዎች የሠለጠኑበት ኾኖ፡ እንደሥርዓታችን፡ ጽላቱን የያዘው ታቦት፡ ሊገኝ የማይቻል የኾነ እንደኾነ፡ አምልኳችንን፡ በዘመኑ ኃጢአት ባልተባበረ ካህን አማካይነት፥ ወይም፡ ይህን የመሰለው ካህን በማይገኝበት ጊዜ፡ እውነተኛው ካህናችንና ሊቀ ካህናታችን የኾነውን፡ ራሱን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ካህናችን አድርገን፡ በማናቸውም ቦታ፥ ጊዜና ኹኔታ፡ ልናካኺድ የሚገባን፡ በዚሁ መልክ ነው። ከዚህ ያለፈ ወይም የተለየ እምነት ወይም ሥርዓት ቢኖር፡ እንደክህደት ወይም እንደባዕድ አምልኮ የሚቆጠር ይኾናል።

አባ ገብርኤል የሚባሉት ጳጳስ፡ "ክብረ ቅዱሳን" በተባለው ድርሰታቸው ውስጥ፡ ፀረ ማርያሞችን ለመቃወም ሲሉ፥ ወይም እነርሱ፡ ስለጽላትና ታቦት ያላቸውን የነቀፌታ አስተሳሰብ ለማክሸፍና ለማስተባበል ሲሉ፡ በተለይ፡ "ክብረ ታቦት" በሚለው ምዕራፍ ሥር፡ ከብሉያቱ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ የጠቃቀሷቸው ቃላት፡ ዓላማቸውን የሳቱ በመኾኑ፡ ተገቢው እርማትና መስተካከል ይደረግባቸው ዘንድ፡ በዚህ አጋጣሚ ላሳስብ እወድዳለሁ። ይኸውም፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ፡ ስለጽላትና ታቦት እንደተብራራውና እኛም ኢትዮጵያውያን፡ እስከዘመነ ክርስትና ድረስ ስናደርገው እንደቆየነው ኹሉ፡ እነዚያ ጥቅሶች፡ በቀጥታ የሚመለከቱት፡ እስራኤል፡ እርሱን አምላካቸውን፡ እንዲያመልኩባት፡ በዘመነ ብሉይ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች ተጽፋ፡ ለሙሴ የተሰጠችውን፡ አንዲቱን መለኮታዊት ጽላተ ኪዳን ብቻ እንጂ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ ይልቁንም በዛሬው ጊዜ፡ ሰዎች፡ በያለበት፡ በእየጃቸው፡ በብዛት እየቀረጹና በየቤታቸው እያስቀመጡ፡ እስከመሸጥ፥ መለወጥ፥ መሠረቅና መዘባበቻ እስከመኾን የደረሰውን ጽላትና ታቦት ባለመኾኑ፡ የጥቅሶቹ አቀራረብ፡ ለማንኛቸው ሊኾን እንደሚገባ ለይቶ በማስገንዘብ፡ "ሊታረምና ሊስተካከል ያስፈልጋል" ያልኩት ስለዚህ ነው።

ቅዱሱ ኪዳን፡ "እኔ አምላክህ፡ ቀናተኛ ነኝና፡ በአምልኮትህ ፍጹም ኹን!" የሚል፡ ግልጽና ቀጥተኛ፥ የጸናም መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ ያለበት በሚኾኑ፡ ይህ የአምልኳችን ጉዳይ፡ በብርቱ ሊታሰብበት እንጂ፡ ቸል ተብሎ ሊታለፍ የሚገባ አይደለም:: ምእመናንም፡ የሃይማኖታቸው መሠረት ነውና፡ በግልጽ አውቀውትና በትክክል ተረድተውት፡ በምግባር ሊፈጽሙት ይገባል:: ስለዚህ፡ ጽላትን ወይም ታቦትን በሚመለከት፡ እዚህ ላይ በአጽንዖት ማሳወቅ የምፈልገው፡ በዘመነ ብሉይ በነበረችውና በሙሴ እጅ በተሰጠችው፥ "ታቦተ ሕጉ" ወይም "የኪዳኑ ታቦት" በተባለችውም፡ በዚችው፡ በአንዲቷ ጽላተ ኪዳን ላይ የተቀረጸው፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ቃል ስለኾነ፡ ራሷ ጽላቷ፡ ከነታቦቷ ትመለክ ነበር:: በአዲሱ ኪዳን ጽላትና ታቦት የሚፈጸመው፡ የሥጋ ወደሙ አምልኮት ግን፡ እንዲህ አይደለም፤ ይህ፡ የአዲሱ ኪዳን አምልኮት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለድ፡ ሰው የኾነውና ኢየሱስ ክርስቶስ የተባለው፡ ያ፡ እግዚአብሔር ቃል፡ ሕያው ኾኖ፡ ዛሬ የሚመለከው "በመንፈስና በእውነት" ነው፤ ማለትም፡ ሥጋውና ደሙ በተቀመጠበት፡ በአዲስ ኪዳኑ ታቦት ፊት፡ እኛ፡ በእውነት ስንቀርብ፥ እርሱ ደግሞ፡ በዚያ ላይ፡ በቅዱስ መንፈሱ ተገልጾ፡ አምልኳችንን ይቀበላል::

እንዲህ፡ በእውነት የምናቀርብለትን አምልኳችንን፡ በመንፈስ መቀበልን የሚወድደው አምላካችን፡ በጽላቱና በታቦቱ፥ በሥጋ ወደሙም ላይ ተገኝቶ፡ መለኮታዊ ምስጢሩን የሚያከናውነው፡ በመንፈስ ቅዱስ መኾኑን፡ በቁርባን ጊዜ፡ በእርግጥ ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉት፡ ከካህናቱም ኾነ ከምእመናኑም ወገኖች፡ የበቁት ብቻ በመኾናቸው ይታወቃል:: "የበቁት" ማለትም፡ በንስሓቸው፡ "እውነተኞች" ኾነው የቀረቡት ማለት ነው፤ ለእነርሱ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተለወጠው፡ የመለኮት ሥጋና ደም ይሰጣቸዋል:: በ"እውነተኛነት"፡ ወይም፡ በ"እውነተኛ ንስሓ" ያልቀረቡት ግን፡ ካህናቱም ኾኑ ምእመናኑ፡ የኀረሱት፡ ምድራዊዉን የኅብስት ቁራሽ፥ የተኀነጩትም፡ ምድራዊዉን የወይን ጭማቂ እንጂ፡ መንፈሳዊዉንና ሰማያዊዉን አይደለም፤ እነዚህ፡ በ"እውነት" ባለመቅረባቸው፡ "ስላልበቁ"፡ በምሥጢረ ቁርባን ትርጓሜ እንደሚታተተው፡ መንፈሳዊው ሥጋ ወደሙ፡ ከእነርሱ ተወስዶ፡ በዚያው ቤተ ክርስቲያን ላሉት፡ ወይም በበረሃ ለሚኖሩት፥ በ"እውነተኛነታቸው "ለበቁት" ይሰጣቸዋል ማለት ነው::

እውነቱ ይህ ኾኖ ሣለ፡ የአባ ገብርኤል የጽሑፍ አቀራረብ፡ በሰዎች ሥርዓት፡ ጽላቱን ባርኮ፡ ለጽላትነት የሚያበቃው፡ መቼም ጳጳስ ነውና፡ ከጽላቱ ይልቅ፡ "ጽላቱን የሚባርከው ጳጳስ፡ ሊከብር ይገባል" ለማሰኘት፡ የተቃጣ ሙከራ ይመስላል:: አዎን! ራሱ እግዚአብሔር፡ በእጁ ጽፎ፡ በመለኮታዊ ኃይሉ ለቀደሳትና ራሱ፡ የእግዚአብሔር ቃል ኾና ትመለክ ለነበረችው ጽላተ ኪዳን፡ የተሰጠውን አምላካዊ ክብር፡ በሰው እጅ ተቀርጾና ተባርኮ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ለቅዱስ ቁርባን መሠዊያነት ለሚበቃው፡ የአዲስ ኪዳኑ ጽላት አሳልፎ መስጠት፡ ራስን፡ ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከል፡ "ከጽላቱ ይልቅ፡ ጽላቱን የምንባርከውን፡ እኛን፡ ጳጳሳቱን፡ አምልኩን!"፥ ግብፃውያን ጳጳሳት፡ ትተውልን የኼዱትንም የሃይማኖት ቀምበር፡ "እንደተሸከማችሁ ቀጥሉ!" እንደማለት ይቆጠራል::

በዚህም፡ *"እናንተ፡ በመጻሕፍት፡ የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም፡ ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው:: ነገር ግን፡ ሕይወት እንዲኾንላችሁ፡ ወደእኔ ልትመጡ አትወድዱም:: እኔ፡ ከሰው፡ ክብርን አልቀበልም፤ ዳሩ ግን፡ የእግዚአብሔር ፍቅር፡ በራሳችሁ እንደሌላችሁ አውቃችኋል::*

*"እኔ፡ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፤ አልተቀበላችሁኝምም፤ ሌላው፡ በራሱ ስም ቢመጣ፡ እርሱን ትቀበሉታላችሁ፡፡ እናንተ! እርስ በርሳችሁ፡ ክብርን የምትቀባበሉ! ከአንዱም፡ ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ! እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?"* የሚለው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል መድረሱን እንመለከታለን፡፡

## ኢትዮጵያ፡ በጽላትና ታቦት ላይ ስለሚፈጸመው በደል ስትፋረድ!

በዘመነ ብሉይ የነበረውና በዘመነ ሐዲስ ያለው የጽላትና የታቦት ምሥጢርና ሥርዓት ይህ ኾኖ ሣለ፡ በዚሁ፡ እጅግ በተቀደሰው፡ የአምልኮ ንዋየ ቅድሳት ላይ፡ በየዘመናቱ የደረሰውን፥ በተለይም፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በግለሰብ፥ በኅብረተሰብና ባገር ደረጃ እየተፈጸመ ያለውን ታላቅ በደል፡ ማንኛውም ሰብአዊ ተመልካች፡ በቅርብ የሚያውቀው ስለኾነ፡ በዝርዝር ማብራራቱ ባያስፈልግም፡ እዚህ ላይ፡ መጠነኛ ሐተታን ሰጥቶ ማለፉ አግባብ ይኾናል፡፡

አዎን! ይህን የተነሣንበትን፡ የጽላትን ወይም የታቦትን ምሥጢር በሚመለከት፡ እጅግ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ነገር ቢኖር፡ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንደዚያ፡ እስከመስቀል ሞት በደረሰ ሥቃይ፡ መከራውን አይቶ፡ በደሙ ተቤዥቶ፡ ከአሪታዊው ቀምበር ነጻ ያወጣትን፥ ከእኛም እንድትቀርብለት የሚፈልጋትን፡ ንጹሕና እውነተኛ የኾነችውን፡ መንፈሳዊት አምልኮውን፡ እንደገና ወደውርደት መልሰን፡ ለዲያብሎስና ለአገልጋዮቹ መዘበቻና መጫወቻ፥ መጠቀሚያም ማድረጋችን ነው፡፡ ይኸውም፡ በአሁኑ ጊዜ፡ ዲያብሎስ፡ በጽላት ላይ፡ በአዋጅ ባስተላለፈው ዘመቻ ምክንያት፡ በይፋና በብዛት እየደረሰ በሚታየው ድርጊት ተረጋግጦ ይታወቃል፡፡

በዚህ ረገድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ያገኘነውና ይኸው፡ "ጽላት" ወይም "ታቦት" የሚባለው፡ አንዱ፡ የተቀደሰው ቅርሳችን፡ የገጠመው አሠቃቂ ዕድል፡ በሥርቆትና በሽያጭ አበጋዞች አማካይነት፡ የነጋዴ መጠቀሚያ በመኾን ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከእርሱም በኋላ፡ የእርሱ ፍቅር አገብሮአቸው፡ ለተጋደሉላትና ለተሠዉላት፥ በአምልኮቷም፡ ንጽሕት ለኾነችው፡ ለቅዱሱ ኪዳን የተዋህዶ ሃይማኖታችን፡ አንደኛው መታወቂያ ኾኖ የኖረው፡ ይህ፡ የተቀደሰ ምልክታችን፡ በተቃዋሚዎቻችንና በአረማውያን ዘንድ ሳይቀር፡ በሕዝብ አደባባዮችና በግል መኖሪያ ቤቶች ውስጥ፡ ለትርኢት እየቀረበ፡ እንዲህ መሣቂያና መሣለቂያ፥ መጫወቻና መዘባበቻ በመኾን ጭምር፡ በርኵሰት ሲቀለድበት እናያለን፡፡ በዚህ ጊዜም፡ ከኢትዮጵያውያን መካከል፡ በድርጊቱ፡ አብረው እየሣቁና እየተሣለቁ፥ እየተጫወቱና እየዘበቱ፡ ቢበዛ ከንፈራቸውን ሲመጥጡ፥ ሌሎቹ ደግሞ፡ "አዬ ጉድ!" እያሉ፡ ዝም ብለው፡ በምናለብኝነት ይመለከታሉ፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ ራሱን፡ "እኔ ኢትዮጵያዊ ምእመን ወይም ካህን ወይም ጳጳስ ነኝ" ብሎ በማስተዋወቅ፡ በተለይም፡ በስደት ስም፡ በባዕዳን አህጉር በሚኖሩ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ መካከል በሚገኝ፡ በማንኛውም ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት እጅ፡ "ጽላት" እየተባለ፡ በሚቀርብበት ጊዜ፡ ከዋናዋ ቤተ ክህነት አለመሰጠቱ እየታወቀ፡ በሥርዓተ አልበኝነት የሚፈጸመው የአምልኮ ፌዝና ቀልድ እጅግ ያሳዝናል፡፡

እንዲሁም፡ በቃለ አዋዲው ደንብ መሠረት፡ የቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ሊቀ መንበር፡ ሥልጣነ ክህነት ያለው ቄስ ሊኾን ሲገባ፡ እንኳንስ ሥጋ ወደሙ የተቀበሉ ሊኾኑ ይቅርና፡ ምእመንነታቸው እንኳ ተረጋግጦ የማይታወቅ፥ አቋሙና ምግባሩም የሌላቸው፡ ወንዶችና ሴቶች ግለሰቦች፡ የአመራሩ ምርፋቅ (የBoard ቦርድ) ሰብሳቢና አባሎች እየተባባሉ በመመራረጥ፡ የአስተዳደር ሥልጣን በመያዛቸው፡ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ላይ የሚፈጸመው አሳፋሪና የድፍረት ድርጊት፡ ሃይማኖቱን ብቻ ሳይኾን፡ ራሱን፡ ኢትዮጵያዊነትን፡ በባዕዳን ዘንድ ጭምር፡ ከከፍተኛ ቅሌትና ትዝብት ላይ በመጣል፡ አጠያያቂ እንዲኾን አድርጎታል።

ከኹሉ ይልቅ የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው፡ ኢትዮጵያን፡ ለማፈራረስና ለማውደም፡ በሙሉ ኃይላቸው የተነሡት፡ ባዕዳንና የወገን ተፃራሪዎች፡ በጽላትና በታቦት ላይ እያካኼዱ ያሉት ግዙፍና ረቂቅ ዘመቻ አንሶ፡ ራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያውያን ነን" የሚሉት ሰዎች፡ በተለይ በአገር ውስጥ፡ የሚፈጽሙት የርኩሰት ድርጊት ነው። ይህም፡ ካህናቱ፡ እርስ በርሳቸው በሚጣሉበት ጊዜ፡ አንደኛው፡ ሌላውን ለመጉዳት ሲል፡ ለዲያብሎስ ሴራ መሣሪያ በመኾን፡ ጽላቱን ራሱ ይሠርቅና፡ "ጽላቱ ጠፋ!" ብሎ፡ በምእመናኑ ዘንድ በሚነዛው ወሬ ይጀመራል። ከዚያ፡ ምእመናኑ፡ "ጽላቱ ከጠፋ፡ እንግዴህ፡ አምላካችንን፡ በምንና እንዴት ልናመልከው ነው?" ብለው፡ እንዲደናገጡና እንዲሸበሩ በማነሣሣት፡ እነርሱን፡ ከመጨረሻው የተስፋ መቁረጥ ደረጃ አድርሶ፡ የሚቀጥለውን ኃጢአት ያሠራቸዋል። ይኸውም፡ ይህን ለመሰለው፡ የዲያብሎስ የርኩሰት ተግባር መሣሪያ የኾነው፡ ሌላው ካህን፡ ከምእመናኑ መካከል፡ ለዚህ ሰይጣናዊ ተልእኮ በተዘጋጁ ግለሰቦች ተባባሪነት፡ ጽላቱን የሠረቀው ማን እንደኾነ ለማወቅ ወደጠንቋይ ኼዶ መጠየቁ ነው። በዚህም፡ ዲያብሎስ፡ ባሮቹ ሊያደርጋቸው ባጠመደው ወጥመዱ ውስጥ፡ ኹሉም እንደገቡለት ይታያል።

ተከታትሎ ስለሚደርሰው ኹኔታ ግን፡ ከዚህ አልፌ ማተቱ ስለሚጨንቀኝና ስለሚዘገንነኝ፡ ነገሩን፡ እዚሁ ላይ አቆመዋለሁ። በዚህ ድርጊት፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና ቅድስት እናቱን፡ ድንግል ማርያምን፡ ምን እንደሚሰማቸው፥ ምንስ እንደሚሉ መገመቱንማ፡ ለማሰብ መሞከሩ እንኳ አይቻለኝምና፡ እተወዋለሁ!

በዚህ ጊዜ ነው፡ እስራኤል፡ የኃጢአታቸው ብዛትና የበደላቸው ጽናት፡ ታቦተ ጽዮንን፡ በዚያን ጊዜ፡ አረማውያን በነበሩት፡ በፍልስጥኤማውያን እጅ፡ እስከመማረክ ያደርሳት የነበረው ዘግናኝ ታሪክ፡ በዓይነ ሕሊና ፊት፡ እንደመጽሔት ድቅን እያለ፡ የጥንቱን በማዘከር፡ ኢትዮጵያዊዉን መንፈስ፡ በታላቅ የኀዘን ማዕበል የሚያማታው።

የቅርቡን፡ የደርግ የግፍ አገዛዝና አሁን ያለንበትን የበቀል አመራር፥ እንዲሁም፡ ለወደፊት የሚጠብቀንን አስፈሪ ጽዋ፡ ለጊዜው እናቆያቸውና፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ጥቂት ራቅ ባሉት፡ በዮዲት፥ በአሕመድ ግራኝና በፋሺስቱ ሙሶሎኒ የጭካኔ ወረራዎች ጊዜ፡ የተቀበላቸውን መከራዎች፡ እስቲ እንደገና እናስታውሳቸው! "እኒያ፡ እልቂት የተመላባቸው የመቅሠፍት ጊዜያት፡ የእግዚአብሔር፡ የቃል ኪዳን አገር የኾነችውን ኢትዮጵያን እንዲያጥለቀልቁ ለምን፡ ከአምላክ ተፈቅዶ ታዘዘ?" ብለን በግድ መጠየቅና መልሱን ለማግኘት መሞከር ይኖርብናል። ለሃይማኖታዊ ሰውነት፡ ወይም ለኢትዮጵያዊ፡ በተለይም፡ በዕድሜአችን ደርሶ ያየነውን ለምንገመግም፡ ለእኛ፡ መልሱ ይህን ያህል ከባድ አይኾንም።

ይኸውም: ይህን የመሰለው መቅሠፍት: በአንድ ሕዝብ ላይ፥ ያውም ከፈጣሪው ጋር በቃል ኪዳን በተሣሠረ: እንደኢትዮጵያውያን ባለ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው: የዚያ ሕዝብ: የኃጢአት ጽዋ መልቶ ሲፈስስ ብቻ መኾኑ: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ከጥንት ጀምሮ የታመነበት ስለኾነ ነው::

የጭካኔን ሠይፍ የታጠቁት: እኒያ የጥፋት አበጋዞች ምን አደረጉ? የሚፈርሰውን አፍርሰው፥ የሚጠፋውንም አጥፍተው: ከፈጸሙ በኋላ: በመጨረሻ: ራሳቸው ጠፉ እንጂ: ዕድሜ አግኝተው: በገዢነት ሥልጣን: በኢትዮጵያ አልቀዩም:: የመጡት: ለሌላ ሳይኾን: በቀጥታ የቅጣት ተልእኮን ለማድረስ ብቻ መኾኑ: በዚህ ይታወቃል:: በተለይም: የፈራረሱትና የተደመሰሱት: በይበልጥ: የአምልኮ ምልክቶች የኾኑት: ሐውልቶችና አብያተ ክርስቲያን በመኾናቸው: ጽዋው መልቶ: የቅጣቱ መሣሪያዎች የኾኑትን ልኡካን እንዲመጡ ያደረገው ኃጢአት: ከአምልኮ በደል ጋር የተያያዘ መኾን እንዳለበት: በግልጽ ያታያል:: እስራኤል: በታቦተ ጽዮን አማካይነት: ከፈጣሪያቸው ጋር ያደረጉትን: የአምልኮ ቃል ኪዳናቸውን አፍርሰው: በእርሷ ሊፈጽሙት የሚገባቸውን የአምልኮ ሥርዓት በሚያቃውሱበት ጊዜ፥ወይም ጣዖት ማምለክ: ወይም በአጋንንት አምልኮ መዘፈቅ በሚጀምሩበት ጊዜያት ኹሉ: እግዚአብሔር: በአካባቢያቸው: ለእነርሱ መቅጫ ያኖራቸውን አሕዛብ እያስነሣ: ይቀጣቸው እንደነበረው ማለት ነው::

ስለዚህ: በእነዚያ ጊዜያት የነበረውም: የኢትዮጵያውያን ኃጢአት: አምልኮን የሚመለከት እንደነበረ: ጥርጥር የለበትም:: ታዲያ! ያ ኹሉ መፈራረስና ጥፋት የደረሰው: በጊዜአችን ሲፈጸም እንደምናየው: በእነዚያ ዘመናት የነበሩት ትውልዶች: ኃጢአታቸው: ከሌላው ጋር ተደማምሮ: የአምልኮ ምልክቶቻችን በኾኑት: በጽላትና በታቦት፥ እንዲሁም: በቀሩት: የቅዱሱ ኪዳን ቅርሶቻችን ላይ ከፈጸሙት: የክህደት: ወይም የዓመፅ: ወይም የአመንዝራነት በደል የተነሣ ካልኾነ በቀር: በሌላ: በምን ሊኾን ከቶ ይችላል?

በእነዚያ የመከራ ዘመናት: ሐውልቶቹ እየወደቁ እንዲሠባበሩ፥ አብያተ ክርስቲያኑም: ከነንዋያት ቅድሳቶቻቸውና መጻሕፍቶቻቸው ጋር እየተኰሰተሩ እንዲቃጠሉ፥ የቤተ ክህነቱ፥ የቤተ ሕዝቡና የቤተ ምልክናው ወገኖች የኾኑት ካህናት፥ ምእመናንና መኳንንት በሰይፍ ስለት እንዲያልቁ፥ እንዲሠቃዩና እንዲሳደዱ በተደረገባቸው ጊዜያት: በጽላታቱም ላይ ይኸው ተመሳሳይ ዕድል: አብሮ ደርሶ እንደነበረ የታወቀ ነው:: ከእሳቱ ቃጠሎ ለማዳን በተደረገው ሙከራ: የተረፉ ጽላቶች ቢኖሩም እንኳ: በየዋሻው ተጥለው ከመቅረታቸው በቀር: ከጥፋቱ ጉዳት እንዳላመለጡ: በየጊዜው የሚከሠቱት የቅርሶች ግኝቶች፥ በየዋሻውና በየገደላገደሉ ላይ ተሠርተው የሚገኙትም: የዛሬዎቹ አብያተ ክርስቲያን በዋቢነት ያስረዳሉ::

ታዲያ: የጽላታቱ አምልኮ ፍጻሜ: ይህን በመሰለ ውጤት የሚያበቃ ከኾነ: የአዲስ ኪዳኑ አምልኮተ እግዚአብሔር: በኢትዮጵያውያን ዘንድ: በበለጠ ተጠናክሮ: እንዴት ሊቀጥል ቻለ? ማለትም: እውነተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር: በሥርዓተ ክርስትና: እንደሥርዓተ ኦሪቱ ሳይኾን: እንደአዲስ ኪዳኑ: ያለጽላት ሊካኼድ: እንዴት የሚቻል ኾነ?

## ኢትዮጵያ፡

ለፈጣሪያችን፡ ምስጋና ይድረሰውና፡ በዘመነ ኦሪት፡ በጽላተ ሙሴ ይመለክ የነበረው፡ እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ቃል፡ በኋለኛው ዘመን፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾኖና ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፡ በመስቀል ላይ በመሠዋት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንዲወርድ ካደረገ በኋላ፡ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!"* ብሎ፡ ገና በሕይወተ ሥጋ ሣለ፡ ለሳምራዊቷ ሴት የተናገረውን ቃሉን፡ በደሙ ባተመው በአዲሱ ኪዳን፡ በምግባር እንፈጽመው ዘንድ፡ ጸጋውንና ሥልጣኑን ስለሰጠን፡ ጽላት ሊኖር በማይቻልበት ጊዜ፡ አምልኳችንን፡ ያለጽላት ለመቀጠል እንድንችል አደረገ! አዎን! አምላካችን፡ ይህን ጸጋና ሥልጣን፡ ለመላው የሰው ልጆች፡ በተለይም፡ የቅዱስ ኪዳኑን ቅርስ ለምንጠብቅለት፡ ለእኛ ኢትዮጵያውያን የሰጠን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ደመኛ ተቃዋሚና የዘር ጠላት የኾነው ዲያብሎስ፡ በአገልጋዮቹ መሣሪያነት፡ ከላይ የተገለጸውን በመሰለ ጭካኔ፡ በጽላትና ታቦት፥ በሌሎቹም የአምልኮ ንዋያት ቅድሳት ላይ፡ ጥፋት ከማድረስ የማይመለስ፡ ኃይለኛ ባላጋራ መኾኑን በማወቁ እንደኾነ ለመረዳት፡ ለማንም ሃይማኖተኛ አያዳግተውም።

እንግዲህ፡ በእነዚያ የመከራ ዘመናት የነበሩት፡ የኢትዮጵያ ትውልዶች፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ በጽላትና በሌሎቹ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምልክቶቻችን ላይ የነበራቸው፡ የአምልኮ እምነትና ሥርዓት፡ መምህራችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከነገረን ቃል ውጭ ኾኖ ከተገኘ፡ በእያንዳንዳቸው ላይ የደረሰው፡ ያ፡ የቅጣት መቅሠፍት፡ ሊያስደንቅ፥ ሊያጠያይቅም አይችልም።

ምክንያቱም፡ በዚህ ረገድ የሚፈጸመው ኃጢአት፡ ጽዋው ሲመላ፡ የሚያስከትለው ፍዳ፡ ይህን ለመሰለው፡ ለማይቀረው፡ አጠቃላይ ጥፋትና ውድቀት የሚዳርግ በመኾኑ ነው። በተከታታይ የተተኩት ትውልዶችም፡ ከእነርሱ በፊት ስለደረሱት መቅሠፍታዊ ቅጣት፡ በዝርዝር አጥንተውና በማስተዋል ተመልክተው፡ ካለፈው በመማር፡ ስሕተታቸውን አርመውና የአምልኮ ምግባራቸውን አስተካክለው ባለመገኘታቸው፡ ያው ኃጢአትና በደል ቀጥሎ፡ የቅጣቱ መቅሠፍት፡ በተጠቀሱት ትውልዶች ላይ ብቻ ሳይኾን፡ ይኸው፡ ከእኛም ዘመን ደርሰና ተከሥቶ እናየዋለን።

"ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!" በሚለውና በዚህ፡ በኹለቱም መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግሞ እንደተመለከተው፡ ይህ ትውልድ፡ በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት፡ ከፈጣሪው፡ በቃል ኪዳን በተቀበላቸው፡ ጽላቱንና ታቦቱን፥ እንዲሁም፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተሰጠውን፡ *"ምአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለውን፡ የዘውድና የመንበረ ዳዊቱን ዙፋን በመሳሰሉት፡ የአምልኮ ምልክቶቻችን ላይ በፈጸመውና አሁንም እየቀጠለ በኼደው፡ የክህደትና የዓመፅ ኃጢአቱ ምክንያት፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ እየቀራረጠው ያለውን የቅጣት ሠይፍ፡ ወደአፎቱ እንዲመለስ ለማድረግ፡ ከዚሁ በደሉ፡ ንስሓ የመግባት ዝንባሌን ሊያሳይ ስላልቻለ፡ እነሆ፡ ለባሰው የጭካኔ ክንድ ሊዳረግ፡ እየተዘጋጀ መኾኑን፡ በገሃድ እንመለከታለን። ከዚህ መቅሠፍታዊ እልቂት ለማምለጥ፡ የሚሰማ ጆሮ ያለው ኹሉ፡ ራሱን በንስሐና በቁርባን አዘጋጅቶ መገኘት ይኖርበታል።

## እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡
## ራሱ፡ ጽላትና ታቦት የመኾኑ ምሥጢር።

ቀደም ብለው በተጠቀሱት፡ በእነዚያ የመከራ ዘመናት፡ የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን አምላክ በኾነው፡ በእግዚአብሔር አምልኮት ላይ፡ ያን የመሰለው፡ እጅግ አሠቃቂ፥ አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታ እንዲደርስ ያደረገው፡ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!"* የሚለውን መለኮታዊ ሥርዓት በመቃረን፡ "ጽላት"፡ ማለትም፡ "ጽላትን የያዘው ታቦት"፡ በተለያየ ችግር ምክንያት፡ ሊገኝ ያልተቻለ እንደኾነ፡ ሥልጣነ ክህነት ያለው ካህን ቢኖርም እንኳ፡ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ሊፈጸም እንደማይፈቀድ ተደርጎ ከተሠራው የሰዎች ሥርዓት የተነሣ መኾኑን መገንዘብ ይገባል። ይህን ሥርዓት ለሠሩትም፡ *"ይህ ሕዝብ፡ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን፡ ከእኔ፡ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የኾነ ትምህርት እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል"* የሚለው የእግዚአብሔር ቃል፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና ሊጠቀስላቸው አግባብ ይኾናል።

በኢየሱስ ክርስቶስ የጸደቀውና ከላይ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው እውነተኛው፡ የአዲስ ኪዳኑ፡ የጽላት ሥርዓታችንም ቢኾን፡ የሠመረ ኾኖ፡ በትክክል ተፈጻሚነት የሚኖረው፡ ዘመኑ፡ የሃይማኖት ዕረፍት የተገኘበት ሰላም ሲኾን ነው እንጂ፡ አለዚያ፡ ዛሬ ያለንበትን የመሰለ፡ ክህደትና ዓመፅ፥ አመንዝራነትም የሠለጠነበት ዘመን በሚመጣበት ወቅት፡ በተግባር ሊፈጸም እንደማይችል፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በእየራሳችን የክህነት አገልግሎት ላይ እየደረሰ የምናየው ችግር አረጋግጦልናል።

ጽላት ወይም ታቦት ሊኖር ባልቻለበት፥ እኔ ራሴ፡ በደርግ እሥር ቤት፥ ከዚያም፡ በአገሬና በባዕድ አህጉር፡ በግዞትና በስደት የኑሮ ኹኔታ ላይ ሣለሁ፡ ሥጋ ወደሙን እንደተቀበልሁ ሆኜ እንድገኝ ያደረገኝን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ቸርነት፡ እዚህ ላይ፡ በምስክርነትና በምሳሌነት ልጠቅሰው እወድዳለሁ። አዎን! መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለዚያች፡ ውኃ ልትቀዳ ለመጣች ሳምራዊት ሴት፡ *"እስመ እግዚአብሔር መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ ወበጽድቅ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ"* ማለትም፡ *"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት፡ ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል"* ሲል ከተናገረው ቃሉ የተነሣ፡ ያ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ቸርነት፡ ለእኔ ስለተደረገልኝ፡ በሰባት ዓመታት የእሥር ቤት ሕይወቴ ውስጥ፡ ራሴን፡ በየዘወትሩ ዕለታት ሳይቀር፡ ሥጋ ወደሙን እንደተቀበልኩ አድርጌ እንድቆጥረው አስችሎኛል። ይህንኑም፡ በየጊዜያቱና በያጋጣሚው፡ በአንደበቴ መናገር ብቻ ሳይኾን፡ በጽሑፍም ሳሠፍረው እንደቆየሁ፡ ዛሬም በአጽንዖት እገልጸዋለሁ።

እንደእኔ፡ በእሥር፥ በግዞትና በስደት፥ ወይም፡ ክህደት በሠለጠነበት፡ ይህን፡ የዛሬውን በመሰለ ዘመን የሚኖር እውነተኛ ምእመን፡ ቤተ ክርስቲያን በሌለበትና ካህን በሚታጣበት፡ አስቸጋሪ ኹኔታ ላይ ሲኾን፥ ወይም፡ በቤተ ክርስቲያን መገኘት የማይችልበትና ከዓቅሙ በላይ የኾነ፡ ጽኑ ችግር በሚያጋጥመው ጊዜ ኹሉ፡ ከላይ በተጠቀሰውና በሌሎቹ ተመሳሳይ የጌታ ቃላት መሠረት፡ ራሱን ጽላትና ታቦት፥ መንበርና መቅደስ፥ እንዲሁም፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና እናቱን ድንግል ማርያምን፡ ካህንና መሥዋዕት በማድረግ፡ "በመንፈስና በእውነት"፡ ሥጋ ወደሙ እንደተቀበለ ይኾንለታል።[፳፩]

ይህን፡ የእኔን የመሰለውን እሥራትና ስደት ላላዩ፡ ይህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ቸርነት፡ ምንም ዓይነት ስሜት ሊሰጣቸው፡ ምናልባት አይችል ይኾናል። እውነተኛው ዳኛ ልዑል እግዚአብሔር፡ ለእኒህና እነርሱን ለመሰሉት ተጠራጣሪዎች፡ ይህ፡ በእኔ የደረሰው መከራና የመንፈስ ቅዱስ ትድግና፡ አብነት ኾኖ፡ ሊያስተምራቸው ካልቻለ፡ ተጨማሪ ትምህርት የሚኾናቸውን፡ ተገቢውን ፍርዱን፡ በጊዜው መስጠቱ ስለማይቀር፡ ያኔ ይገነዘቡታል ብዬ አምናለሁ። በቅዱሱ ኪዳን እውነተኛ አምልኳችን ጸንተን ለመኖር የቀረጥን ኢትዮጵያውያን ኹሉ፡ ከዚህ፡ ከዛሬውና ወደፊትም፡ ሊመጣ ከሚችለው፡ የአምልኮ ችግር ጠብቆ ያወጣን ዘንድ፡ የተሰጠን ብቸኛ መፍትሔ፡ የማያቋርጠው ምስጋናችን ይድረሰውና፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰፊ ልግሥናው፡ *"አምልኳችሁ፡ በእውነትና በመንፈስ ይኹን!"* ያለው፡ ይህ፡ የኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ ጸጋው ብቻ መኾኑን ስመሰክር፡ እጅግ ደስ ይለኛል።

ይህን እውነታ ለማጠናከር፡ ማለትም፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ ሴቶቹም፥ ወንዶቹም፡ እያንዳንዳችን፡ እየራሳችን፡ መንፈሳዊዉንና አማናዊዉን፡ የአዲስ ኪዳን ጽላት የያዘው፡ ታቦት የሚገኝበት፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ስለመኾናችን፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡ በመንፈስ ቅዱስ የጻፈውን እንመልከት! *"እናንተ፡ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ! ...እናንተ፡ የእግዚአብሔር ታቦቱ እንደኾናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም፡ በእናንተ ላይ አድሮ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም፡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ያፈርሰዋል። ...የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ እናንተ ናችሁ! የእግዚአብሔር ቤቱ፡ ቅዱስ ነውና፡ እንግዲያ፡ የእግዚአብሔር ቤት*[፳፱] *የኾነውን፡ ራሳችሁን አታርክሱ!"*

አሁንም፡ እንደገና፡ ለእግዚአብሔር ምስጋናችን ይድረሰውና፡ እንዲህ ባይኾን ኖሮ፡ በአሁኑ፡ የዓላውያን (የከሃዲዎች) ዘመን፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ ስለሚቀኑበት፡ ስለዚሁ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን አምልኳቸው፡ ከቶ ምን ይውጣቸው ነበር? እግዚአብሔር ወልድ፡ ዲያብሎስንና ከእርሱ የሚመነጩትን፡ የክፋት ኃይላት ኹሉ ደምስሶና ድል አድርጎ፡ በትንሣኤው ብርሃን የተነሣው፡ እኛን፡ የቃል ኪዳን ልጆቹን፡ ከሥጋዊቷ የአሪት የአምልኮ ቀምበር፡ ነጻ ሊያወጣንና የመንፈሳዊዉን የአምልኮ ጸጋ ሊያቀዳጀን፥ ከዚህም ክብራችን የተነሣ፡ ልጆቹ ኾነን፡ የዘለዓለም መንግሥቱን እንድንወርስለት አይደለምን? እንዲህ ካልኾነማ፡ ታዲያ፡ ለሌላ፡ "ለምንድር ነው?" ዲያብሎስ፡ ጽላትንና የዚያ መያዣ ሣጥን የኾነውን ታቦት፡ ምክንያት አድርጎ፡ ንጹሒቱን የእግዚአብሔር የአምልኮ ሥርዓታችንን፡ በተለመደ ተንኮሉ በማበላሸት፡ የመለኮትን፡ የተቀደሰ ስም፡ በአረማውያንና በአሕዛብ፥ በሃይማኖት ተቃዋሚዎቻችንም ዘንድ፡ "እንዲረክስ ለማድረግ ነው!" ሊባል ነውን?

ይህ ከኾነማ፡ እንኳንስ፡ ያን ያህል የመሥዋዕትነት ዋጋ የከፈለልንን፡ እርሱን፡ የቃል ኪዳን አምላካችንን ይቅርና፡ ለዚያ ቤዛነቱ፡ ምንም ዓይነት አስተዋጽዖ ያላደረገነውን፡ እኛን ምስኪኖቹን እንኳን፡ የቱን ያህል ባሳዘነን? በውኑ፡ ወሰን የሌለውን፡ ይህን፡ የፈጣሪያችንን ቸርነትና ጸጋ፡ ዋጋቢስ ልናደርገው ይገባልን? በምድራዊው አኗኗርና በሥጋዊው አስተዳደር እንኳ፡ በገንዘብ ተገዝቶ ሐርነት (ነፃ) የወጣ ባርያ፡ ወደባርነቱ ሊመለስ ይላልን? አይልም፤ የመገዛት ዝንባሌ ያለው፡ ሰነፍና ልበቢስ ካልኾነ በስተቀር፡ ወደባርነቱ ሊመለስ አይልም።

እኛም ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ፡ በመለኮታዊ ቤዛነት፡ ነጻ ከወጣን በኋላ፡ ከፈጣሪያችንና ከቃሉ በልጠው፡ በላያችን ሠልጥነውብን የነበሩት ግብፃውያንና የራሳችን ሰዎች ተመሣጥረው፡ የሃይማኖት ሥልጣናቸውንና ሰብአዊ ግዛታቸውን፡ ለማጽናት ሲሉ፡ ያወጡት ሰብአዊ ሥርዓት፡ እንዲጸናብን ካደረግን፡ "ዐም ሐራ" ወይም "ነጻ ሕዝብ"፥ ወይም፡ "ክርስቲያን"፥ ወይም "ኢትዮጵያዊ" የሚያሰኘን፡ መታወቂያና መለያ፥ መጠሪያም ስማችን፡ እንደሚያመለክተው፡ የእነዚያ፡ የእግዚአብሔር አምላኪዎችና የቃል ኪዳን ነጻ ሕዝቦች የተባሉት፡ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን ልጆች መኾናችን ቀርቶ፡ የመገዛት ዝንባሌ ያለውን፡ ያን፡ ሰነፍና ልበቢስ ባርያ መምሰላችን አይደለምን? በድል አድራጊነት፡ ከዲያብሎስ ገዢነትና ከኃጢአት ባርነት፥ ከእሪት ቀምበርና ከሞት ነጻ ያወጣንን፡ የአሸናፊውን አንበሳ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ ከንቱ ማድረጋችንስ አይደለምን? በዚህስ ጊዜ፡ ተፃራሪዎቻችን፡ "ጣዖት አምላኪዎች!" ሊሉን አይደለምን?

በዚህ ረገድ፡ የሰዎች ባህልና የእግዚአብሔር ሥርዓት የተለያዩ መኾናቸው ተከሥቶ የሚታይበትን፡ በአሁኑ ጊዜና በራሳችን አገር ውስጥ እየተካኼደ ያለውን፡ የመንፈሳውያን በዓላቶቻችንን አከባበር፡ በምሳሌነት እንመልከት! ይኸውም፡ ለክብረ በዓል ሲባል፡ እንደእሪቱ ሥርዓት፡ ታቦት ተሸክሞ የማውጣቱ ሰብአዊው ልማድ እንዲሰፍን የተደረገው፡ ለአምልኮተ ባዕድ ቅርብ በኾነው፡ በመኻልና በደቡቡ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሲኾን፡ መለኮታዊዉን ሥርዓት በተከተለው፡ በጥንታዊው፡ የሰሜኑ ክፍለ ሀገር ግን፡ ልማዱ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ እንዲስፋፋ ከመደረጉ በስተቀር፡ በበዓላት ጊዜ፡ በሥርዓት የሚወጣው፡ መስቀል ብቻ በመኾኑ ይታወቃል።

## ኢትዮጵያ፡
## ሌላ አሕመድ ግራኝ ቢነሣ፡ በጽላትና ታቦቱ ላይ ስለሚደርሰው ምስቅልቅል ስትፋረድ!

ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ በቃል ኪዳኒቱ የእግዚአብሔር አገር፡ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ፡ በእሳቶ ይሁዲት፥ በግራኝ አሕመድና በፋሺስቱ ሙሶሎኒ፡ የቅጣት መሣሪያነት የተፈጸመው፡ ያ፡ ጽኑ መቅሠፍት፡ ዛሬም፡ በዚህ፡ ከሃዲ፥ ዓመፀኛና አመንዝራ ትውልድ ላይ እየተካኼደ መኾኑን፥ ይህም ማለት፡ ትውልዱ፡ ከፈጣሪው ጋር የተጋባውን፡ የበኩሉን የቃል ኪዳን ግዳጅ ባለማክበሩ፡ ከሃይማኖት አልባው፡ የደርግ አገዛዝ ጀምሮ፡ በቁጣ ተመዝዞ እየመታ፡ በደም የታለለው ሠይፍ፡ ገና ወደአፎቱ ያልተመለሰና በበለጠ ጭካኔ፡ እንደገና ሊቀራርጥ፡ እንደተሠነዘረ የሚገኝ መኾኑን፡ በአራጁ ፊት፡ ለእርድ ተዘጋጅቶ እንደቆመው ፍሪዳ፡ ኹሉም፡ እነሆ ይመለከተዋል።

አምላከ ኢትዮጵያ አያድርገውና፥ አሁን፡ ኹሉም ነገር እየተመቻቸለትና እርሱም እየተሰናዳ ያለው፡ ያ፡ የአሕመድ ግራኝን የሚመስለውን ሃይማኖታዊ ሠይፍ፡ የታጠቀው የቅጣት ኃይል፡ እንደእግዚአብሔር-አልባው የደርግ አገዛዝ፡ ምናልባት፡ እርሱም፡ የነደፈው ዕቅድ ተሳክቶለት፡ ብሔራዊዉንና መንግሥታዊዉን ሥልጣን ለመጨበጥ ቢችል፡ ይህን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንን፡ አጽንተን ለመቀጠል የምንችለው፡ እንዴት ነው?

ይህ አሳዛኝ ፍጻሜ ከመድረሱ በፊት፡ "የአምልኮ ሥርዓታችንን፡ ዛሬ፡ እንደፈለግነው በማካኼድ ላይ ነን" እያልን፡ በምንዘናናባት፡ በአሁኗ ሰዓት እንኳ፡ የአምልኮ ምልክታችን ያደረግነውን፡ ይህንኑ፡ ጽላት የያዘውን ታቦት፡ ከያለበት፡ እንዲሠረቅና እንዲሸጥ በማድረግ፡ ሲሣለቁብን፥ ሲዘባበቱብንና ሲፈነድቁብን የምናያቸው ተፃራሪዎቻችን፡ በመተባበር፡ በሚያደርሱብን ጥቃት በመጠቀም፡ ይኸው ኃይል፡ በጉዲትና በግራኝ፥ በፋሺስቱም ጊዜ የተፈጸመውን የመሰለ ጥፋትና እልቂት፡ "ሊያደርስ አይችልም!" ብለን የምንደመድምበት ምን ማስረጃ አለ? "ያለጽላት፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም" የሚሉና በሰው ሥርዓት የሚመጻደቁ ወገኖች ቢኖሩ፡ አያድርስና፡ በዚያን ጊዜ፡ ያን ጽላት የያዘ ታቦት፡ ምን ሊያደርጉት ነው? ወዴትስ ሊያደርሱት ነው? ከሥርቆት፥ ከዘረፋና ከቃጠሎ የተረፈ ቢኖር እንኳ፡ በእነዚያ የቀድሞዎቹ የመከራ ዘመናት እንደኾነው ኹሉ፡ በየጢሻው ሊጥሉት፥ በየምድራሁ ሊቀብሩት፥ ወይም በየዋሻው ሊሸሽጉት አይደለምን?

ታዲያ፥ አሁንም፡ አያድርስ እንጂ፡ እንዲህ በመኾኑ፡ በእሪቱ የአምልኮ ሥርዓት አምነው እንዲቀጥሉበት የተደረጉት፡ ኢትዮጵያውያን ወገኖች፡ በዚያን ጊዜ፡ "እንግዴህ ወዲህ፡ የእግዚአብሔር አምልኮ ቀረብን! ተቋረጠብን! ጠፋን!" ብለው ተስፋ በመቁረጥ፡ ሊያማርሩ አይደለምን?

ይልቁንም፡ በሃይማኖት ረገድ፡ እጅግ የሚያሠቅቀው፡ ያ ኹሉ ጽላት፡ ወይም ታቦት፡ አካላዊ ቃል፡ እግዚአብሔር ወልድ የተቀረጸባትን፡ የእሪቷን ጽላተ ኪዳን እንደያዘችው እንደታቦተ ጽዮን እንዲመለክ ለማድረግ ሞክረው፡ ምናልባት፡ ያ ሙከራቸው፡ የሠመረላቸው ወገኖች ካሉ፡ በዚያ ኹሉ ጽላት፡ ወይም ታቦት ላይ፡ ያን የመሰለ የርኵሰት ክፉ ጽዋ በሚገጥመው ጊዜ፡ የሚደርሰውን የሃይማኖት ሽንፈት፥ የዲያብሎስንም የድል አድራጊነት ድንፋታ ማሰቡ ነው:: በዚያ ኹሉ ጽላት፡ ወይም ታቦት ምክንያት፡ ያ፡ በአዲሱ የምሕረት ኪዳን፡ *"በመንፈስና በእውነት አምልኩኝ"* ብሎ የተናገረ እግዚአብሔር፡ አሁንም እንደነዚያ አሳሳች ወገኖች እምነት፡ በዲያብሎስና በአገልጋዮቹ ተቃዋሚዎቻችን ዘንድ፡ እንደተሠረቀና እንደተዘረፈ፥ እንደተቃጠለና እንደተቀበረ፥ እንደተጣለና እንደተሸሸገ ሊቆጠር አይደለምን? ታዲያ፥ በዚህ የተሳሳተ የአምልኮ ልማድ የተነሣ፡ እንደገና ሊመጣ ካለው የቁጣ መቅሠፍት፡ ራስን ማዳን፥ ለሰማዕትነት የሚያበቃንን፡ ሃይማኖታዊ አምልኳችንንም ማትረፍ የሚቻለው እንዴት ነው?

ለዚህ ከባድ ጥያቄ፡ መልሱ፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ ከመምህራችን፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተምረን፥ ከአባቶቻችንና እናቶቻችንም ወርሰን የያዝነውን፡ እውነተኛውን፡ የአምልኮ ሥርዓታችንን ጠብቀንና አጽንተን በመገኘት ብቻ ነው" የሚል ይኾናል::

ያም፡ የአምልኮ ሥርዓት፡ ዘለዓለማዊውና ሕያዉ ጽላታችን ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፥ የእርሱ ዘለዓለማዊት ማደሪያና ሕያውት ታቦታችን ለኾነችውም፡ ለቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ "በእውነትና በመንፈስ" የምናቀርበው፡ የሃይማኖት አምልኳችን፥ እንዲሁም፡ የጾም፥ የጸሎትና የምጽዋት ምግባራችን ነው።

እነዚያ የቀደሙት ትውልዶች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፡ ለዓለም፡ በይፋ ባሳወቀችው አገራቸው ላይ የፈጸሙት የአምልኮ ስሕተትና የምግባር በደል፥ በዚያ ኃጢአታቸውም ምክንያት፡ የደረሰባቸው ያን የመሰለ አሠቃቂ እልቂት፡ "በዚህም ትውልድ ላይ ሊደገም ይኾን?" ብለን እንድናስብ፡ ኢትዮጵያዊነታችን ያስገድደናል። ከዚህ የተነሣ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸው አምላካችን፡ ይህች ሃይማኖታችንና አምልኮታችን፡ ምንም ዓይነት ሕፀፅና ነቀፅ እንዳይኖርባት አድርጎ የሠራት መኾኑን የምናውቅ፡ እኛ፡ የዘመኑ ኢትዮጵያውያን፡ ኹላችንም፡ ልንፈጽመው የሚገባን ግዳጅ አለ፤ ይኸውም፡ መጀመሪያ፡ በነፍስ ወከፍ፡ በየራሳችን፡ የአምልኳችንን አቋምና አካኼድ፡ አጥርተንና አስተካክለን፡ መገኘት ሲኾን፥ ቀጥሎ፡ ኢትዮጵያዊ ወገናችን የኾነው ኹሉ፡ ይህንኑ አውቆት እንዲከተለው ማስተማር ነው። እንዲህ በማድረግ፡ ምናልባት ይህን ትውልድ፡ ከተመሳሳዩ መቅሠፍታዊ ቅጣት ለማዳን ይቻል ይኾናል፤ በዚህም፡ የየበኩላችንን፡ ኢትዮጵያዊ ግዴታ፡ እንወጣለን። እኔንም፡ በዚህ ተልእኮ፡ እንዲህ፡ ጸንቼ፡ እንድቀጥልበት የሚያደርገኝ፡ ይህ እምነት መኾኑን ልገልጽ እወድዳለሁ።

## ሙሴና
## ኢትዮጵያዊቷ ሲጳራ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደሚነበበውና ሕያው በኾነው በኢትዮጵያውያን ትውፊት እንደሚታወቀው፡ እግዚአብሔር፡ የኋላ ኋላ፡ ለባለሙዋልነት ያበቃው፡ አገልጋዩ ሙሴ፡ በመለኮታዊ ጥበቡ፡ ከግብፅ ምድር ተሰድዶ፡ በዚያን ጊዜ፡ ምድያም ትባል ወደነበረችው፡ የኢትዮጵያውያን መኖርያ ክፍለ ሀገር እንዲመጣ አደረገው።

ሙሴም፡ እስራኤላውያን፡ ከረዥም ዘመናት የባርነት ቀምበር ተላቅቀው፡ የቃል ኪዳኑን ታቦት፡ ከእግዚአብሔር እጅ በመቀበል፡ የመጨረሻውን የድል አክሊል የሚጎናጸፉበት፡ ያ የመለኮት የማዳን ተስፋው፡ እውን የሚኾንበት ጊዜ እስኪደርስና ለዚህ ታላቅ አገልግሎት እስኪጠራ ድረስ፡ ራሱን በማዘጋጀት፡ በዚያች፡ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ቆየ። ሙሴ፡ ቀደም ባለው ሕይወቱ፡ ገና በግብፅ ሣለ፡ ከገጠሙት ኹኔታዎች፡ በተረዳው መጠን፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያውያን በሚበቃ ያውቅ ነበር። ተሰድዶ በመጣባት፡ በዚችው ምድርና በእነዚህ ሕዝብ መካከል ይኖር በነበረበት ጊዜ፡ ሲጳራ የተባለች፡ ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና ከእርሷ ልጆችን ወልዶ፡ ኢትዮጵያዊ የቤተሰብ ትዳርን መሥርቷል።

ከኹሉም ይልቅ፡ ሙሴ፡ ስለእግዚአብሔር ማንነትና ስለሥነ ፍጥረቱ ምንነት፡ ጥልቅ ምሥጢራቱን ጭምር፡ ከኢትዮጵያውያን የተማረውና ያወቀው፡ በዚያን ጊዜ ነበር። አዎን! የዔዶም ገነት በነበረችበት መካን ላይ ራሱ፡ በአካል ተገኝቶና እግሩን አሳርፎ፥ ክልሏንና አካባቢዋን በመዘዋወር ለመጎብኘት ዕድል ያገኘው፡ በዚያን ጊዜ ነበር።

ይህንኑም ኹሉ፡ ኋላ በጻፋቸው፡ በአምስቱ ብሔረ ኦሪት፡ (ዘፍጥረት፥ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኁልቊ፥ ዘዳግም) መጻሕፍቱ ውስጥ የመዘገባቸው ሐተታዎች ያስረዳሉ።

ይኸው ሙሴ፡ በኪዳነ ልቡና ላይ የተመሠረተውን፡ የኢትዮጵያውያንን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓት ተከትሎ፡ የፈጸመው የሱባዔ ዘመን፡ እግዚአብሔርን ለማወቅና በእርሱ ለማመን ከምታበቃው፡ ከመጨረሻዋ የእውቀትና የእምነት ማዕርግ አደረሰው! ይህችም ማዕርግ፡ ለመለኮታዊው ምሕረት የተመደበችውን ዕለት አምጥታ፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ ራሱን እንዲገልጥለት አደረገች! እስራኤላውያን፡ ከግብፅ የባርነት ቀምበር ነጻ የሚኾኑባትን ታላቅ ተልእኮ እንዲያከናውን፡ በዚያችው አፍታ፡ ከእግዚአብሔር የቀረበለትን ጥሪ፡ በቆራጥነት ተቀብሎ፡ በምግባር ለመፈጸም ለቻለባት ሃይማኖትም አበቃችው!

ሙሴ፡ እስራኤላውያንን፡ በእግዚአብሔር ኃይል መርቶ፥ የኤርትራንም ባሕር በተአምር አሻግሮ፡ በድል አድራጊነት፡ ከምድረ በዳው መግቢያ ሲደርስ፡ በመጀመሪያ የተቀበሉት፡ ኢትዮጵያዊት ሚስቱ ሲጳራ፥ ከእርሱ የወለደቻቸው፡ ወንዶች ልጆቹ፥ ጌርሳምና አልዓዛር፥ ደግሞ፡ እርሷንና ልጆቿን፡ በእርሱ ዘንድ ጠብቆና አቆይቶ፡ አሁን፡ ከአማቱ ከሙሴ ጋር መልሶ ያገናኛቸው፡ ራጉኤል ወይም ዮቶር የተባለው፡ አባቷ ኢትዮጵያዊው ካህን ነበሩ።

በዚህ ኹኔታ፡ ሙሴ፡ ከአማቱ ዮቶር ጋር እንደገና በመገናኘቱ፡ ቀደም ብሎ፡ በኢትዮጵያ፡ ከሚስቱ ወገኖች መካከል ባሳለፈው የዓርባ ዓመታት የህልውና ዘመኑ ውስጥ፡ ስለኢትዮጵያዊነት መሠረታዊ እምነት፥ ስለክህነት አገልግሎት ምሥጢርና ስለመለኮታዊው መንግሥት መዋቅር የቀሠመውን እውቀት፡ በበለጠ ለማጠናከር፥ ለማሳደግና ለማሟላት፡ አጋጣሚው ረድቶታል። ይህ ብቻ ሳይኾን፡ እነዚህ የእውቀቱ ዘርፎች፡ በግብር ላይ ውለው፡ የሚፈጸሙበትን ሥርዓታት ጭምር፡ በዓይኖቹ ተመልክቶ ለመረዳት የቻለበትንም ዕድል አስገኝቶለታል።

ይኸውም፡ በዚህ ግንኙነት ጊዜ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የእግዚአብሔር አምልኮታቸውን በመከተል፡ ከመልከ ጼዴቅ ወርሰውና ጠብቀው፥ ከትውልድ ወደትውልድ እያስተላለፉ ያኖሩዋቸው ሥርዓቶቻቸው፡ ምን ዓይነቶች እንደኾኑ፡ ካህኑ ዮቶር፡- ፩ኛ፡ ሙሴና አሮን፥ የእስራኤል ሽማግሌዎችም በሙሉ በተገኙበት፡ ወደፈጣሪው ባሳረገው፡ በእህሉ ቁርባንና በሚቃጠለው መሥዋዕት አማካይነት፡ የቤተ ክህነቱን ሥርዓት፥ ፪ኛ፡ ሙሴ፡ የሕዝቡን አቤቱታ ሰምቶ፡ በአግባቡና በቅልጥፍና ይወስንላቸው ዘንድ፡ ባቀረበለት የአስተዳደር ዘዴ አማካይነት፡ የቤተ ምልክናውን ሥርዓት፡ ለእስራኤላውያን በማሳየቱና በማሳወቁ ነው። በሌላ አገላለጽ፡ በእግዚአብሔር ንጉሥነት የምትመራው መለኮታዊት መንግሥት፡ የምትካሄድባቸውን፡ የቤተ ሕዝቡን፥ የቤተ ክህነቱንና የቤተ ምልክናውን ሥርዓታት፡ ኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር፡ ለሙሴ በቃልና በግብር አሳውቆታል። ሙሴም፡ ከአማቱ የተረዳውን[፳] ኹሉ ተቀብሎ፡ ከዚያኑ ጊዜ ጀምሮ፡ በተግባር ላይ አውሎታል።

"ታዲያ፥ እኔስ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"

## ስድስተኛው ቃል ኪዳን፡ ኪዳነ ዳዊት፡፡

ስድስተኛው ቃል ኪዳን፡ እግዚአብሔር፡ ከዳዊት ጋር ያደረገው ሲኾን፡ እርሱም፡ በመለኮታዊው የዘውድ ዙፋን ምልክትነት የሚታወቀው ነው፡፡ ከትውልዱ ሐረግ ለሚወለደው ዘሩ፡ የዘለዓለማዊት መንግሥቱን ዘውድ የሚያቀዳጀው መኾኑን፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ ቃል ኪዳን አማካይነት፡ ለዳዊት፡ መሐላውን አጽንቶለታል፡፡ ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ የትውልድ ሐረግ በመገኘቷ፡ የዳዊት ዘር ከኾነችው ከድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ፡ ይህ ቃል ኪዳን ደርሶ የተፈጸመበት ፍሬ፡ እርሱ መኾኑ ተረጋግጦ፡ የዳዊት ልጅ ተብሎ ተጠርቷል፡፡

### *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* ማነው?

ከዕብራውያን ታላላቅ አባቶች መካከል አንዱ የኾነው፡ የአብርሃም የልጅ ልጅና የይስሐቅ ልጅ የኾነው ያዕቆብ፡ ልጆቹን በባረከበት ጊዜ፡ ስለእያንዳንዳቸው ባሰማው የትንቢት ቃል ውስጥ፡ ይሁዳን፡ *"የአሕዛብ መታዘዝ፡ ለእርሱ የሚኾነው ገዢ* (ኢየሱስ ክርስቶስ) *እስኪመጣ ድረስ"*፡ በትረ መንግሥትን ወይም የገዢውን ዘንግ ይዞ የሚቆይ አንበሳን አስመስሎ፡ ተናግሮለታል፡፡ የዚህ ትንቢታዊ ጥቅስ ባለቤት ማንነት ሲፈለግና ሲጠበቅ ከቆየ በኋላ፡ እነሆ፡ በራእየ ዮሐንስ መጽሐፍ፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ሥርዉ ለዳዊት"* ማለትም፡ *"ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፥ እርሱም የዳዊት፥ ሥር፡ ድል ነሥቶአል"* ተብሎ በተነገረለት[፳፱]፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደርሶ የተፈጸመ መኾኑ ተረጋግጦ ታወቀ፤ ተረዳ፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ሕገ መንግሥታቸውን፥ ብሔራዊ መሪያቸውንና የአስተዳደር ሥርዓታቸውን በሚመለከት፡ ያደረጉት ዘለዓለማዊ ምርጫቸው ምን እንደኾነ፡ በአገር ደረጃ ሳይቀር፡ በቀጠለው መለኮታዊ ትውፊታቸው አማካይነት፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ ደጋግመው፡ በይፋ ገልጸዋል፡፡ በብሉያቱ ኪዳናት ላይ የተመሠረተውን አዲሱን ኪዳን፡ በጋለ መንፈሳዊ ስሜት መቀበላቸውና እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በልባቸው የጻፈው ሕጉ፡ ሕገ መንግሥታቸው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም ንግሥትነት፡ የምትመራው የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ፡ መንግሥታቸው መኾኑን፡ በፍጹም እምነት አውቀው መከተላቸው፡ የዚህ እውነታ ግዙፍ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ብሔራዊ መፈክራቸውና ምልክታቸው አድርገው የሚገለገሉበት፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው የእግዚአብሔር ቃልና ይህንኑ፡ ወደሥዕል በመተርጎም፡ ዘውድ ጭኖ፡ በትእምርተ መስቀል በተከለለ መጸር ላይ የሚውለበለብ፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የተሸከመው አንበሳ፡ ኹለቱም፡ ለዚሁ እውነታ፡ ሌሎቹ፡ ተጨባጭና ጠንካራ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

ይኸው፡ የአንበሳ ፍካሬና ምስል፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተሰጠ፡ የእርሱ ብቸኛ ሀብቱ ነው! ለሌላ ለማንም ሊኾን አይችልም፤ ሊኾንም አይገባም፡፡ ይህም፡ የአዲሱ ኪዳን መታወቂያ ዓርማ፡ በማዕከሉ ላይ ሠፍሮ የሚገኝበት፡ የብሉዩ ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ፡ የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ምልክትና ማኅተም ኾነ!